

በቅርቡ ለህትመት የሚበቃ የቤተ
ክርስቲያን ታሪክ (ክፍል ሁለት)





ከዚህ ቀደም በደራሲው
የታተሙ መጻሕፍት









# ምን ሠርተን እንለፍ?

በ

ስሜ ታደሰ

Copy Right© 2014- Sime Tadesse

All right reserved

የመጀመሪያ እትም መስከረም 2007 ዓመተ ምህረት

ስሜ ታደሰ

# ምን ሠርተን እንለፍ?

zicsime@yahoo.com.
0911 717982/0910427987

2007 ዓመተ ምህረት

## አሳታሚ

የኢትዮጵያን ባይብል ባፕቲስት ቸርች ፌሎሽፕ
Ethiopian Bible Baptist Church Fellowship

የሽፋን ንድፍ እና ገጽ ቅንብር
በሐዋርያው ጴጥሮስ

## መታሰቢያነቱ

በጌታ እረፍት ላሉት በእናትነቱዋ ወደር ለሌላት ለምንወዳትና ለማንረሳት እናታችን ለወይዘሮ አፀደ ማሞ

እውነተኛ አባት፣ አቅም ፈጣሪ ባል እና ምክሩ ጥበብ ለሞላበት ለምንወደውና ለምናከብረው ወንድማችን ከሰለሞን ሰዩም

አርቆ አሳቢ፣ የተግባርና የሰላም ሰውነቱ ለገነነብን ለምንወደውና ለምናከብረው ወንድማችን ለጳውሎስ ታደሰ

ውጤታማ ሕይወት በመኖር ምሳሌነቱ ለጎላብን ለመስፍን ኩመራ

ታማኝነት እና ቁርጠኝነት ኑሮዋ ለሆነው ለሰላማዊት አከሉግ

እና ጥበብን በብዕሩዋ ለክርስቶስ ክብር ማዋሉዋ ላስደመመን ለፅጌሬዳ አሰራት ይሁንልን።

## ልዩ ምስጋና

ለተከበረው አባቴ ለአቶ ታደሰ ገብረ ክርስቶስ

ለባለቤቴ ለዚክ ኑሩ

ለእህቴ ለኢየሩሳሌም ታደሰ እና ባለቤቷ ዳንኤል ኢያሱ

ለወንድሜ ለዮሴፍ ታደሰ

ለእህቴ ጽጌ ታደሰ

ለሙሉ ጎበና እና ለባለቤቷ አሰግደው ገረመው

ለማህሌት ሰለሞንና ለባለቤቷ ኢያሱ ገስጥ ተጫኔ

ለአቶ ዘነበ ተስፋዬ

ለወይዘሮ ሰብለወንጌል በላቸው

ለኢያሱ ዕቁባይ እንዲሁም ለመድኃኒት ዘውዴ

ለሰላም ሕፃናት መንደር

ለአቶ ሰሎሞን በለጠ

ለሚኒልክ አስፋው

እንዲሁም

ለተከበረው ወንድም ለአቶ በዛብህ ወርቅነህ

ለመጋቢ ወንድምአገኘሁ ታከለና ለሰለሞን መኮንን

ይሁንልኝ።

## ተገቢ ምስጋና

ለዚህ ሶስተኛ መጽሐፍ መገኘት ምክንያት የሆናችሁትን ሁሉ በድጋሚ ማመስገን እፈልጋለሁ፤ ቀዳሚዎቹ የቤዛ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ምዕመናን ናቸው፤ ባስተማርኩ ቁጥር አብረውኝ ሀሳብ አንሸራሽረዋል፤ በሰበኩ ቁጥር በአግባቡ ትኩረት በመስጠት አድምጠውኛል፤ ለአውደ ጥናት በቀረቡ ፅሑፎቼ ደግሞ ታዳሚዎች ሁሉ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ መልዕክቴን በተሻለ ሁኔታ እንድፅፈው አግዘውኛል እናም በ‹‹ምን ሠርተን እንለፍ?››መፅሐፍ ቅድሚያውን ይወስዳሉ።

ትምህርቶችን በፅሑፍ የመቀየር ልምድ በቤዛ ባይገኝ ኑሮ ማን ተጠቃሚ ይሆን ነበር? ማንም። አሁን ግን በቃል ያለ ይረሳል በፅሑፍ ያለ ይወረሳል እውን ሆነ። ለዚህ ደግሞ ያለ መታከት ምኞት የማይሰጡትን ፊደሎቼን በማቅናት በትዕግስት የፃፈችልኝ ፀጋ ፈቃደ ብዙ ምስጋና ይገባታል።

# መግቢያ

ይህ መግቢያ በሁለተኛው መፅሐፌ በ ለእውነት እንቁም ላይ ይገኛል፤ እሱኑ አሻሽዬ በዚህም አዲስ ዝግጅት ትተዋወቁበት ዘንድ አድርጌያለሁ።

ጥድፊያ በሞላበት ዓለም ውስጥ እየኖርን ባለበት ሰዓት ነው፤ ሌላ ተጨማሪ ሊነበብ የሚገባውን ሥራ ወደ እናንተ ያደረስኩት። ገፀ ብዙ ይመስላል ቢሆንም ግን በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን በየብቻው የሚያስተናግድ ስለሆነ አያ ሰለችም። ይህን ደግሞ የመረጥኩት ሆን ብዬ ነው። ጥቂት ማንበብ የወደደ ሁሉ ቁም ነገር አገኘበት ይሆን? ብሎ ላሰበው ቅደሚያ የመስጠት ዕድልን ለመቸር እንዲሁም ከዳር ዳር እዘልቃለሁ ለሚልም ነገሮች ሁሉ ተገምደው ወደ አንድ አቅጣጫ እየተጓዙ እንዳላቸው እንዲረዱ በመፈለጌ ዐይነተ ብዙ ርዕስ ነገሮችን አካትቼበታለሁ።

በውስጡ ለክርስቲያኖች «የባከነ ጊዜ ተብሎ» የሚሰጥ ምንም ሌላ እድል ስለሌለ ዛሬ ሠርተን ማለፍ እንዳለብን በሁሉም ፅሁፎች አሳያለሁ። በተያያዥ የንባብ ባህልን ለማዳበር ጥረት አደርጋለሁ። ከዚህም የተነሳ ያነጋገራል በምላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የተመጠኑ ለጥናት መነሻ የሆኑ ስራዎችን እንዲሁም በየራሳቸው ሊቆሙ የሚችሉ ተነበው ቶሎ ተጠናቀው ሊጠቀሙ የሚችሉ ፅሑፎችን በዝግጅቴ አካትቻለሁ።

አስነዳደሬ የይዘት ቅርርብ ያላቸውን ለማጣመር መሞከር ነው። እንግዲህ የንባብ ጊዜያችሁን ሳልሻማ እንብባችሁ ምላሻችሁን እሰማ ዘንድ ምኞቴ ነው።

ወይም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ በመቅረባቸው ለዛቸውን እንዳያጡ መጠነኛ ማሻሻያ አድርጌባቸዋለሁ። አብዛኞቹ ግን ሙሉ ለሙሉ «እንደ ወረደ» ወደ እናንተ የመጡ ስለሆኑ «የሚያነብ ሁሉ እንደ ቤርያ ሰዎች ነገሩ እንዲህ ነውን?» እያለ ያብራራውና ያሰፋው ዘንድ እፈልጋለሁ።

መልካም ንባብ

ስሜ ታደሰ



# መሸጋገሪያ

የዚህ መጽሐፍ ርዕስ "ምን ሠርተን እንለፍ?" የሚል ነው፤ በዝግጅቱ ሁሉ በሰዎች ልጆች የሚያልፍ ዘመን ውስጥ የማያልፍን ቋሚ እና  በጎ ስራን ሰርተው ማለፍ ግድ መሆኑን ያሳውቃል፤ ከዚህም የተነሳ በውስጡ ያሉት ርዕስ ነገሮች እርስ በርሳቸው ተሳስረው ይህንኑ አብይ ርዕስ ነገር ያብራራሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "...የክብር አባት የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበልጥ እንድታውቁት የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለ ማቋረጥ እለምናለሁ..." (ኤፌ 1፡15-20) ያለበትን ሁነኛ ፀሎት በአግባቡ መጣጥፎቹ ያስተዋውቃሉ፤ በመሰረቱ እግዚአብሔርን ማወቅ የሕይወት ሁነኛ ማዕከል ነው፤ ውጤታማነት በአግባቡ ሊመዘን የሚችለውም የሁሉም ነገር ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሀሳብና ማንነቱ ጋር በመተዋወቅ ሲዘልቅ ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሕይወት በመኖር ውስጥ እድገት የሚያሳየውና ለሌሎች ጥቅም የሚውለው ከአደራ ሰጪው ተገቢውን አደራ ተቀብሎ ሲገኝ ነው፤ ይህ መጽሐፍ በርካታ ርዕስ ነገሮችን ቢይዝም በየንባቡ አደራ እንዳለበት ሰው መኖር ተገቢ መሆኑን ያበስራል "...የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ አደራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኛለሁ..." ቆላ 1፡25-28 የሚለው ቃል ብዙ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነው፤ አደራ ከሚታመን ሰው በተሰጠ ጊዜ ተቀባዩ በአግባቡ ፈፅሞት ለመገኘት ጊዜውን፣ ገንዘቡን ዕውቀቱን ሁሉ በወቅቱ ይጠቀማል፤ ይልቅኑ አደራው ከልዑል እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጅ የወረደ ከሆነማ እንዴታ።

ይህ መጽሐፍ የ "ለእውነት እንቁም"ም ፈለግ ተከትሏል፤ ሀገራዊ ጉዳዮችን ይዟል፤ ወጣቶች በጊዜያቸው ሊተዋወቁት የተገባቸውን ጭብጦች አካቷል፤ የንባብ ባህልን በማዳበር መጽሐፍትን አስተዋውቋል፤ የቅርብ እና የሩቅ አርአያ ሰብ ሰዎችን በየመልዕክቱ ዳሷል፤ ጊዜው ደግሞ ሕብረትንና መተጋገዝን የሚጠይቅ መሆኑን አረጋግጧል፤ በቀደመው መጽሐፍ የሴቶች ድርሻ በቤተክርስቲያንና በሕብረተሰቡ ዘንድ ምን ሊሆን እንደተገባው እንደገለጠ ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ደግሞ "ወንድ በኢትዮጵያ አውድ ውስጥ" ያለውን ይዞታ በአግባቡ አስነብቧል።

እንግዲህ ከአንድ ንባብ ወደ ሌላ ንባብ በተሸጋገርን ቁጥር ምን ሰርተን ለማለፍ እየሰራን መሆኑን ልብ እንበል።

መልካም ንባብ

ስሜ ታደሰ

# ማውጫ


መታሰቢያነቱ

ምስጋና

መግቢያ

መሸጋገሪያ

ምን ሠርተን እንለፍ?

"ፀሐይ ሮሽሌ"

«የተሰጠኝ አደራ»

«እግዚአብሔርን... ይበልጥ እንድታውቁት እፀልያለሁ»

እርሱን እንሰብካለን

አገልጋዮቹን ጠርቶ

የምን ጎዶሎነት

ምን ፍለጋ ላግባ!

ካልተጣጣሙ ቢፋቱስ?

ቃል ኪዳንና ምንነቱ

«ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሀም ግባ...ስራህንም አድርግ...

ተማሪነት

መምህርነት

እግዚአብሔር ፀሎትን ይሰማል

ተግዳሮቶች

ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መጥቷል ወይስ ዳግም ይመጣል?

ፍልሰት - አፍላሽ እና አሜሪካ 224

«የአንድ አራሽ ንግግር» አሌ ኤሪክሰን 1928ዓ.ም. 233

ቅይማት [illegible]

ወንድ በኢትዮጵያ አውድ ውስጥ [illegible]

ወንጌላውያን፣ ዘማሪዎችና መዝሙሮቻችን [illegible]

የሕብረት ምንነት [illegible]

እግዚአብሔርን ለምን ይኮንኑታል? [illegible]

ከቆሙት በታች...[illegible]

መሪነት የሚርቁት ወይስ የሚቀርቡት? [illegible]




# ምን ሠርተን እንከፍ?

ጠቅላይ ሚኒስትራችን መለስ ዜናዊ በ2004 ዓ.ም. አርፈዋል፤ የሞቱት 57 አመታትን ኖረው ነው፤ በእሳቸው ድንገታዊ ሞት አገሪቱ አዝናለች፤ አልቅሳለች፡የዚህንም እርግጠኝነት ሁላችን በኢትዮጲያ በመኖር አይተነዋል።

የእሳቸውን የእረፍት ዜና በዚህ ዝግጅት መግቢያና ማጠቃለያ አድርጌ ያካተትኩት የ1928ቱ የአሌ ኤሪክሰን **«የአንድ አራሽ ንግግር»**ን ልከኝነት አፅንሆት ለመስጠት ነው። መፅሐፉ ሞትን አስመልክቶ «...እንግዲህ በሞታችን ቀን ከበጎ ስራችንና ጥረታችን የተነሳ መታወሻ የሚሆነን ሀብት ትተን ለማለፍ በሥራ ላይ እንሁን» ይላል።

እኔም ይህን መፅሐፍ ባነበብኩ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነበር፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መሞታቸውን በመስማት ሰንደቅ አላማችንን ዝቅ አድርገን ከፅንባ ጋር የከረምነው። አሌ ኤሪክሰን *«...ሰው ሁሉ በሕይወቱ ሳለ በጎረቤቶቹ መካከል ለራሱ መታሰቢያ ማቆም ይገባዋል፤ ሙቶ ቶሎ የሚረሳ ሰው ነፍላላና ምናምንቴ መሆኑ አይቀርም፤ በሞታችን አንድ እንኳ ባያዝንልንና ባያለቅስልን ለአንድ ሰው እንኳ ወረታ አልዋልንም ማለት ነው... በመቃብር ላይ ውድ የሆነውን የመታሰቢያ ድንጋይ ከማቆም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌልን መሰበክ ድሆችን መርዳት ይሻላል...»* (ገፅ 95-100) ማለቱንም ልብ አልኩኝ።

መለስ ዜናዊ ወንጌል ስለ መሰበካቸው ወይም ስለ መስበካቸው የማውቀው ምንም ነገር የለም፤ በወንጌል ውስጥ የተገለጡ ዕሴቶችን ግን ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲያከናውኑ ግን አይቻለው:: ይህ እውነት በመሆኑ ሀገር አልቅሷል፤ እኔም ጭምር::

*ታዲያ ይህን መንደርደሪያ በአግባቡ ጠብቄ ይልቅኑ እላለሁ፡-* «ይልቅኑ በክርስቶስ የሆነው ማኅበረሰብ በተናጥልና በጋራ ሆነው በሰው ሕይወት ውስጥ ፍቅርን ሊዘሩ ይገባል፡፡ *ታታሪነት፣ ታማኝነት፣* ስራተኝነትን እና መስዋዕትነትን በየኑሯቸው በመግለጽ ቀነ ህልፈታቸውን መጠባበቅ አለባቸው» በማለት እሞግታለሁ።

በዚህም በ ምን ሠርተን እንለፍ? ስራ ውስጥ በዋናነት ማስነበብ የፈለኩት ቤተ ክርስቲያን ብርሃንና ጨው በመሆን ራሷን እንድትገልጥ እግዚአብሔር ወስኗል፤ የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ ደግሞ ራዕይ አላቸውና ተልዕኳቸው ግብ መምታት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ ያለ እረፍት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

> «ነፍሴም ወደ አምላኳ ስጋም ወደ አፈሩ ሳይመለስ፤
> ቶሎ ቶሎ ብዬ ስራዬን ልጨርስ፡፡»

የሚለውን ዝማሬ በግልና በጋራ ስንዘምር የመዘመራችን ሁነኛ ምክንያት በመኖር ውስጥ የወንጌልን ሰባኪነት ስራን ዕለት ዕለት መስራት፣ የቤተ ክርስቲያንን ጠቀሜታ መገንዘብ፣ በእርምተ ጥቅም ሥራ ላይ መጠንከር፣ የመሪዎች ማንነትና አመራራቸውን መፈተሽ እና ልብ መግዛት ተገቢ መሆኑን በዚህ ቀዳሚ ጽሁፍ ወደ ሞት ከመሄዳችን በፊት አስነብባለሁ፡፡ በዚህ ደግሞ እተጋ ዘንድ ማርክ ዴቨር ባለውለታዬ ነው፡፡ እሱ «Nine marks for the Healthy Church» የሚል ግሩም መጽሐፍ ጽፏል በስራው የዘከራቸው ጭብጦች እኔም በሀገሬ ክርስቲያን ሆኜ ራሴን ሳገኝና ኢትዮጵያዊ ሆኜ ስለ ሀገሬ ስጨነቅ ስራዬ ፍሬያማ እንዳይሆን የሚያደርጉ እንቅፋቶችን በመለየት መጽናትን በትይዩ ደግሞ ሊጠነከሩና ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ ዋነኛ ጉዳዮች ላይ በግልና በጋራ ሳናመነታ መረባረብ የዛሬ ስራችን ሊሆን መገባቱን ልብ ብዬበታለሁ፡፡

ይህን አድርገን የዘለቅን በቀኑ መጨረሻ በጌታ ፊት እንገኛለን፤ በሞታችንም ብዙ እልቃሽ እናገኛለን፡፡

እንኪያስ የክርስቶስ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት ሊያስቡበት የሚገባቸውን ሁነኛ ምልክቶች አንድ ሁለት እያልኩ ላስነብብ፡-





# ምልክት አንድ
# የወንጌል ሰባኪነትን ስራ መስራት

በዚህ ዘመን ላይ ቆመን መጪውን ስናጤነው በየጊዜው እየተወደደ ሊሄድ የሚችል ውድ አቅርቦት «ዜና» ብቻ ሆኖ ይገኛል፡፡ ዜና ይሸጣል፣ ዓለም ዜናን ለማግኘት አግኝቶም ለመግዛት በሩጫ ላይ ነው፡፡ ዜና ትናንትን፣ ዛሬን ነገንም አመላካች ሀብት በመሆን ላይ ይገኛል፤ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ የኢንተርኔት አቅርቦቶች ሁሉ ማዕከል ያደረኩት «ዜና»ን ነው፤ ዘንድሮ የሰው ልጅ እሱን በውድ እየገዛ ነው።

በወዱ በሚቸበቸበው ዜና ውስጥ ቤተክርስቲያናት «መልካም ዜና» አለን ብለዋል፤ ይህን እንዴት እያሸጋገሩት ነው? ዴቨር መልካሙ ዜና«በጣም ደህና ነን ጌታ ይክበር» ማለትብቻ ከሆነ፤

መልካሙ ዜና «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ብሎ መመስከሩ ብቻ ከሆነ፤

መልካሙ ዜና «ኢየሱስ የአንተ ጓደኛ መሆን ይፈልጋል» የሚል ከሆነ፣

መልካሙ ዜና «በቅድስና በመኖር ጌታን ማመስገን ነው» በሚል ከቆመ ይህ ገለፃ እና እምነት ወንጌል አይደለም፤ ለመልካም ዜናነትም አቅም የለውም» ይልቅስ መልካሙ ዜና እምነትን እንዲሁም ንስሀን በሁሉ ውስጥ መግለጫው አድርጎ የቆመው ነው ይላል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ኢሳይያስ ትንቢት ከተናገረ ከ700 ዓመታት በኋላ መጣ፤በሕዝቡም መካከል ተገኝቶ የኢሳይያስን ጥቅል አነሳ፤ከዚያም ያነበበላቸው እንዲህ ይል ነበር፤-(ኢሳ.51፡7-61፡1)

> *«በተራሮች ላይ የቆሙ የምስራቹን ይዘው የሚመጡ እግሮች ሰላምንም የሚናገሩ መልካሙን ዜና የሚያበስሩ፣ ድነትን የሚያውጁ ፅዮንንም አምላክሽ ነግሶአል የሚሉ እንዴት ያማሩ ናቸው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች የምስራች እንድሰብክ እግዚአብሔር ቀብቶኛል፤ልባቸው የተሰበረውን እንድጠግን፣ ለምርኮኞች ነፃነትን፣ ለእስረኞች መፈታትን እንዳውጅ ልኮኛል...»*

የሚለውን አነበበላቸው። ይህ ንባብ የወንጌል ምንነትን ይገልፃል፤ ይጋራልም።

በዚህም ውስጥ ድነትን የሚያውጁ በመባሉ ሰዎች በሀጢአት መውደቃቸውን፣ እኛም ሀጢአተኞች መሆናችንን፣ ሀጢአትም መርዝ መሆኑን ያሳውቃል፤ ዮሐንስ ምዕራፍ ሦስት እና ኤፌሶን ምዕራፍ ሁለት ይህንኑ ያበራራሉ፤ ቅዱስ ቃሉ እግዚአብሔር ፍቅር ነው በማለት ብቻ የሚቆም አይደለም፤

ይልቁኑ ያለ ቅድስና ማንም እግዚአብሔርን ልብ ይለው፣ ያየው ዘንድ እንደማይችል ይናገራል፤(ዕብ 12፡14) ኢየሱስ ጓደኛ ብቻ ይሆን ዘንድ እንደመጣ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም፤ ይልቅስ እንደ ማር 10፡45 «የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣም» በሚለው ቃል ይገለጣል፤ ወንጌል ማዕከሉ መስቀል ነው፤ ቤዛ የመሆን ታሪክ፤ በዚያ ውስጥ ደግሞ ቃላት የማይገልፁት የመከረኝነት ፅዋ እና ድል አለበት።

ማርቆስ 1፡15 ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ ኢየሱስ መጥቶ «ጊዜው ደርሷል የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች፤ ንስሀ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ» በማለት አወጀ።

«የወንጌል ሰባኪነት» አቅም በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በጤናማነት መለኪያ የሚያኖራት ዜናዋ ተሸሞንሙኖ ከፊሉን እውነት በመግለፅ የሚቀርብ ሳይሆን ኃጢአትን በመግለፅ፣ ንስሀንና እምነትን በማወጅ ፤ ኢየሱስ መጥቼለታለሁ ያለለት ሲፈፀም በዚያን ጊዜ ምልክት አንድ ተፈፃሚ ሆነ ይባላል።

## ምልክት ሁለት
## የቤተ ክርስቲያንን ጠቀሜታ መገንዘብ

አባብን አይተውት ሳይሆን ስሙን እንኳን ጠርተውት የሚንቀጠቀጡ «Snake Phobia» ያለባቸው ሰዎች አሉ፤ አይጥን ካዩ ከሀገር የሚሰደዱ፣ ባህርን ተመልከተው የሚናጡ ሰዎች አሉ፣ የእኔ ብጤ የሆኑ ደግሞ የፎቅ ደረጃን በመውጣት እግራቸው የሚተሳሰር የከፍታ ፎቢያ ባለቤቶች ብዙ ናቸው፤ ፎቢያ ልናደርገው ብንችል፣ ልናየው ብንሞከር፡- በላያችን ላይ ጉዳት የማያስከትል ወይም ልንከላከለው የምንችለው ሆኖ ሳለ ግን ያንን እንዳንገምት በሚያደርግ ስጉነት ውስጥ የሚከት የልማድ መጠሪያ ነው።

በዚህ ዘመን ውጤታማ ሊያደርጉ በሚችሉ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ሰዎች መክረው በመጨረሻ ታዲያ ማን ያድርገው ወይም ማን ሐላፊነቱን ይውሰድ በሚባልበት ጊዜ ሁሉም ጉዳዩን ለሌላው ሊተዉ ይስተዋላል።

በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆንን አብዛኛው አማኝ ልክ ነው፤ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲመሰክር ይሰማል፤ ይህ ሆኖ ግን ሐላፊነቱን እንዲወጣ ሲጠየቅ መቀበጣጠሩን ይጀምራል፤ ሰበበ ብዙ በመሆን «ፈራሁት ባይ» ይሆናል ይህንን የመሰጠት - የCommitment Phobia ወይም ራስን ለመስጠት የመፍራት ዝንባሌ በመባል ሊጠራ ይችላል።





የቤተ ክርስቲያን አባልነት ተፈላጊ እና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፤ ማንም ከጌታ ጋ የተገናኘ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠምቆ አልያም ቤተ ክርስቲያኒቱ ያዘጋጀችውን የአባልነት ቅፅን በመሙላት አባል ሊሆን ይገባዋል።

ይህን በማድረጉ የወንጌልን ብርሀን ወደ ሰዎች ለማድረስ አቅም በሚፈጥርለት ማዕከል ራሱን ያገኘዋል፣ ከተዛቡ ትምህርቶች ራሱን እንዲጠብቅ ይታገዛል፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ይታነፃል፣ ልዑል እግዚአብሔርን የማክበር አቅምንም ያገኛል።

ይህም በአማኙ ሕይወት እንዲታይ በአጥቢያዋ ፕሮግራሞች ሁሉ ላይ መገኘት አለበት፣ አብሮ መፀለይ፣ በየጊዜውም የፍቅር ስጦታውን በመስጠት በህብረት በመሆን መጠቃቀምም ይጠበቅበታል።

የመሰጠት ፎቢያ ወይም የCommitment Phobia የመጣው ታዲያ ይህን ጊዜ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 16፡24 ላይ «ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፤መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ... ሰው በነፍሱ ምትክ ሊከፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድነው?» አለ። በዚህም ክርስቲያን ሆኖ መገኘት ዋጋ ያስከፍላል፤ ያንን ዋጋ ደግሞ ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ራሱን ሊጠይቅ ይገባዋል።»

እግዚአብሔር ለአማኞች ከሰጠው ስጦታ ውስጥ አንዱ የምትታየዋን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ነው፤ በዚያ በመሆን ፍቅርን መቀባበል፤(ዮሐ 15፡12፣17) በአንድ ላይ በመሆን ጌታን ማክበር ይቻላል፤(1ጴጥ 2፡12) በሕብረትም በመሆን ደቀ መዛሙርትነት ይታያል፤(ዮሐ 13፡34-35)። ይህ እንዳይሆን ያልተጋ አማኝ፣ ይህን መፈፀም አለመፈፀሙን የማትሰብክና የማትከታተል አጥቢያ ጤናዋ ታውኳል፤ ጤነኛ ትሆን ዘንድ «ከዳንኩ በቂ ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ተገኘሁ አልተገኘሁ» ከሚሉ ዋልጌዎች መዳን ይኖርባታል፤ በቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ተገቢውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አደራ መወጣት የየራስ መስቀልን እንደመሸከም ይቆጠራል፤ ይህ ደግሞ ተፈርቶበት ሳይሆን ተወዶበት መታየት አለበት።

## ምልክት ሦስት
## በእርምተ ጥቅም ላይ መትጋት (Church Discipline)

አማኝ በተሳሳተበት ተገኝቶ ማረም፣ የጤነኛ ቤተክርስቲያን መገለጫ ነው፤ በዚህም ጤናማ ሆኖ ማደግን፣ የሀጢአትን መዘዝ መገንዘብን በአጠቃላይ የማህበረ ምዕመኑን ጤንነት መጠበቅን፣ በጎ

ምስክርነትን በውጭ ላሉት ማቅረብንና እግዚአብሔርን ለማክበር መወሰንን አጉልቶ የማሳያ መገለጫ ስለሆነ «እርምተ ጥቅም» (Church Discipline) ተፈላጊው አምድ ነው።

የዚህን መሰረትነት ዕብራውያን 12፡ 1-4፣ ማቴ 18፡15-17፣ 1ቆሮ 5፡1-11፣ ገላ. 6፡1፣ 2ተሰ 3፡ 6-15፣ 1ጢሞ 1፡20፣ 1ጢሞ 5፡19-20፣ ቲቶ 3፡9-11 በአግባቡ አብራርተዋል፤ ለምን? እንዴት? መቼ እንደሚከናወን ሁሉ ፅፈዋል።

በርካታ አማኞች በእርምተ ጥቅም «Discipline» ላይ የሚወሩ ንግግሮችን ሁሉ በበጎ አይመለከቱም፤ ይጠሉታል፤ ይሸሹታል፤ ጭርሱኑ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንዳልሆነ በመቁጠር «ምን አገባችሁ?» ይላሉ ይህ ግን ቤተ ክርስቲያን አነማንን እንደያዘች እንኳ አለመገንዘብ ነው።

አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰዎች ስብስብ ነች። ያውም የሀጢአተኞች፤ እነርሱ መቀረፅ፣ መስተካከል፣ መማር፣ መታየት፣ መፈተሽ አለባቸው፤ እነሆን በማድረግ ደግሞ እንዲያድጉ መጣር የግድ ተፈላጊ ነው፤ ያንን ውጤት ለማስገኘት መገሰፅ፣ መንቀፍ፣ መምከር፣ እንደ ሁኔታው ለጊዜው ማራቅ፣ አግባብ በሆነ ደረጃም ማስወገድ መገለጫዋ ነው።

ብዙ ሰዎች ግን ኢየሱስ የተናገረውን በማንሳት «አትፍረዱ ይፈረድባችኋል»ን እየጠቀሱ እያስጠቀሱ ራሳቸውን ደብቀው ሊያመልጡ ይጥራሉ፤ (ማቴ. 7፡1) ግና ያንኑ መጽሐፍ ሳይለቁ እስከ ማቴ 18፡15-17 ቢዘልቁ የሚያገኙት ድንቅ የንፅህና መገለጫን ነው፤ እሱም *«ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው፤ ቢሰማህ ወንድምህን እንደገና የራስህ ታደርገዋለህ፤ ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚፀና አንድ ወይ ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው፤ እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን፤-ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አህዛብና እንደቀረጥ ሰብሳቢ ቁጠረው፤ እውነት እላችኋለሁ በምድር ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል...»* በማለት ራሱ ጌታ ያስተማራቸውን እውነት የትኛውም የክርስቶስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊያምነውና ሊታዘዘው ይገባል።

በዚህም በረከት እንጂ መርገም አይመጣም፤ በበርካታ ቤተክርስቲያናት ይህን በአግባቡ አለመታዘዝ ዕድገት የሚመስል ቡፍታን ብቻ ፈጥሮ ይታያል፤ ይህን እያንዳንዱ ልብ ሊለውና ሊታዘዘው ይገባል። እርምተ ጥቅም የፍቅርና የበረከት መገለጫ ነው፤ እግዚአብሔር አይደል እንዴ ሕዝቡን እየቆነጠጠ መስመር ሲያሲዝ የነበረው ለዚህ ደግሞ ዕብ 12ን ማጥናት ተገቢ ነው።

«ፍቅር የበደልን ብዛት ይሸፍናል፤ ወይም አትፍረዱ እንዳይፈረድባችሁ» በማለት ያለ





አውዱ ከመዘባረቅ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ጋር መገጣጠም ተገቢ ነው።

## ምልክት አራት
## የስነ መለኮት ትምህርት ተፈላጊነት ላይ መጠንከር

አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጤናማነቷ የሚረጋገጠው እግዚአብሔርን በትክክል ባወቀችው መጠን ነው፤ ልዑል እግዚአብሔርን የተረዳንበት አቅም ራሳችንን ከምናውቅበት አቅም ጋር ተያያዥነት አለው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሁሉን መፍጠሩን፣ እኛንም መምረጡን፣ ድነታችን ከእኛነታችን የተነሳ ሳይሆን ከእርሱነቱ የመነጨ መሆኑን ያስረዳል፤ ይህ እግዚአብሔር፡ ፈጣሪ፡ ሰጪ፣ የእምነታችን መነሻም መድረሻም መሆኑን ያውጅልናል፡ እሱ ቅዱስ ነው፤ አቅመኛም ነው፣ በሁሉ ስፍራ ተገኚ፤ ሁሉንም አዋቂ ነው፤ ይህን የሆነውን እግዚአብሔርን በትክክል መረዳት ራሳችንን በአግባቡ እንድንገነዘብ እና ገደባችንን እንድናውቅ ያስገድደናል።

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ታማኝ ነው። ዘፀ 34፡6-7

የመጽሐፍ ቅዱሱእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ሉቃ24፡27,45-47) (ኢሳ 53፡4-6)

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ልዑል ነው። ማቴ 6፡10 ራዕ 21፡1-4 ን ማጥናት ተገቢ ነው፤ ይልቅኑ የእግዚአብሔርን ልዑልነቱን በተመለከተ በርካታ ቤተ ክርስቲያናት ራሳቸውን በየገዛ ጥያቄዎቻቸው ውስጥ በመጣል *እውን እግዚአብሔር ልዑል ነው ወይ?* ወደሚል ግንዛቤ ሲሄዱ ይታያል፤ ይህን መስማት ከአማኞቹ መጠመቅ በፊት መጥቶ ቢሆን ያንን ሰው ባለማጥመቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ባይቀላቀል በተሻለ ወይም ቅፅ ሞልቶ ባልተቀላቀለ ይላል ማርክ ዴቨር ምክንያቱም ዋንኛ መለኪያ የሁሉ የመገንዘቢያ ማማ ነውና።

አማኞች እግዚአብሔርን በራሳቸው ልክ እንዳይቀርፁት መጠንቀቅ አለባቸው፤ እንዲህ ባደረጉ ግዜ ፈሪሀ እግዚአብሔር አይኖራቸውም፡ ለእርሱ ተገዢ አይሆኑም፤ መቅኖ ቢስ ኑሮ መለያቸው በመሆን እድሜቸውን ይገፋሉ፡ አጥቢያዋንም ያዳክማሉ ይልቅስ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱሱ" እግዚአብሔርን ማመን እርሱንም በመከተል መፅናት አለባት። ለዚህም መማር አሁንም መማር ግድ ነው፡፡

# ምልክት አምስት
# የመሪዎች ማንነትና አመራራቸውን መፈተሽ

የማርክ ዴቨር መፅሐፍ በገፅ 219 ላይ የጆርጅ ኦርዌልን Animal Farm (የእንስሳት ዕድር) መፅሐፍ ያነሳል፤ እሱን እንደ መግቢያ በመቁጠር ጉዳዩን ያብራራል፤ ኮሚኒዝምን እንመሰርታልን ያሉ ሀገራት በእኩልነት ስም ያመጡትን ጣጣ ለመዘከር ደራሲው ሰዎችን ማናገር ተወ፤- እንስሶች በሕብረት በመሆን የሰውን መንግስት በመጣል ባለሀብቱን በማስወገድ ራሳቸው ሁሉን ተቆጣጠሩ፤ ማስተዳደርም ጀመሩ፤ በአዲሱ በእንስሳት አመራር ውስጥ ግን በመጀመሪያ ትናንት በሰው ልጅ የተሰራባቸውን ግፍ ከግምት በማስገባት ያ በእነርሱ እንዳይደገም፣ እንስሳቱ ሊሻሻል የማይገባው ሰባት መሰረታዊ ሕጎችን አወጡ፤ ይህንንም እንደ መለያ በመቁጠር ፅኑ መመሪያን አፀኑ።

<u>*ሰባቱ ትዕዛዛት*</u>

1. *በሁለት እግር የሚሄድ ሁሉ ጠላት ነው።*
2. *በአራት እግር የሚሄድ ወይም ክንፍ ያለው ሁሉ ወዳጅ ነው።*
3. *ማንኛውም እንስሳ ልብስ መልበስ የለበትም።*
4. *ማንኛውም እንስሳ በአልጋ ላይ መተኛት የለበትም።*
5. *ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም።*
6. *ማንኛውም እንስሳ ማንኛውንም ሌላ እንስሳ መግደል የለበትም።*
7. *እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው።*

እነዚህ በሆታ እና በእልልታ ፀድቀው ስራ ላይ ዋሉ፤ ውሎ እያደረ ግን የብዙሀን ስምምነት የነበረው እየተሸረሸረ መጣ፤ እርስ በርስም መጠላለፍ ቀጠለ ከጥልልፉ ውስጥ አንዱ፡-

> *«...ዓሳማዎቹ እንከን በሌለው ሁኔታ ማንበብና መፃፍ አስቀድመው ችለዋል፤ ውሾቹ በቂ የማንበብ ችሎታ ነበራቸው፤ ነገርግን ሰባቱን ትዕዛዛት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር የማንበብ ፍላጎት አልነበራቸውም፤ ሙርየል የተባለችው ፍየል ከውሾች በመጠኑ በተሻለ ሁኔታ ማንበብ ችላለች፤ ደግሞም በቆሻሻው መጣያ ላይ ካገኟቸው የጋዜጦች ቁርጥራጮች ለሌሎች ታነብላቸው ነበር፤ መንደሚን የተባለው አህያ እንደ ዐሳማ የማንበብ ችሎታ ነበረው ነገር ግን በችሎታው መቼም መች ሰርቶበት አያውቅም፤ እርሱ በሚያውቀው መጠን ለማንበብ የሚያጓጓ አንዳችም ነገር እንደ ሌለ ይናገራል ከሎቨር ፊደሎቹን ሁሉ ተምሮ ሳለ ፊደሎቹን አገጣጥሞ ቃላትን ለመስራት አይችልም፤ በከለር ከ «መ» ፊደል ወዲያ ማለፍ አልቻለም... ከጊዜ በኋላ እንደታወቀው ኢጅግ ደንቆሮች ከነበሩት መካከል በጎች፣ ዶሮዎች እና ዳክዬዎች ሰባቱን ትዕዛዛት በቃል ማጥናት እንዳልቻሉ ታወቀ... (**የእንስሳት ዕድር** ገፅ 25-6)*

*ይህ ዐይነት ልዩነት እየሰፋ በመምጣት አንዱ በሌላው ላይ በመነሳት ዐሳማ የበላይነቱን ወደ መያዝ መጣ፤ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሰባቱ ትዕዛዛት ቀስ በቀስ ተወግደው፤ አንድ ትዕዛዝ ተሻሽሎ መጣ እሱም፡- «እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው ግን አንዳንድ እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው»* (የእንስሳት ዕድር ገፅ 97) የሚል ሕግ ተነበበ በማለት ገለፃው ይቀጥላል።

ቤተ ክርስቲያን በአመራሯ ይህን የመሰለ አቅጣጫ ይዛ የምትጓዝ ከሆነ ንፅህና የጎደላት ትሆናለች፤ ከዚህም የተነሳ አቅም እና ምስክርነቷ አጉል ይሆናል፡፡ ይልቅስ ማህበረ ምዕመናዊነቷን ያማከለ፣ መሰረታዊ መስፈርትን የተከተለ ክርስቶስ ተኮር የሆነ አመራር ኖሯት ራሷን ትመለከት ዘንድ ተገቢ ነው።

ክርስትና በመሪ አስፈላጊነት ላይ እምነት አለው፣ ተገቢ መሪ በሀገር፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን እንዲኖር ይፈልጋል፤ ይህንንም ለመተግበር የሚያስችሉትን መለኪያዎች ያስተዋውቃል፤ በዚህ መንገድ የመጡ መሪዎች እንዲደመጡ እንዲከበሩ ይህም በቤተ ክርስቲያን እንዲገለጥ የእግዚአብሔር መለያው ሆኖ ይሰራበታል። ይህ መሪ ሳይሆኑ መሪ ነን ያሉትን አይመለከትም።

በመሰረቱ በአብዛኞቹ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ዘንድ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው አንድ ክፍል አለ፤ ዕብ 13፡7-17 «...የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መሪዎቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ ተመልከቱ፣ በእምነታቸውም ምሰሉአቸው...» ካለ በኋላ በቁጥር 17 ላይ «...ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም፤ ምክንያቱም እነርሱ በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ፤ ስለዚህ ሥራቸውን በሀዘን ሳይሆን በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ታዘዟቸው አለበለዚያ አይበጃችሁም...» በማለት በእርግጠኝነት ይመሰክራል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ለውጤት የሚሰሩ ከሆነ ስለመሪዎቻቸው ያላቸውን ግንዛቤ እና እምነት ማስተካከል ማረምና ለተገቢው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ተገዢ መሆን አለባቸው፤ ይህን ባለ መገንዘብ በርካቶች ራሳቸውን ለቤተ ሙከራነት አብቃቅተዋል።

እንግዲህ ከላይ የተጠቃቀሙት አምስት መለያዎች በቂ ግንዛቤን ይፈጥራሉ የሚል እምነት አለኝ።

እንኪያስ ሁላችን በማንበብ ላይ እያለን አንድን ቁም ነገር ልብ እንበል፤ እሱም በአንድ ባጃጅ ጀርባ ላይ «ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን» ይላል፤ በዚህ ደግሞ ትናንትን በበጎ አስበን ነገን ለማለም ስንነሳ ትልቅ መሆን እንደምንችል በማመንም ጭምር እንደሆነ ያስረግጣል፤ ለዚህ ደግሞ እጅ ለእጅ መያያዝ የግድ ነው።

ለመያያዝ አቅም በማይፈጥሩ ጉድለቶች ላይ ማነፍነፍ ተገቢ አይደለም፣ «እናንተ ቤት ይህ አለ፤ እኛ ጋ ግን» ብሎ መፎለል አቅምን ያሳሳ ካልሆነ በቀር ኃይልን አይፈጥርም፤ ይልቅስ እጅ ለእጅ በመያያዝ በመከባበርና በመፈቃቀር «ቀን ሳለ የጌታን ፈቃድ እንፈፅም» የጤናማ ቤተ ክርስቲያን ምልክቶች ይንገሱብን፣ በሌሎችም ይገለጡ ዘንድ እንተያይበት፡ይህ ሲሆን የሴጣን ሀሳብ ይከሽፋል፤ ሥጋዊ ግንዛቤ ይሳሳል በምትኩ የእግዚአብሔር መንግስት በመሲሐይቷ ማህበረሰብ ላይ ይፀናል። ዝግጅቴ የሚጠቃለለው ጠቅላይ ሚኒስትራችንን በድጋሚ በማንሳት ነው፤ በእኔ እምነት እሳቸው በሀገራዊ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ኢትዮጵያን አስተዋውቀዋል፤ በዕድሜያቸውም ተጠቅመዋል፤ በሞታቸው ሰሞን በነበሩት የሀዘን ቀናት በጎውን ራዕይ ለማስቀጠል መበርታት እና እጅ ለእጅ ተያይዞ ሀገሪቱን ከፍ ማድረግ የብዙዎች ቃል ሆኗል። በነገራችን ላይ መለስ ዜናዊን ለዚህ ርዕስ ነገር የመመጠናቸውን ሶስት ሁነኛ ምሳሌዎችን ብጠቁምስ፡—

## አንደኛው

*“የአፍሪካ ሕብረት ፅ/ቤት ከአዲስ አበባ ተነቅሎ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በአንዱ ይሁን”* የሚል ሙግት በአንድ ወቅት ተነስቶ ነበር፤በዚያን ጊዜ አብዛኛው ለመጣው አደናጋሪ አጀንዳ ሊያዘነብል ትንሽ ሲቀር ሰውየው የመጨረሻ ተናጋሪ ሆነው ቀረቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአፍሪካ ሕብረት መመስረት ምክንያት የሆኑትን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በማንሳት ለሕብረት ዘብ እንቁም ማለታቸውን ዘከሩ፣ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሀ/ማርያምን እነሱ ለኢትዮጵያዊነት እና ለአፍሪካ ተቆርቋሪነታቸውን አወደሱ፣ ለኔልሰን ማንዴላ መጠለያና ስልጠናን ማደርጀታቸውንም አስታወሱ ወደ ኋላ መለስ ብለውም ሀገሪቱ የጣልያን ወረራን በመመከት በአድዋ በምኒሊክ እና በጣይቱ አሸናፊነት የጥቁሮች ታሪክ በኢትዮጵያ መመስረቱን መሰከሩ፤ ሲጨርሱም «ቅኝ ባለመገዛት አፍሪካዊ ምሳሌ የሆነችውን ኢትዮጵያን ትቶ የተሻለ ሌላ አቅም አለኝ የሚል ሀገር ስሙን ይጥራ» አሉ በዚህ መሰረት ጣይ ጥያቄ «እኔ አለሁ» ያለ በጊዜው አልመጣም፤ ከዚህም የተነሳ አዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት ዋና ከተማ ሆና ዘለቀች።





## ሁለተኛው

በሮም ከተማ ቆሞ ለሰባ አመታት የጣሊያንን ከተማ ሲያደምቅ የነበረውን የአክሱም ሐውልት ለሀገራቸው መሬት ማብቃታቸውም ለ“ለምን ሠርተን እንለፍ?” ሌላኛው ነጥብ ነው። ኃያላን መንግስታት አፍሪካን ሲቀራመቱ የጣሊያን አይን ከአድዋ ሽንፈት በኋላ አርባ አመታት ቆጥሮ በድጋሚ ለማጥቃት ዝግጅት አድርጎ ጠበቀን፤ በዚያን ጊዜ ነበር ሀውልታችንን(ቅርሳችንን) ከሶስት ቦታ ቆርጠው በመርከብ አጫጭነው በሀገራቸው በሮም የተከሉት፤፤በዚያም ለበርካታ አመታት ሐውልቱን አቁመው አሸናፊነታቸውን ሲዘክሩ ኖሩ፤ እርግጥ ነው የተዘረፉ ቅርሶቻችን እንዲመለሱ ብዙ ኢትዮጵያውያ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፤ ዛሬም ድረስ ይህንኑ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

መለስ ዜናዊን በተመለከተ ግን ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ ሁነኛ ቀን መጣላቸው፡- የኢትዮጵያውያን ሐውልት በቆመበት ፊት ለፊት የዓለም መንግስታት መሪዎች ተቀምጠው ባሉበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ “የሰው ወርቅ አያደምቅም ጣሊያን ዘርፋ የወሰደችውን የሀገሬን ሀውልት ዛሬ ትመልስ፤ ይህን ባለመፈፀም መመካከር ልዩነትን እንጂ ስምምነትን አያመጣም” ብለው ሞገቱ፡ ይህ ተፅዕኖ አሳዳሪ የነበረው ፅኑ ቃል ምላሽን አመጣ፤ ጣሊያን ሀብታችንን መለሰች፤ በነበረበትም ቆመ፤ ይህ በጎውን ሰርቶ በማለፍ ታሪክ ላይ የሚዘከር ሌላኛው ጉዳይ ነው።

## ሶስተኛው

ተዘካሪ የህዳሴው ግድባችን ነው፤ አባይ በአረብ አገራት ተፅዕኖ፣ በግብፅ ከኔ በላይ ላሳር ባይነት፣ የእንግሊዞችና የሀያላን መንግስታት ጣልቃ ገብነት፣ ተካተውበት ለብዙ መቶ አመታት የገዛ አባያችንን እያየነው ትቶን ሄዷል፤ ሳንጠቀምበት ተጠምተንበታል፤ ተርበን ታሪካችን አነጋጋሪ ሆኗል፤ ዛሬ ግን ይህ ታሪክ ተቀይሯል፤ ሰውየው “አባይን የደፈረ ብቸኛ መሪ” ተሰኝተው ተሸኝተዋል። ይህ የህዳሴ ግድብ እንገታችንን በሁሉ ዘንድ አስደፍቶ የነበረውን ታሪካችንን አስወግዱዋል፤ ቀና ያለን ሕዝብንና በራሱ የሚተማመን ሰራዊትን ፈጥሯል። ህዝቡም በሀገራዊ አጀንዳው ያለ ቋንቋ፤ ያለ ብሄር፤ ያለ ክልል ልዩነት እጅ ለእጅ ተሳስሮ ህብረትን አፅንቷል ሰውየው ይህንንም ፈፅመው አልፈዋል።

***

ታዲያ ከላይ የተዘከሩት ሁሉ በሁላችን የተመሰከሩ የታዩና የሆኑ ስለሆኑ ሁላችን በመኖር ውስጥ እራሳችንን እንድንፈትሽ ለሰው ልጆች ጥቅም እንድንሰራ እንዲሁም ክርስቶስን በማላቅ እና ክርስቲያናዊ እሴቶችን በማስፈን እንኖር ዘንድ ጥሪ ቀርቧል።

በቅርቡ ዶ/ር በቀለ ሻንቆ የሥዩም ተፈራን "አብሬሀ አክሁ" መጽሐፍ በፑሽኪን አዳራሽ ሲመረቅ ዶክተሩ የመክፈቻ ንግግር አድርጎ ነበር፡-እኔም ያንን በማንሳት ርዕሰ ነገሬን እቋዋጫለሁ፤ ሰውዬው ካለው ልምድ አንዱ በመካነ መቃብር በመገኘት በየሀውልቱ የተፃፉትን ማንበብ ነው። በሁሉም ሟች ሀውልቶች ላይ የጋራ ጽሑፍ አለ፤በሁሉም ላይ የተወለዱበት እና የሞቱበት ቀን ተፅፏል፤ ዶክተሩ በንግግሩ በጋራነት ካየው ምስስል አልፎ በሳጥኑ ውስጥ ያለውን ሰው አስቧል፤ ብዙዎቹ እውቀታቸውን ሳያካፍሉ፤ ልምዳቸውን ሳያጋሩ፤ እምነታቸውን ሳይገልፁ፤ ዋጋ ያለውን ሀብት ይዘው ተቀብረዋል፡ እንኪያስ ሊጽፉ የተገባቸው ሳይጽፉ፣ ማስተማር ያለባቸው ሳያስተምሩ፣ ሁነኛ መከሊት ያላቸው መከሊቱን ይዘው እንዳይቀበሩ ምን ሥርተን ለማለፍ እራሳችንን አዘጋጅተናል? ማለት አለባችሁ በማለት ተናገረ እኔም የዶክተር በቀለ ሻንቆን ጭብጥ በመጋራት ምን በመስራት ላይ ነን? እላለሁ።



# "ፀሐይ ሮሽሌ"

# "ምን ሠርተን እንኑር?"

***

*"...ሠላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና" ማቴ. 5፡9 (አመት)*

*«...ስለዚህ ሠላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ..." ሮሜ 14፡16-19 (አመት)*

ጥረት የሚያስፈልገውን ስራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንግስቱ ዜጎች ሁሉ በመመሪያነት ሰጥቷል፤ ያም መመሪያ በምድር ባሉ ሰዎች ዘንድ ሁሉ ያለልዩነት ሠላምን ማስፈን ነው፤ ሠላም ግንኙነትን ያጠነክራል፤ ልዩነትን ያጠባል፤ ሁልጊዜ ለግጭት መንስኤ የሚሆኑትን ሁሉ በአግባቡ ለመፍታት ይጥራል፤ ሠላምን በማስፈን መኖር፤ ረሀብ ቢገኝም ተካፍሎ መብላትን ይጠራልና ሁሌ ጥጋብ አለ ፤የሰውን ክብር የሚያጎድፍ ምንም ነገር ሲገጥም፤- ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩን በማወቅ መቀባበልን ያመጣል፤ እንደ ድንገት ከወላጆች ልጆች ቢለዩ፤- ሕፃናቱ አሳዳጊ አጥተው አይንከራተቱም፤ ሠላም ሁነኛ ዳኛ ሆኖ ሁሉን በያለበት ያደላድለዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላምን የማውረድ ስራን የክርስቶስ ነኝ ብሎ ራሱን ከሚያስተዋውቅ ክርስቲያን ሁሉ ፈልጓል፤ እርግጥ ነው ይህን ተፈፃሚ ለማድረግ ከራስ ጋር መታረቅ፣

የእግዚአብሔርን ፈቃድ በአግባቡ መረዳት እና አሁን መሆን የሚገባውን በጎ ነገር ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆን ቅድሚያውን ይይዛል።

የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ የተከተለው ሐዋሪያው ጳውሎስም የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅና ሰላም የሞላበት መሆኑን በመግለፅ አማኞች ተግባራዊ ኑሮአቸውን በዚሁ ማዝለቅ እንዳለባቸው ቀደም ብሎ መክሯል፤ ይህን ምክሩን እውን ለማድረግ እርስ በርሳችን በመተናነፅ ማንኛውንም በጎ ስራ በመከወን ያንን በዘላቂ ጥረት ማኖር ተገቢ ሆኗል።

***

ይህ ገለፃም በምስክር ይፀና ዘንድ ሠላምን በአግባቡ ለመግለፅ አቋም ወስዳ የተግባር ሰው የሆነችውን ፀሐይ ሮሽሊን የዚህ ፅሑፍ "የምን ሠርተን እንኑር" መገለጫዬ አደርጋታለሁ።

የተመቻቸ ኑሮ ለመኖር ኢትዮጵያን ለቃ ስዊዘርላንድ ለመኖር አቀናች፤ በዚያም ሀሳቧ እየሞላላት ባለበት በ1986 እ.ኤ.አ. ከከፈተችው የቴሌቪዥን መስኮት ዜና ሲተላለፍ ልብ አለች፤ ሰበር ዜናው ኢትዮጵያ በአሰቃቂ ረሀብ ውስጥ መውደቋን ያረዳል፤ ያየችው ምስል ያተኮረው አቅመቢስ የሆኑ ህፃናት ያለምንም እርዳታ ተርበው ሲቀበሩ፤ ወጣቶች አቅማቸው ተሟጦ በቀረው ሙጣጭ አቅም የወላጆቻቸውን ቀብር ሲምሱ ማየቷ አብረከረካት።

ሴቲቱ፡-ደንግጦ መቆምን፣ ከንፈር መጥቶ መዘንጋትን፣ ከተግባር የጎደለ ፀሎትን ሳታሰማ በቀጥታ ጥረት ሊጠይቅ የሚገባውን ስራ ለመስራት ሁኔታውን ባየችበት በዚያው ቅጽበት ወሰነች። ሀዘን፣ ለቅቃና ሞት ከበዛበት ስፍራ ደርሳ ያቅሟን ማድረግ የልብዋ ጽኑ ውሳኔ ሆኖ ተገለጠላት።

እና ያሰበችውን አደረገችው፤ ታከናውነው የነበረውን እቅዶቿን ገለበጠች፤ ምቹ ኑሮዋን ተወች፤ ሰላም፣ መረጋጋት፣ እረፍት በጎደላቸው ሁሉ ዘንድ በመድረስ ፍቅርን መዝራት ሁነኛ የኑሮ ትርጉም መሆኑን ለመግለፅ ተነሳሳች፤አደረገችውም። በዚህ ጥረቷም "ሠላም የሕፃናት መንደርን" ከሀያ አምስት አመታት በፊት በአዲስ አበባ መሰረተች።

ይህ ተቋም ዛሬ ለብዙዎች ደራሺ ሆኑዋል፤የሠላም መንደሩ ያለ ዘር፤ ያለ ሀይማኖት፣ ያለ ቋንቋ ልዩነት ሁሉን በመደገፍ ስሙን ሠላም አሰኝቶ በማህበረሰቡ ውስጥ ተገኝቷል፤ በአንድ ወቅት ፀሐይ ሮሽሊን የጠየቀ ዘጋቢ "ለሌሎች የምትሰጪው ምክር ምን ይሆናል?" ባላት ጊዜ ምላሿ "መጀመሪያ ወደ ሲዊዘርላንድ ስሄድ ብዙ ነገር መስራት እና ሀብታም ሆኖ መኖር ምኞቴ ነበር፤ አላማዬም ይኸው ነበር፤ይህ ግን አልሆነም... የልጆችን ችግር፣ ረሀብና ጉስቁልና አየሁ፤ማየቴ በብቻው በቂ ምላሽ እንደሚፈልግ ተረዳሁ፤ እናም አላማዬን ሰርዤ ወደዚህ ስራ ገባሁ፤... እኔ





ለማንም የምመክረው በዚህ አለም እስካለን ድረስ በአንድ ቀን ውስጥ አንድ ልብስ ብቻ እንለብሳለን፤ ለሆዳችን ውስን ምግብ እንመገባለን፤ መኝታችንም በአንድ አልጋ ላይ ነው... ከዚህ ውጭ ግን ለራሳችን የምናከማቸው የትኛውንም ነገር ካላካፈልነው በቀር ከጌታ በረከት አናገኝም፤... ይህን መፈፀም ደግሞ የጌታ ፈቃድ ነው..." (Seellam Children's Village 25th Anniversary 2011. p.3-4) የሚል ምላሽ ሰጥታ እንደነበር አውቃለሁ።

ታዲያ በዚያው በሰላም ሕፃናት መንደር እድጋ ለቁም ነገር የበቃችው ማሪቱ ፀጋዬ፡- ስለ ሠላም ምንነት ስትገልፅ *"...ሠላም የህፃናት መንደር እኔ የምፈልገውን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገኝን ሁሉ በማድረግ አሳድጎኛል፤ ሕይወቴን ሊለውጥ የሚችለውን ነገር ከማድረግ ጀምሮ ራሴን እስከማስቻል የደከመልኝና በምን መንገድ መጓዝ እንዳለብኝ ያሳየኝ ደግሞም በግሌ የዘላለም ሕይወትን ነፀብራቅ ያየሁበት ስፍራ ነው..."* በማለት ፅፋለች።

ይህ ምስክርነት ከሀያ አምስት አመታት በላይ በዚህ ያደጉትን፣ የሰለጠኑትንና ለቁም ነገር የበቁትን የሁሉንም ድምፅ የሚወክል ነው።

"ሠላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው" ማለት ይኸው ነው፤ "እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ለማግኘት መጣርም" የሚገለፀው በዚሁ ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን ሁሉ በሁለት ቋጠረ፤- ቀዳሚው እግዚአብሔር አምላክን በፍፁም ልብ፣ ሀሳብና ሀይል መውደድ፤ ከዚያም ቀጥሎ የሰውን ልጅ ሁሉ እንደራስ አድርጎ መውደድ የሰው ሁለንተናው ሆኖ ተገለጠ።

እንኪያስ በ«ምን ሠርተን እንለፍ» ውስጥ የሀገር መሪን መለስ ዜናዊን በማንሳት ብቻ በቂ እና የተሟላ ለውጥ አይመጣም፤ ይልቅስ በ«ምን ሠርተን እንኑር» ውስጥ ራሳቸውን ከሰፊው ሕዝብ ጋር ያስተያዩም ውጤታማን ስራ በመስራት ላይ መገኘታቸውን ማረጋገጥ የዚህ ሰነድ መልዕክት ነው።

ክርስትና በክርስቶስ ኢየሱስ ትምህርትና የመስቀል ስራ የተገነባ እምነት ነው፤ ይህን እያንዳንዱ ልብ ሊለው ይገባል፤ ሁላችን በሚያልፍ ዘመናችን የማያልፈውን የጌታን ፈቃድ በመፈፀም ለመኖር እንስማማ።

# «የተሰጠኝ አደራ»

*«...የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ አደራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኛለሁ...እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ፡- በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤(ቆላ 1፡25-28). እንግዲህ «...ሌላውን ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው» (2ቆሮ 11፡28)*

***

የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም ላይ ያሉ፣ በመምራት ላይ ያሉ፣ በማስተዳደር ላይ ያሉ ሰዎች ሊያስቡበት የሚገባ አንድ መሰረታዊ ቁም ነገር አለ።

ይህን ደግሞ ለአይሁዳውያንም ሆነ ለአህዛብ የከብሩን ወንጌል እያዳረሰ ይዘልቅ ዘንድ አደራ የተባለው ጳውሎስ በማያሻማ ቃል አኑሮታል።

ሐዋሪያው ይህን ሲያቀርብና ሲናገር በቀዳሚነት ወዳጆቹንና የስራ አጋሮችን አልጠራም፤ ስለ እነርሱም ምንም አልተናገረም፤ ስለ ራሱ ግን ተናግሯል።

ያም ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ አንድ አደራ አለ ያም አደራ በቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አገልጋይ ሆኖ መዝለቅ ነው።

የሚዘለቀውም «የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት በማቅረብ ነው» በማለት ሐዋሪያው ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ተጠርቻለሁ ይላል።





*በበኩሌ አደራ እንዴት ተፈፃሚ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ሰውየው በሞት አፋፍ ላይ ሆነው ወዳጃቸውን አስጠሩት የ 6፤8፤10 ዓመት ልጆቻቸውን በአጠገባቸው አስቁመው «እኔ መሞቴ ነው አባክህን አንድ አደራ ተቀበለኝ፤ እነዚህን ያለ እናት ያሳደጓቸውን ልጆቼን እንደ ልጆችህ ቆጥረህ ለቁም ነገር አብቃልኝ» አሉዋቸው ተጠያቂው በዕንባ ውስጥ ሆነው «እሺ ቃልህን እፈፅማለሁ አደራህን ተቀብያለሁ» አሏቸው፤አደራ ሰጪው የሶስት ቀን ዕድሜ ብቻ ነበርና የቀራቸው በሰላም አረፉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውየው ከራሳቸው ሁለት ልጆች በተጨማሪ ሶስቱንም አሳደጉ፤ ሲያሳድጉ ግን ብዙ ተግዳሮት ገጥሟቸዋል፤ ቃላቸውን ለመጠበቅ ቤታቸውን ሸጠዋል፤ ተጨማሪ ገቢ ለማስገኘት ቀን ከሌት ሰርተዋል፤ በዚህ ሁሉ በርትተው ሶስቱንም ልጆች ለቁም ነገር አብቅተው፤ ወደማይቀርበት ሄደዋል።*

አደራ ቃል ነው፤ ሊፈፀም የሚገባው ስራ ነው፤ የሰውን አደራ ለመወጣት ሰው ታማኝ ከሆነ ይልቅኑ እግዚአብሔር አገልጋዩን አደራ ብሎ ቃል ሲሰጥ እንዴት አይከበር።

በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖር የሰው ትንሽ ከሚያሰኙ ጉዳዮች አንዱ አደራ መብላት ነው «የእንጨት ሽበት» የሚያሰኘውም ይኸው ነው። በአገልግሎት ውስጥ ልዑል እግዚአብሔር በራሱ ሁሉን ነገር ማድረግ ሲችል ግን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን መስዋዕት በማድረግ ያቆማትን ቤተክርስቲያኑን ለአንድ ሰው አደራ አለ፤ ለሐዋሪያውጳውሎስ።

ይህን ደግሞ ለመፈፀም «እግዚአብሔር ቃሉን በሙላት ለምዕመናኑ ያቀርብላቸው ዘንድ አደራ አለው። ይህን ጳውሎስ ለመፈፀም ዕለት ዕለት ተጋ፤ ሆነለትም፤ ትጋቱም አገልጋይ የሚለውን ስም አስገኘለት።

በመሰረቱ እግዚአብሔር «ይሁን» ብሎ በሰጠው ባለ አደራ ላይ ይገለጣል። ልብ በሉ ሰውየው ስለታመሙ ስለሚሞቱም ቀጣዩን የልጆቻቸውን ሕይወት ለተማመኑበት ለሌላው ሰው (ለወዳጃቸው) ሰጥተዋል። እግዚአብሔር ግን እግዚአብሔር ነው፤ ሁሉን ይችላል፤ ሁሉን ያውቃል፤ በሁሉም ቦታ ይገኛል፤ እሱ «ታሞ» አቅም አጥቶ ለዛሬ ብቻ እያለ እያዘነ አደራ አይልም። ይልቅስ እግዚአብሔር ሐዋሪያው ጳውሎስን ጠርቶ ለሰዎች የሰራውን የድነት ስራ ለመግለጥ ከሰው ጋር አብሮነትን ለመመስረት፣ አማኑኤል ሆኖ እሱ ከሰው ጋር ለመሆን ሰው የሆነበትን ታሪክ እንዲተርክለት አደራ ተቀባይ ፈለገ። እግዚአብሔር አደራ ተቀባይ የፈለገው የእርሱን ቃል በሙላት ለማቅረብ ነው፤ ለዚህ ሊቀ መልአኩን ሚካኤልን፣ የምስራች አብሳሪውን ገብርኤልን ወይም ከገዛ መላዕክቱ አንዱን ለመጠቀም አልፈለገም፤ ይልቅስ ውጤታማ የሚሆንበትን በመለኮታዊ ሀይሉ ከሀጢአት ሙትነት ያነቃውን በእርሱ ስራ ሕያው ባደረገው ሰው በመጠቀም ሌሎችን ሰዎች ለዚህ

ሕይወት ማብቃትና የበቁትን በእግዚአብሔር ቃል በመሙላት የሚኖርን ሰው ፈለገ።

አደራው አንድ እና አንድ ብቻ ነው፤«የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ለወገኖች ማቅረብ»ይህን አደራ ለመፈፀም አገልጋይ ሆኖ መዝለቅ ተገቢ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ላለፉት 2000 ዓመታት በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመዋል፤ ከውስጥ ከገዛ ወገኖች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ መልኩ ተፈትናለች፣ ከውጭ ክርስቲያን ካልሆነው ማኅበረሰብ በርካታ ፈተናዎችን ተቋቁማለች ወደ ፊትም እንዲሁ ትቋቋማለች።

ተግዳሮትን በማሸነፍ የተወጡ ቤተክርስቲያናት በእርግጠኝነት ማሸነፋቸውን የምንለየው ለመቋቋም የሚያስችል ትጥቅ እንደነበራቸው ወይም እንዳልነበራቸው በመለየት ብቻ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ያስተናገዱ ክርስቲያኖችና አጥቢያዎች ብቻ ፈተናውን እየተቋቋሙ ዘልቀዋል። ለመዝለቅ መብቃት «አደራን ተቀብለው በትክክል በተወጡ አገልጋዮች» አገልግሎት ይመጣል፤ የልዑል እግዚአብሔርን ሙሉ ቃል ሳይሸቃቅጡ፣ ሳይከልሱ፣ ሳያፈዙ፣ ሳይገነጣጥሉ የእርሱን ቃል የቀደሙቱ በትጋት አስተምረዋል፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ውስጥም ሰርጎ ተግባራዊ ምላሽን እንዲሰጥ አድርገዋል፣ የበረቱ አደራ ተቀባዮች ባሉበት ሁሉ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዲያብሎስን በአግባቡ ተቋቁማለች፣ የወንጌልን ሙሉ መልዕክት ያለመቆጠብ አድርሳለች፣ በክርስትና አማካኝነት የሚመጣውን የትኛውንም መስዋዕትነት በደስታ ተቀብላለች።

አደራ ተቀብለው አደራውን በበሉ ዘንድ፣ አደራውን ሳይቀበሉ አደራ እንደተቀበሉ በቆጠሩ ዘንድ፣ በክርስቶስ ሳይሆኑ ክርስቲያን ነን ባሉት ዘንድ፣ መንፈሳዊ ለውጥ ሳይኖር መንፈሳዊ መስለው በኖሩት ዘንድ፣ ሕያዋን የተከማቹበት መስሎ ግን የሙታን ቁጥር በጨመረበት ዘንድ፣ ዲያብሎስን በፅናት የመቋቋም አቅም ሳይኖር ከእርሱ ጋር ተሻሽቶ የመኖር ዘይቤን ባሰፉት ዘንድ፣ ፍቅርን፣ ሠላምንና አንድነትን ሳይሆን ጥላቻን፣ መራኮትንና መለያየትን በነዙት ሁሉ ዘንድ የእግዚአብሔር አደራ በዚያ ተፈጻሚ አልነበረም።

ሐዋሪያው ይህ እንዳይሆን ራሱንና ፈለጉን ሊከተሉ የተገባቸውን ሁሉ «የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ አደራ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሆኛለሁ...» አለ፤ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን በመምራት፣ በመመስረት፣ በማሳደግ ላይ ላሉት ሁሉ ይህንኑ ጌታ ያለ ነቁጥ ለውጥ ይናገራል።





በየጊዜው በክርስቶስ የሚመሰረት ቤተክርስቲያን ራዕይና ተልዕኮ ከዚህ የእግዚአብሔር አደራ ሊወጣ አይችልም። እኔ በግሌ በአዲስ አበባ እና በተቀሩት የኢትዮጵያ ከተሞች በሚመሰረቱ አጥቢያዎች ሁሉ ላይ ጥልቅ ደስታ አለኝ።

ከሀያ አምስት አመታት በፊት በእናት በአባቴ ቤት መጠነኛ ውዝግብ ተነሳ፣ ትንሹ ወንድሜ ወንጌላዊ መኮንን ታደሰ እና ዛሬ በመጋቢነት የሚያገለግለው ወንድም አገኘሁ ታከለ፤ በአንድ ላይ አድረው ሊነጋጋ ሲል ቤቱን ለቀው ይወጣሉ፤ ይህን ያየች እናታችን «የት ልትሄዱ ነው?» ባለች ቁጥር «የወንጌል አደራ አለብን» በማለት ወይ ሰሜን ሸዋ ወይ ምስራቅ ሸዋ ወይም ከዚያ አልፈው አገልግለው እንደሚመለሱ ይገልፁላታል።

*መደጋገሙ ያሳሰበው አባታችን «ወንድም አገኘሁ አዲስ አበባ ስንቱን ጉድ ተሸክማ እያለች በዚህ ያለውን ሕዝብ በወንጌል ሳትደርሱ በዚህ ያለውን ስራ ሳትጨርሱ ምን አሻግሮ ያስኬዳችኋል?»* አላቸው።

«አዲስ አበባ እያለ! የምን እንክርት!» የአባታችን ንግግር ነው፤ ይህ አባባል የወንጌልን ሩጫ የጊታ የሚመስል አንድምታ ያለው ይምሰል እንጂ እውነት ግን አለበት፤ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነች፤ አዲስ አበባ የአፍሪካም ዋና ከተማ ነች፤ አዲስ አበባ የተባበሩት መንግስታት በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ቢሮዋቻቸውንና ራሳቸውን ይዘው የሚገኙባት ከተማ ነች፤ አዲስ አበባ የመላው ኢትዮጵያውያንም ከተማ ነች፤ ሁሉን ቋንቋዎች እና ሁሉን ብሔር ብሔረሰቦች የያዘች ከተማ ናት።

ሀዲስ አለማየሁ በጊዜው የአዲስ አበባን ኖሙና ይዛ ስላለች አዲስ ከተማ ሲፅፍ *«...አዲስ ከተማ በኢትዮጵያ ከሚሰራውና ከሚፈራውም ሌላ ኬላ እየሰበረ፣ ቀረጥ ሳይከፈልበት ለሚገባው የውጭ አገር እቃ ለአብዛኛው መደብር ስለሆነች የአዲስ አበባ ወይዛዝርትና መኮዋንንት ሸማግሌና ባልቴት፣ ወጣቶችና ህፃናት፣ የውጭ አገር እቃ ለመግዛት እዚያ መሄድ አለባቸው፤ አዲስ ከተማ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ እንዲሁም የዘመናዊት ኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና የስራ ፍሬዋ ባንድ ላይ የሚታይባት ስለሆነች ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ከልዩ ልዩ አገር በብዛት የሚመጡ አገር ጎብኚዎች እዚያ መሄድ አለባቸው፣ አዲስ ከተማ ገጠሬው በየክፍሉ ያፈራውን ጭኖም ሆነ ተሸከም እየመጣ ለከተሜው ቸርቻሪ የሚሸጥባት ስለሆነች ከየአቅጣጫው የሚመጣው ገጠሬ ሁሉ እዚያ መሄድ አለበት፤ ተሸካሚው ተሸከም፣ ደላላው ደልሎ፣ ኢታላዩ ኢታሎ፣ ለማኙ ለምኖ፣ ሌባው ሰርቆ የለት እራቱን የሚያገኝባት ስለሆነች ሁሉም እዚያ መሄድ አለበት* (**ወንጀለኛው ዳኛ** ገፅ 89/1974 ዓ.ም) ይላሉ።

*ይቺን «...አዲስ አበባ ከፍ ሲል አፐረት ዝቅ ሲል እጦት ያዋስናታል፤ ለምሳሌ የመጓጓዣ አፐረት አለ፤ ነዋሪዎች ሚኒባስ በሚጠብቁበት ናፍቆት የመድህኒዓለምን ምፅአት አይጠብቁም... አንድ ድንገት ቢመጣ... ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በሚኒባሱ ታጭቆ የተላከለት ይመስል በታላቅ ጉጉት እየተጋፋ ወደ ሚኒባሱ በር ይሮጣል»* ይላል በዕውቀቱ (***መግባት እና መውጣት*** *በዕውቀቱ ስዩም ገፅ* 174)

ሀዲስ አለማየሁ፣ በእውቀቱም፣ አባቴም፣ እኔም በዚህ እንስማማለን፤ አዲስ አበባ ላይ በበቂ ሁኔታ ወንጌል አልተሰፋፋም፤ አደራው ተፈፃሚ በሚሆን ደረጃ ሐላፊነትን በአግባቡ አልተወጣንም፤ ከዚህም የተነሳ ከብርሀን ይልቅ ጨለማው የነገሰባት በምትመስል ከተማ ውስጥ ሁላችን አለን። በዚህች በርካታ ሚሊዮኖችን በማኖር በምታስተዳድረው ከተማ ክርስቶስ ደምቆ ከብሮ መታየት፣ መገለፅም አለበት።

የቤተ ክርስቲያናት በአዲስ አበባ መገኘት ይህን ሐላፊነት በመወጣት ለመዝለቅ ነው፤ መዝለቁ የአጩብጫቢ ቁጥር ለመጨመር፣ በግቢው ዘምሮ ከሰፈር ውጭ ዝምታን ለመምረጥ፣ ብርሀንነትን በማህበር በተገናኙ ጊዜ አድርሶ ከዚያ በኋላ ብልጭ ብሎ ድርግም የሚልን ትውልድ ለማፍራት ቤተ ክርስቲያን አልተጠራችም፤ አልተለየችም።

የመገኘቱዋ ሁነኛ ምክንያት እግዚአብሔር በዘላለም እቅዱ ያዘጋጃጀውን እነርሱን አድኖ፣ ከብርሀኑ ጋር ማገናኘት፣ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ፤ በበከተው የሰው ሕይወት እግዚአብሔር ሲሰራ ማየት፣ ወደ ክርስቶስ ቁመት የሚያድግ ሰራዊት ማደራጀት፣ ይህም በከተማዋ ለሚድኑት የሕይወት ሽታ፣ ሊጠፉ ላሉት ደግሞ የሞት ሽታ ምክንያት ለመሆን ነው፤ የተገኘችው።

ይህን ስም ከተግባር ጋር ይዛ የምትነሳው፤ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን አደራ እንዴት እንደምትወጣው ሐዋሪው ገልፆላታል፤ በዚህም ሁላችን ደስ ሊለን ይገባል። በመሰረቱ የቤተ ክርስቲያን ተከላና ምስረታ አስፈሪ አጀንዳ አይደለም፤ የማያስፈራው የስራው ጀማሪና ፈፃሚ ራሱ ልዑል እግዚአብሔር መሆኑ ነው፤እርግጥ ፈተና አለበት፤ ውጊያና ተግዳሮት አለበት፤ ቢሆንም ግን ከስራው ጋር ጌታ አብሮ አለ።

በመሰረቱ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት በቀረበበት ስፍራ ሁሉ የሚሆነው ውጤት በቆላስያስ መልእከት ውስጥ በሚገባ ተዘርዝሯል፤ «...እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ እየመከርን፣ እያስተማርን፣ እርሱን እንሰብካለን...» ቆላ 1፡25-28ይላል።





ልብ በሉ የእግዚአብሔር ሀሳብ በአግባቡ በሰዎች ልብ ውስጥ ገብቶ ተግባራዊ ምላሽ እንዲሰጥ ጥበብ አስፈልጓል፤ በዚያ ውስጥ እንደ ሰዉ ጉዳይና አይነት መምከር፤ ማስተማር፤ መስበከም ግድ ሆኗል።

የቤተ ክርስቲያን በዋና ከተማው በአዲስ አበባ እና በመላው የኢትዮጵያ ከተሞች መመስረት አደራን በአግባቡ በመፈፀም ከጌታ ብድራት" ለማግኘት ይረዳል። ይህ ፍሬያማ እንዲሆን በሀገሪቱ ያለን ሁላችን ሐላፊነት አለብን፤ መፀለይ፣ ማገዝ፣ ማፅናናት፣ ማበረታታት፤ አለብን፤ ከዳር ቆሞ ተመልካች ለመሆን ማንም አልተጠራም።

እኛ ሰውዬ ያለ እናት ያሳደጓቸውን ልጆቻቸውን ለወዳጃቸው በመስጠት ሰላማዊ ሞት ሞቱ፤ አደራ ተቀባዩ ሰውየም በብዙ ድካም አደራቸውን ከዳር እንዳደረሱ አንብበናል። እኔና እናንተ በእግዚአብሔር ተፈልገን ልዑል የሆነው እሱ አደራን ሰጥቶናል፤ ይህን እየፈፀምን በጌታ ፊት እንገኝ ዘንድ ዛሬ እግዚአብሔር ተፈላጊነታችንን ያበስርልናል።

***

*ተከታዮቹን ሶስት ንባባት አንብበን ከጨረስን በኋላ ወደ አንድ ስምምነት እንድንደርስ እፈልጋለሁ፤ እግዚአብሔርን ይበልጥ እንድናውቀው እንድንሀልይ፤ ሌሎች ደግሞ በመወለድ የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ እግዚአብሔርን ያውቁት ዘንድ መስራት እንዳለብን እውቃለሁ።*

*እኔ በሐዋሪያው ጳውሎስ ምክርና ፀሎት ተባርኪያለሁ።*

# «እግዚአብሔርን . . . ይበልጥ እንድታውቁት እፀልያለሁ»

## ክፍል 1

እኔና ልጄ ፅናት አርብ ጠዋት ከቴሌቭዥኑ ፊት ተገኘን፤ «እሷ በአምስት አመት ዕድሜዋ በ EBS Channel የሚተላለፈውን መንፈሳዊ መልዕክትና መዝሙር ትረዳዋለች ባልልም ግን ከውስጡ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነሱ አባባሎች ላይ ትኩረት ታደርጋለች፤ በዚያውም ዘና በማለት ትቆያለች፤ ከዚያም ከጠዋት 1:20 ሲሆን ደግሞ ሻንጣዋን አዝላ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ትንቀሳቀሳለች» በሚል እምነቴ እሷ ከኢ.ቢ.ኤስ. የሚተላለፈውን ታያለች።

እኔ ደግሞ ለቴሌቭዥኑ ጀርባዬን ሰጥቼ ከእርሷ ትይዩ ሆኜ የኢትዮጵያዊውን የነብይ ሼክ ዘካሪያስ መፅሐፍን ገረፍ ገረፍ አደርጋለሁ፤ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩ እኒህ ሰው ኋላ ላይ ከጌታ ጋር ተገናኝተው እንዴት የወንጌል አርበኛ እንደነበሩ የሚገልፅ መፅሐፍ ነው፤ እሳቸው ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ቀርበው ሳለ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ሰላሳ መጽሐፍ ቅዱስ ለአገልግሎታቸው በመስጠት በእነዚህ መፅሐፍት ስለ ክርስቶስ መስክር አሉ፤ ምኒሊክም «አንተ የክርስቶስ ገንዘብ ስለሆንህ ስምህ ከዛሬ ጀምሮ አለቃ ንዋየ ክርስቶስ ተብለህ ትጠራለህ» አሏቸው፤ በዚህ ጊዜ ሰውየው «መንግስተ ሰማይን ከሞት ወዲያ የማይ መስሎኝ ነበር እንጂ በምድር ላይ አልተጠባበቁም ነበር አሁን ግን ላደረጉልኝ ወሰን የሌለው አክብሮት እምላክ በምድር እንዳነገሱት የሰማዩን መንግስት ያውርስልኝ...» (ግንቦት 1899) ማለታቸውን እያነበብኩ እያሰላሰልኩም ሳለ ፅናት (ሚኒኒ) «አፈረስኩት ትላለች





ምኑን ነው ያፈረሰችው? እንዴት ነው የፈረሰላት?» በማለት ከንባቤ ለየችኝ።

EBS የአዜብ ሀይሉን የመዝሙር ክሊፕ ነበር ለእይታ የለቀቀው ዘማሪዋም

አመለጥኩት /3

መሀላውን ቃል ኪዳኑን አፈረስኩት

አዲስ ኪዳን አደረኩኝ ከኢየሱስ ጋራ

በጎልጎታ ቀራኒዮ በዚያ ተራራ

ነበር የምትለው ልትረዳኝ በምትችለው ሚኒን አናገርኳት «ሚኒኒ እኛ ጌታን ከምንወድበት ምክንያት አንዱ እኮ እሱ ሁላችንንም መውደዱ ነው፤ ስለሚወደን አንድ ጊዜ ሴጣን ሰብስቦ በሩን ዘግቶ እግዚአብሔር እንዳያገኘን ሲከላከል በነበረ ጊዜ «ኢየሱስ ጎበዙ ቤቱን አፈራርሶበት እኛን አወጣን ሴጣንም እያዘነ ባዶ እጁን ቀረ» ለዚህ ነው «አፈረስኩት» እያለች የምትዘምረው አልኳት እናም በቂ መልስ እንደሰጠሁ በማመን መለስ ስል «ታዲያ ለምን አፈረሰልኝ» አትልም አለችኝ። ይህን ግዜ ነው፤ ጨዋታው በ5 ለ50 መጠናቀቁ የገባኝ እሷ የእኔን 50 ዓመት አስመዘገበች እኔም 5ቷን የእርሷን ያዝኩ፤ በዚህም የዕድሜ ልውውጥ ሆነ።

ልጆች ያስባሉ፣ ያገናዝባሉ፤ የእግዚአብሔር የሆነውን ማንነቱን በማስተዋል መሰረት ያለውን ዕውቀት ሊይዙ ይችላሉ ከዚህም የተነሳ ነው መሰለኝ IEC International evangelical church የልጆች ዕድገት አቅጣጫ ይዞ በውኑ እየዘለቀ መሆኑን የምናረጋግጠው ትምህርቶች ሁሉ በመነሻነት «እግዚአብሔር» ላይ ብቻ ሲያነጣጥሩ ነው የሚል ስልት ይዘው የወጡት። እነርሱ መፅሐፍት እየመረመሩ ነው:እኔም ተቀብዬ እያጠናሁ ነው።

የተዘጋጁት መፅሀፍት ራዕይ፣ አላማና ግብ አላቸው:- እሱም «እግዚአብሔርን ራሱን እንወቀው» በሚል ተጀምሮ በዚሁ መጠናቀቁ ነው። ገለፃው ሁሉ:-

- አዳምና ሔዋን ላይ አተኩሮ ብቻ አያቆምም እነርሱን በፈጠረው በአበጀው በእግዚአብሄር ማስተዋልና ጥበብ ላይ ቆይታ ያደርጋል፤
- ኖህ ላይ እና የሰራው መርከብም ላይ ከፍተኛ ትኩረት አይሰጥም፤ ይልቅስ ውሆችን እንዴት ከሰማያት በላይ እንዳኖረ የምድርም ጥልቅ እንዴት ራሷን ከፍታ ተባባሪ እንድትሆን ባደረጋት እግዚአብሔር ላይ ዐይኑን ያነሳል፣

- አብርሀምና ሳራ ልጅ የማግኘታቸውን ደስታ ላይ ሳያተኩር «ቋሚ የፍጥረት ሕጎች»ን በመሻር የዕድሜዋን መግፋት ተቀብላ ብትስቅም እግዚአብሔር ግን ቻይ በመሆኑ ላይ ይፀናል።

- በኢያሱ «ፀሀይ ቆመች» ከሚለው ግንዛቤ ላይ ሳይተሻሽ እሱን አልፎ እግዚአብሔር ምድርን ብቻ ሳይሆን በፀሀይ ዙሪያ እየዞሩ ያሉትን በሙሉ ከነበራቸው የዘወትር እንቅስቃሴ ለፈለገው ደቂቃም ሆነ ሰዓት ቀጥ የማድረግ አቅም ባለው ላይ በማተኮር ይፀናል።

- በዳንኤል እና በተራቡት አንበሶች ላይ ብቻ ከመገረም እሱን አልፎ ዳንኤል «የገዛ እግዚአብሔሩን» የተረዳበትን አቅም፣ አንበሶች ረሀብተኞች ሆነው ሳለ በተጣለላቸው አንድ ሰው ላይ የመናጠቅ አቅም ባሳጣቸው እግዚአብሔር ላይ ያተኩራል።

- ጳውሎስ እና ተሳፋሪዎቹ በታላቁ ባህር ላይ በተፈጠረው ታላቅ ወጀብ ውስጥ የሆነውን ተከታታይ ድርጊትን መግለጥ ላይ ብቻ ሳይሆን «ማንም አይጠፋም» ያለበት እምነት መነሻውም መድረሻውም እግዚአብሔር እንዴት መሆን እንደቻለ ያብራራል።

- ሕጎች ሁሉ በሁለት ይቋጠራሉ፤ «እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ፣ ሀሳብህ፣ ሀይልህ ውደድ፣ እና ባልንጀራህን (ሰውን) እንደራስህ አድርገህ ውደድ» ከሚለው ከዚህ የህግ ፍፃሜ ላይ በመፅናት መቆምንብቻሳይሆን ይህን የገለጠው እግዚአብሔር ከእርሱነቱ ጋር ተያይዞ እሱን በማወቅ ላይ መፅናት የበለጠ በመሆኑ ላይ ያተኩራል።

***

አንድ ምሽት ላይ ምልከታዬን ወደ EBS ቻናል ድንገት ስቀይር ዝግጅቱ ሊጠናቀቅ ጥቂት ደቂቃዎች የቀሩትን «አዳዲስ ግኝቶችን የሚያስተዋውቀው»ን የሰለሞን ካሳን ዝግጅት አገኘሁት፤-

እሱ ከዶ/ር ሰለሞን ቢልልኝ ጋር እየተወያየ ነው፤ ሰውየው በሳይንስ ትምህርቱ ዘለቅት ነው፤ በተለይም በፊዚክስ ትምህርት ከፍ ከፍ ብሏል በ2004ትም (2012) በሳይንስ ግኝቶቻቸውና ዕውቀታቸውን ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በማሸጋገር ብቃት አንቱ የተሰኙ 125 ተመራማሪዎች ተለይተው በአሜሪካው ኋይት ሀውስ ተመርጠዋል።

ከእነርሱ ደግሞ 8 ሰዎች ተለይተው በፕሬዝዳንት ኦባማ መሸለም ነበረባቸው፤ ከእነዚህ አንዱ ሆነው የተለዩት ዶ/ር ሰለሞን ቢልልኝ ነበሩ። እሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን ከጠየቀ በኋላ በመጨረሻ ያቀረበው «ፕሮፌሰር ይቅርታ አድርጉልኝ እና በእግዚአብሔር ያምናሉ?» ነበር ያላቸው።





የሰውየው ምላሽ፡- ሁለቱም ይመጋገባሉ በማለት ሳይንስ በተጨባጭ ግኝቶች ላይ ራሱን የጣለ ቢመስልም በውስጡ ግን እምነትን የሚጠይቁ ጉዳዮች አሉት፤ ልናያቸው ፈፅሞ የማንችላቸው ግን ያሉ በርካታ ነገራት አሉት፤ ሳይንስ ባላየው የሚያምንበት አለው፤ ልክ እንዲሁም መንፈሳዊ ጉዳዮችን በሳይንስ ስሌት ብቻ ልንረዳው ይገባል ብለን ብንነሳ፤ ሁለት የሚመጋገቡ ግን ለመረዳት የተለያየ ስልትን የሚከተሉትን ዓለማትን መጨፈላለቅ ነው የሚሆነው፤ ይልቅስ ሳይንቲስቶች በእግዚአብሔር ላለማመን የሚያግዛቸው ምንም ዐይነት መተማመኛ የላቸውም «ሶስቱ ዕብራውያን ከእሳት ላይ ተጥለው መትረፋቸውን እግዚአብሔራዊ አድርገን ብንቀበል ወይም ብናምን እንደ ጅል ልንቆጠር አይገባም፤ ከዚህም የተነሳ እኔ በእግዚአብሔር አምናለሁ» ምላሻቸው ነበር።

***

ግና ይህንኑ ጥያቄ በቤተ ክርስቲያን ለተገኙ ሰዎች ቢቀርብ ምላሻቸው በተናጥል ምን ሊሆን ይችላል? በቤተ ክርስቲያን መገኘት በብቻው በእግዚአብሔር የማመን ማረጋገጫ ላይሆን ይችላል፤ ይልቅኑ ጥያቄውን ከፍ በማድረግ በቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር የሚያምኑ በርካቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ከእነርሱ ግን «ስንቶች እግዚአብሔርን ያውቁታል?» የሚል ጥያቄ አመንን ላሉት ሊቀርብ ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ምላሻችን፤ አምናለሁ ወይም አላምንም እንደ ማለት እናንተ ግን «ሳናውቀው ነው እንዴ የተከተልነው? ባናውቀው ነው ከምንም ጉዳይ አስበልጠን በቤተክርስቲያን መገኘትን የመረጥነው? ባናውቀው ነው የምናገለግለው? ባናውቀው ነው እንዴ የምናመሰግነው? ባናውቀው ነው?...፤ እናውቀዋለን እንጂ» ይህ የብዙ አማኞች ወቅታዊ ምላሽ ሊሆን ይችላል።

የምላሻችንን ልከኝነት ግን «ራሱን እግዚአብሔርን በማወቅ» ላይ በመምከር ፅኑ መልስ መስጠት ያስፈልጋል።

የአፄ ቴዎድሮስን ልጅ አለማየሁን እንዳስተማሩ የሚነገርላቸውና ለቴዎድሮስም ፀሀፊ ሆነው ያገለገሉት አለቃ ዘነበ እግዚብሔርን በተመለከተ ጥልቅ ግንዛቤ እንደነበራቸው ይነገራል፤ ይህንንም ስራቸውን በፅሑፍ አኑረውት ስለነበረ በ1924 በኢትዮጵያ ታተመ፤ ያንን ግን ጣሊያን አጠፋው። በ1951 ግን ተስፋ ገብረስላሴ አሳተሙት በጊዜውም ጥቂት ኮፒ ስለነበረ ሕዝቡ በእጁ እየገለበጠ አኖረው፤ በቅርቡ ግን በ1995 በዳንኤል ወርቁ ታተመ።

አለቃ ዘነበ «መፅሀፈ ጨዋታ ስጋዊ ወመንፈሳዊ» በሚለው ስራቸው የዛሬ 145 ዓመት እግዚአብሔርን እንዲህ ገልፀውታል፡-

«እግዚአብሔር ሩቅ ነው ጥበቡ አይታይምና

እግዚአብሔር ቅርብ ነው ቶሎ ይሰማልና

እግዘአብሔር መኮንን ነው፤ ቶሎ ይፈርዳልና

እግዚአብሔር እንግዳ ነው ቶሎ ወሬ ይሰማልና

እግዚአብሔር ትሁት ነው ሰውን አይንቅምና»

እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ ቶሎ ይቅር ይላልና (ገፅ 34)

***

እግዚአብሔር ሀኪም ነው ሁሉን በጥበቡ አድርጓልና

እግዚአብሔር ምስጉን ነው ፀሐይን እና ጨረቃን ፈጥሯልና

እግዚአብሔር ክቡር ነው ሰማይና ምድር የርሱ ናቸውና

እግዚአብሔር ባለፀጋ ነው ለሁሉ ይመግባልና

እግዚአብሔር ረቂቅ ነው አይጨበጥምና

እግዚአብሔር ግዙፍ ነው በዓለም ሁሉ ሞልቷልና

እግዚአብሔር ብሩህ ነው ጨለማ የለበትምና

እግዚአብሔር ኃያል ነው የሚቋቋመው የለምና (ገፅ 35)

***

እግዚአብሔር እሳት ነው እጅግ ያስፈራልና

እግዚአብሔር መካሪ ነው መፅሐፍትን ሰጥቶናልና

እግዚአብሔር አባት ነው አሳድጎናልና

እግዚአብሔር ወንድም ነው ሰው ሆኗልና

እግዚአብሔር ወዳጅ ነው የሆዱን ነግሮናልና (ገፅ 35)

***

እግዚአብሔር አገር ነው እንኖርበታለንና





እግዚአብሔር ማርና ስኳር ነው ይጣፍጣልና

እግዚአብሔር ገናና ነው የሚያህለው የለምና

እግዚአብሔር ትልቅ ነው ስፍራ አይበቃውምና

እግዚአብሔር ጥልቅ ነው በዋና አይገኝምና

እግዚአብሔር ፋሲካ ነው ለሁሉ ታርዷልና

እግዚአብሔር አመት በዓል ነው ለሁሉ ደስታ ነውና

እግዚአብሔር ጨው ነው ሁሉን ያጣፍጣልና

እግዚአብሔር ክረምት ነው ሁሉን ያበቅላልና

እግዚአብሔር አይጠረጠርም ሁሉን ያውቃልና

እግዚአብሔር አይዘነጋም በሁሉ ድካም የለበትምና

እግዚአብሔር የሰው ሎሌ ነው በክረምት ለማብቀል

በበጋ ለማብሰል የተዘጋጀ ነውና

እግዚአብሔር እንግዳ አይደለም ከጥንት የነበረ ነውና

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ጥንት ለነበረ አሁንም ላለ ኋላም ለሚኖር አሜን (ገፅ 35- 6)

***

አለቃ ዘነበ እግዚአብሔርን በተረዱበት የገለፁበት መንገድ ደስ ይላል፤ ይገጣጠምላቸው ዘንድ ደግሞ «እግዚአብሔርን ማወቅ» በቅዱሳት መጽሐፍት እና በኑሮ እንዴት እንደተገለጠ በተመጠኑ ገለፃዎቻቸው ቢያክሉልን እንዴት ጨምሮ ባስገረመን ነበር።

***

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ትምህርት በየዘርፉ ያስተዋወቀው መሰረታዊ ቁም ነገር ምን ነበር?ለዚህ ያገኘሁት አንድ መልስ ሁሉም እግዚአብሔርን ገላጮች፣ እግዚአብሔርን አሳዮች መሆናቸውን በመረዳት መደሰት ነው፤ ከዚህም የተነሳ ነው የጠራቸውን ደቀመዛሙርቱን ለሶስት አመታት እግዚአብሔርን ካሳያቸው በኋላ ያደረገው እግዚአብሔርን በማመስገን መፀለይ ነበር፤

የፀሎቱም ሁነኛ ጭብጥ በዮሐንስ 17፡3 እና 26 ላይ ይገኛል።

ቁ. 3 አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆንኸውንና የላከኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት ብሎ አመሰገነ። በዚህም ደቀመዛሙርቱ በሕይወት እስካሉ ድረስ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራቸው ዘንድ የሚያደርጋቸው እግዚአብሔር አብን እንዲሁም እግዚአብሔር ወልድን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ማወቅ መሆኑን ገለፀ፤ ይህ በውስጣቸው እያደገ በውጭ የተገለጠ ይሆን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አብ ሲፀልይም፡-

ቁጥር 26 ላይ *«... ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን እኔም በእነርሱ እንድሆን አንተን እንዲያውቁ አድርጌያለሁ እንዲያውቁህም አደርጋለሁ»* በማለት ፀሎቱን ደመደመ።

ይህን ካለ በኋላ ነው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ የቄድሮንን ሸለቆ ተሻግሮ ማዶ ወዳለው ወደ አትክልት ስፍራ ሲደርስ እግዚአብሔርን ያላወቁት በአግባቡ የካህናት አለቆች፤ ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎችን እንዲሁም ወታደሮችን ይዘው ደረሱ።

ታዲያ በዚያ ሰአት በነበረው ምልልስ ውስጥ ነበር ስምኦን ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ቀኝ ጆሮውን የቆረጠው፤ ያሰው ማልኮስ ይባል ነበር።

በዚህ ጊዜ ነበር ኢየሱስ ጴጥሮስን «ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልስ አብ የሰጠኝን ፅዋ አልጠጣምን?» በማለት ተይዞ የሄደው (ዮሐ. 18፡1-11)

ታዲያ ይህ ከመሆኑ በፊት ነው «...ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን እኔም በእነርሱ እንድሆን አንተን እንዲያውቁ አድርጌያለሁ» ያለው።

«ማድረግ» ከህሎትን በውስጡ የያዘ የድግግም ውጤት ነው፤ ኢየሱስ ያን ብቻ ብሎ አልቆመም እንዲያውቁህም «አደርጋለሁ» በማለት እግዚአብሔርን ማወቅ ቀጣይነት ያለው የተትረፈረፈ የሕይወት ምንነት መሆኑን በፀሎቱ አሳወቀ።

ከአመታት በኋላ የዚህ ፀሎት ምላሽ ሆኖ የመጣው ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉት ወገኖች ሲፅፍ እሱም እግዚአብሔር ብቻ የአማኞች ግብ መሆኑን በፀሎቱና በየመልዕክቱ ላይ አኖረ፡

-

15 *«ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ሰላላችሁ እምነት ለቅዱሳንምሁሉ ሰላላችሁ ፍቅር ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ 16. በፀሎቴ እያስታወስኋችሁ ስለ እናንተ ምስጋና ማቅረብን አላቋረጥሁም 17. የክብር*





*አባት የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበልጥ እንድታውቁት የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለማቋረጥ እለምናለሁ...» ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን እንድታውቁ እፀልያለሁ ይህም ኃይል እንደ እርሱ ታላቅ ብርታት አሰራር ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሳውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው የታየው ነው...»* (ኤፌ. 1፡15-20)በማለት ከኢየሱስ ጋር የተጣጣመ ፀሎቱን ፀለየ፤ እግዚአብሔርን አውቆ ደግሞም እያወቀው ያለለትን ልዑል የሆነውን እግዚአብሔርን እነርሱም በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ተካፋይ እንዲሆኑ አፅንቶ ፀለየ።

***

ዮሐንስ በወንጌሉ የዘላለም ሕይወትን ሲገልፅ ከዳግም መወለድ ጋር በተያያዘ አልገለፀውም ይልቅስ በእግዚአብሔር ጥሪ የዳግም ልደት ተካፋይ የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የመኖራቸው ትርጉም ራሱን እግዚአብሔርን በማወቅ ላይ የተመሰረተ መሆኑን አበሰረበት፤ ይህንኑ ደግሞ ኢየሱስ ቀድሞ በዮሐ. 14፡6አሳየ።

ይህም ኑሮ እርካታ የምላበትን ሕይወት ይገልፃል፤ ያረጋግጣልም፤ ይህም በዚህ ተግባራዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ረቂቅነቱ ሳይሆን ተጨባጭነቱን ያፀናል።

- «አይሁዶች በእግዚአብሔር አብ ያምናሉ ግን ያላወቁት አብ ያለ ወልድ የማይገለጥ መሆኑን ነው፤
- አህዛብ (አረማውያን) በፈጣሪ ሳይሆን በተፈጠሩት ላይ በመታመናቸው በከንቱ ኖረው ያልፋሉ፤
- ክርስትና ግን አብሮነት ነው፤ አብሮነት ከእግዚአብሔር አብ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ይገለጣል፤ እርሱን በማወቅ ይፀናል። ለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቁጥር 26 ላይ «... እንዲያውቁት አድርጌያለሁ፤ እንዲያውቁህም አደርጋለሁ» ያለው።
  - ማወቅ፡- ሒደት ነው፤ ጅማሬ መነሻ ቢኖረውም ቀጣይነት ኖሮት ዘላቂ አቅም የሚፈጠርበት መንገድ ነው፤
  - ማወቅ፡- አድራጊነት ወይም ተግባርን ይዞ ተገላጭ ስለሆነ ያለ ተግባር የሆነ ግንዛቤ ሁሉ ባለማወቅ ውስጥ ይካተታል፤

- ማወቅ:- ራስን መረዳትን ስለሚያመጣ በበለጠ ወደ እግዚአብሔር አቅራቢ ያደርጋል።

- ማወቅ:- የተትረፈረፈ ሕይወትን በአማኙ ኑሮ ውስጥ የሚገልፅ ነው። ይህን በአግባቡ ለመረዳት እግዚአብሔርን ከራሱ መጠሪያ በመነሳት ባህሪውን መፈተሽ ይቻላል።

«ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት፤ ፈቃዱን ማወቅና መፈፀም» የሚለው የእነ ሄንሪ ቲ እና ክለውዲ ኪንግ መፅሐፍ በገፅ 228-229 ላይ የእግዚአብሔር ስሞች፣ መጠሪያዎችና መገለጫዎች በማለት ዝርዝሩን አስነብበውናል ከቀዳሚዎቹ ውስጥ፤-

- ኤሎሂም:- እግዚአብሔር ብርቱ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው የኃያላን ሁሉ ኃያል መሆኑን የሚገልጥ ስም ነው። (GOD)

- ያህዌ:- እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊና ራሱ ህላዌ ያለው መሆኑን ገላጭ ነው። (LORD)

- አዶናይ:- እግዚአብሔር ጌታና ገዥ መሆኑን ያመለክታል። (Lord)

የእንግሊዝኛው የገለፀበትን አካሄድ የአማርኛ መፅሐፍ ቅዱስ አልተጠቀመበትም እኔም በዝግጅቴ ስሙን ለመለየት የመረጥኩት አመት (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) የተባለውን የ1993 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

አብዛኞቹ ሁሉንም መገለጫዎች «እግዚአብሔር» ብለው ስለተኩት ህሊናችን ሊያስበው የሚችልበትን አቅም አሳጥረውታል።

ቢሆንም ግን የእነዚህ ስሞች ሁነኛ ፍቺዎችን በቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ ስንፈትሽ የምናገኘው መልዕክት እግዚአብሔር በገዛ መጠሪያው ውስጥ ማንነቱን መግለጡን ነው። *«ተራራዎችን ከመስራትህ ዓለምንም ከመፍጠርህ በፊት የዘላለም አምላክ ነህ ከአንግዲህ ወዲህ የዘላለም አምላክ እንደ ኾንክ ትኖራለህ...»* (መዝ 90:2)

***

*«አቤቱ እግዚአብሐር ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ኹላቸውም እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጎናፀፊያም*





*ትለውጣቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም»* (መዝ 102: 24-27)

***

*«በሰማይና በምድር እንዲሁም በባህርና በጥልቆች እግዚአብሔር የፈቀደውን ኹሉ አደረገ»* (መዝ 135:6)

***

*እግዚአብሔር (ያህዌ) አብርሃምን እንዲህ አለው «ሳራ ካረጀሁ በኋላ ልጅ እንዴት አድርጌ እወልዳለሁ ስትል ለምን ሳቀች? ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ አመት በተባለው ጊዜ ተመልሼ እመጣለሁ ሳራም ልጅ ይኖራታል ሳራ ግን ስላፈረች «ኸረ አልሳቅሁም ብላ ዋሸች እርሱ ግን «ሳቅሽ እንጂ» አላት* (ዘፍ 18:13-15)

***

*«በዚያን ጊዜ አብርሃምና ሳራ አርጅተው ዕድሜቸው ገፍቶ ነበር ሳራምልጅ የመውለጃዋ ዕድሜ አልፎ ነበር ሳራ በልቧ ካረጀሁ በኋላ በዚህነገር መደሰት ይሆንልኛል ብላ ሳቀች»* (ዘፍ 18: 11-12) ይላል።

ዘፍጥረት ከ65 መጽሐፍት ፊት ቀሞ የሚሰጠን መረጃ በመረጃ ከተደገፈው ከእኛ የ መቶ በመቶ ማረጋገጫ የበለጠ የእግዚአብሔር ማንነት ይበልጣል የሚል ነው። እኛ ደግሞ ይህን ኑሮአችን ካደረግነው በእርግጥ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን።

***

ራሱ እግዚአብሔር:- የሰው ልጅ አካባቢውን በቅጡ እንዲረዳ የስሜት ህዋሳትን ቸረው ያያል፣ ይሰማል፣ ይዳስሳል፣ ይቀምሳል፣ ያሸታል፡በእነዚህም እርግጠኛ በመሆን ኑሮውን ይመራል።

እነርሱ በተለያየ መንገድ ካልተጠቁ የሚያመጡት ውጤት አመርቂ ነው፤ በተያያዥ «ሁሉን በጊዜው ውብ አድርጎ ሰራው» የሚልለት ማፅኛም ከጎኑ አለለት፤ በመፀነስ፣ በመውለድ፣ በህፃንነት፣ በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጎልማስነት፣ በእርጅና፣ በሞት ውስጥ አብረው ሊገኙ የሚገቧቸው መለያዎች አሉላቸው።

ለመውለድ የወንድ ዘርን በመቀበል ለማስተናገድ የሚያስችል ዕድሜ ላይ መገኘት ያስፈልጋል በአመዛኙ ከ55 ዓመት በኋላ ስለ ልጅ ማሰብ ተፈላጊ ላይሆን ይችላል። በመሰረቱ ትዳር ከልጅ ጋር የተገናኘ ሕይወት ስላልሆነ ልጅ ተወለደም፤ አልተወለደም፤ ትዳሩ በተሻለ እና ውጤታማ በሆነ ደረጃ ይዘልቃል።

ሳራ ሴት ነች፤ ለጋብቻ በደረሰ ዕድሜ ላይ አግብታለች፤ ባለቤቷም አብርሀም ነው፤ ግን ኖረው ኖረውአንድን ነገር በቅጡ አረጋገጡ፤ እሱም ልጅ መውለድ አለመቻላቸውን።

ዘፍ 16፡1 «የአብርሀም ሚስት ሦራ ልጆች አልወለደችለትም ነበር እርሷም አጋር የምትባል ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት። አብራምንም ‹እግዚአብሔር ልጅ እንዳልወልድ አድርጎኛል ምናልባት በእርሷ በኩል ልጆች አገኝ እንደሆን ሄደህ ከአገልጋዬ ጋር ተኛ» አለችው።

እሱም ተስማማ ቢስማማም ግን ትዕዛዙን ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት አልፈፀመም እንደ ዘፍ 16፡3 መሰረት ከ10 ዓመት በኋላ ነበር አብሯት የተኛው።

ሚስቱን ያለመታዘዙ ምክንያት ከዛሬ ነገን ተስፋ በማድረግ ከገዛ ሚስቱ ለመውለድ በመፈለጉ ወይም እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ መዝለቅን ምርጫው በማድረጉ አልያም ፅኑ ማረጋገጫዎች የሌሉ ያህል በመቁጠር መኖርን መርጦ ይሆናል።

ከሣራ አኳያ ግን የዕድሜዋን መዝለቅ ከግምት በማስገባት እና የቤተሰቧን ዳሀራ በማጥናት መሀን መሆኗን አፀናች፤ መረጃዋ ሚዛናዊ ነው፤ «የታገሰ ከሚስቱ ይወልዳል» ም ከጊዜ ክልል ውስጥ እንጂ ውጭ አለመሆኑን አስረገጠ፤ ሣራ በዚህ ግዜ የ65 ዓመት ሴት ነበረች፤ይህም ዕድሜ አብርሀም ከአጋር ጋር ተኛ ብላ ያዘዘችበት ጊዜ ነው፤ የ75 ዓመት ሴት ስትሆን መሆኑ ነው አብርሀም ከአጋር ጋር የተኛው ከ65 ዓመት በኋላ ትዳርን በፍቅር ማሳደግ እንጂ ስለ ተጋባን ልጅ ይኑረን የሚለውን እምነት መዘንጋት ነበረበት፤ ምክንያቱም ያሉት መረጃዎች ፈፅሞ ልጅን አያስገኙምና፣ የሚገርመው ግን አብርሀምም 100 ዓመት ሆኖት ሳለ ሳራም የ90 አመት ሴት ሆና ሳለ አብርሀምን የሚጎበኙ እንግዶች መጡ፡-

*«አብርሀም ዕድሜው 99 ዓመት በሆነው ጊዜ እግዚአብሔር (ያህዌ) ተገለጠለት «እኔ ኤልሻዳይ ነኝ...»* አለው ዘፍ 17፡1

እግዚአብሔር ራሱን ኤልሻዳይ ብሎ ሲጠራ፤ ሁሉን ቻይ መሆኑን አሳወቀ ማለት ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ሁሉን ቻይነቱን በማረጋገጥ መኖር ነው። ዘፍ 18፡1 «...እግዚአብሔርም (ያህዌ) የዛሬ አመት በዚሁ ጊዜ በእርግጥ ተመልሼ እመጣለሁ ሚስትህ ሳራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች





አለው» የ90 ዓመቷ ሳራ በድንኳን ውስጥ ሆና ይህን ሰማች «በዚያን ግዜ አብርሀምና ሣራ አርጅተው ዕድሜያቸው ገፍቶ ነበር፤ ሣራም ልጅ የመውለጃዋ ዕድሜ አልፎ ነበር» ይላል።

ሳራ ከትክክለኛ መረጃ ጋር አብሮ ላልሄደው ግጭት ምላሽን የሰጠችው በልቧ ነበር ፤ ቁ.12 ላይ ሳራ «ካረጀሁና ጌታዬም ከደከመ በኋላ በዚህ ነገር መደሰት ይሆንልኛል?» ብላ ሳቀች ቀደም ብሎ በዘፍ 17፡17 ላይ ደግሞ የአብርሀም ምላሽ «አብርሀምም...የመቶ አመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሳራ ትወልዳለችን?...» ብሎ ነበር፤ ይህንንም እሱ ያለው በግምባሩ ወድቆ በልቡ እየሳቀ የተናገረው ነው፤ በዙሪያው ያለ ማንም ሰው አልሰማውም።

ባልና ሚስቱ እግዚአብሔርን ያምናሉ፤ አማኞችም ናቸው ግን እሱን እግዚአብሔርን በአቅማቸው ልክ እንጂ በእርሱ ልክ አላወቁትም፤ ከዚህም የተነሳ የልብ ምላሻቸውን በአግባቡ አደረሱ፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ግን በእርግጠኝነት ቻይነቱን፤ በመተማመን ለእርሱ ራስን መስጠት ነው፤ እርግጠኛ የሂሳብ ስሌትን፣ የእርግጠኛ መረጃን ዋቢነት በማለፍ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ተገጣጥሞ መኖር ነው።

- እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ ማመን አለማመን ጋር፣
- ከእነርሱ መሳቅ አለመሳቅ ጋር፣
- ከእነርሱ በተለይም ከእርሷ መዋሸት ባሻገር ያለፈ ጌታ መሆኑንገለፀ። በማመን መኖር እርሱ የዘላለም ህይወት ነውና።

እግዚአብሔር ከሳራ መሀንነት፣ ከአብርሀም ተስፋ ቁራጭነት አልፎ ያለ ያህዌ መሆኑን በመረዳት፣ አዶናይ መሆኑን በመገንዘብ፣ ኤሎሂም መሆኑን በማስተዋል ለዚህ ማንነቱ ዕለት ዕለት ተገዢ መሆን ነው፤ እግዚአብሔርን ማወቅ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እሱን ያውቁት ዘንድ እግዚአብሔር አብን ያውቁት ዘንድ፣ በግላቸው ትክክለኛውን አኗኗር በመኖር ይዘልቁ ዘንድ ተከታታይ ስራን ሰራ፤ ከዚያም አልፎ ፀለየላቸው።

በዚህ ዘመን ያለን እኛ እንደ ጳውሎስ የፀሎት መልስ ሆነን እንድንገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ይህም ልዑል የሆነውን እግዚአብሔርን ተጠግቶ በማወቅና በማመን፣ በመታዘዝም ይገለፃል ካልተገለፀ የአለማወቃችን ማረጋገጫ ይሆንብናል።

እግዚአብሐር እንዳለው የ90 ዓመቷን ሴት በ91 ዓመቷ ልጅን ትወልድ ዘንድ አደረጋት፡ - በዚህም እሱ እውነተኛ ሆኖ ዘለቀ፤እሱ ሁሉን ቻይ ሆኖ ተገለጠ፤እሱ የሰውን ልብ አነበበ፤ እግዚአብሔር በሰው የመረዳት አቅምና ከአካባቢ ወጤት አኳያ የሚመዘን ሳይሆን በእውነተኛ መንገድ እሱን ማወቅ፣ ሰላምን፣ ዕረፍትንና ተስፋን በአማኝ ሕይወት ውስጥ በማኖር የኃላፊነትንና የተጠያቂነትን ልክ በግል እኗኗር በማሳየት ይዘልቅበታል፤ የኢየሱስ ፀሎት፣ የጳውሎስም ድካም ይኸው ነበር።

እንግዲህ «ያላፈረስነውን አፈረስኩት» እንዳንል በእርሱ ስራ እጃችንን እንዳንከት እና ጥንቁቅ እንድንሆን ፅሁፉ ልብ ይሰጠናል፤ እንደ ሼክ ዘካሪያስ ልበ ሰፊነትን ለክርስቶስ ስራ ያውሉበታል፤ እንደ አለቃ ዘነበ የገባቸውን ያፅፉቸዋል፤ እንደ ጳውሎስ እግዚአብሔርን ማወቅ ለራስ ሆኖ ለሌሎች እንዲሆን ያፀልያል።



# «እግዚአብሔርን... ይበልጥ እንድታውቁት እፀልያለሁ»

## ክፍል 2

«አደፍርስ»የተሰኘውን የረጅም ልብ ወለድ ስራ ያገኘሁት በብዙ ድካም ነበር፤ ታትሞ ስርጭቱ በጀመረ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሐያሳን በጋዜጣ፣ በሬድዮም ትችታቸውን አደረሱበት።

የዝክረ ነገር አዘጋጅ ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል በ1942 በየፁት መፅሐፍ «ትችት ጥንካሬን በማሳየት ካበረታ፣ *አጓጉሉንም በአግባቡ ከጠቆመ ሊመሰገን ይገባል፤ የሀገሬ ተቺዎች ግን ቀድሞ የሚመጣላቸውአጓጉሉ ብቻ ነው፤ ስራውን ዳግመኛ ሰርቶ ዕውቀቱን እንዳያሳይ የሚያደርጉ ይበዛሉ...» ያሉበትን እውነት በአደፍርስ ላይ ልብ ብያለሁ። እሳቸው ቃል በቃል ያሉትም እውነት ሆኗል እስከ ዛሬ ሰዎቻችንን አሰንፎ ያስቀራቸው «ክሪቲክ» (ሂስ) የተባለው ጦር ነው፤ ይሁን እንጂ መስራትና መንቀፍ ለየቅሉ ናቸው ቢሆንም ችሎታ ያለው ሰው በቅን መንፈስ ተመርቶ ስህተት ያገኘበትን ቢገልፅና ቢያስረዳ የሚሻሻልበትንም መንገድ ቢያመለከት ሒስ ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አይሆንም። ያላግባብ የደራሲውን መሰረታዊ ሐሳብ ሳይረዱ ለመዝለፍና ለማስተሐቀር የሚደረገው ግን የፀሐፊዎቹን እጅ የሚያሳጥር በመሆኑ አገርን እንጂ በተለይ አዘጋጅውን ብቻ የሚጎዳ አይደለም።*

*የሆነ ሆኖ «ሕልም ተፈርቶ ሳይተኙ አያድሩም» የተባለውን መሰረት አድርጎ የሒስን ጦር*

*ሳይፈሩ የተቻለውን ያህል መስራት የሚገባ ነው መፅሐፍም ለዘላለም የማይጠፋ ላገርና ለራስ ቀዋሚ የሆነ መታሰቢያ መተው ነው...»* (**ዝክረ ነገር** ገፅ ፲ ) ብለዋል።

ተቺዎቹ አደፍርስ ፍቅር እስከ መቃብርን ተከትሎ የመጣ ትልቅ ስራ መሆኑን ልብ አላሉም፣ በይዘቱ በጎ ባህላዊ እሴቶቹ ቀጣይነት ይኑራቸው በማለት በቤተሰብ የሚመጣ ጋብቻ ከዘመናዊ ተብዬው በብዙ መብለጡን ተቺዎቹ ልብ አላሉም፣ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋን ባሳደገ መልኩ ስራው ሊያመጣ የሚችለውን አቅም ከግምት ሳያስገቡ የመፅሐፉን «ርባነ ቢስነት» አወሩ፣ ፃፉበት፤ ጣርማ በርን ይፋትና ጥሙጋን እንዲሁም የሀር አምባን ዙሪያ ለመግለፅ የተጠቀመበት ቋንቋ ከብዷል ይዘቱ ባህላዊ ትውፊት ላይ ፀና ማለታቸውንም ደራሲው ሰማ፤ አነበበም። ከዚህም የተነሳ የወሰደው እርምጃ ስለራሱና ስለመፅሐፉ መከላከል ሳይሆን ወደ ገበያ የገቡትን «አደፍርሶች» በሙሉ ሰብስቦ በቤቱ ዘጋባቸው፤ ይህም ሆኖ አመታት አለፉ እንዲህም ሆኖ ግን ስሙ ይነሳል፤ ከሒሱ በፊት ተሸምተው የነበሩ መፅሐፍት በሰዎች ይዋዋሳሉ፤ ይገለባበጣሉ፤ እኔም በ70ዎቹ መጨረሻ ላይ አግኝቼ «በድህ አቅሜ» ገዝቼ «ሊዋሱት የማይገባው መፅሐፍ» ብዬ ፃፍኩበት።

***

*ዳኛቸው የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን ጣርማ በርን ተራራ ላይ ሆነው ወደ ታች ሲመለከቱት «... እግዚአብሐር ዓለሙን ሰርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርከምርኪ ያጎረበት ዕቃ ቤቱ ይመስላል...» ነበር ያለው* (ገፅ 5)

በዚህ ዕይታው እግዚአብሔር ዓለሙን በቃሉ እንደፈጠረ አላወቀም፤ «ይሁን» ብሎ እንደሆነ አልተረዳም፤ እሱ ያመነው ያወቀውም እግዚአብሔር ተራራውን፣ ሸንተረሩን፣ አቀበቱን ቁልቁለቱን አበጃጃ ፤ በእጁ ቀረፀ ከዚያም በስራው ላይ አላስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ ሰበሰበና ይፋትና ጥሙጋ ላይ አከማቸው አጎረበትም፤ በዚህ ማብራሪያ አንባቢ እያነበበ የሚያምነው፤ እግዚአብሔር በሰው ልክ በሰው አቅም እጅና እግር ኖሮት መድከሙን፣ እንዲሁም ትርፍራፊ እና ለምንም ጥቅም የማይውሉትን ራሱ እግዚአብሔር ባዘጋጀው «ቆሼ» መጣያ ላይ መጣሉን ማሳወቅ ነው።

ደራሲው እግዚአብሔር ብሎ ያለውን ባወቀበት፣ በታመነበት መንገድ ለሌላው ያሳይበታል፤ ክርስቲያኖች የሚያምኑበትና ሊያውቁት የተገባው እግዚአብሔር ግን የደራሲው እግዚአብሔር አይደለም።

***

ለኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ግን መነሻው ጣርማ በርን የመሰለችው ከፍታ ነበረች፤-ተራራ።





ሳምራዊቷ ሴት እንዲ አለች «...ጌታዬ አንተ ነብይ እንደ ሆንህ አያለሁ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤እናንተ አይሁድ ግን ሰው መስገድ ያለበት በኢየሩሳሌም (ተራራ) ነው ትላላችሁ...» (ዮሐ 4፡19-20) አለችው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እግዚአብሔርን በተመለከተ ሲመክራት «እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን ለምናውቀው እንሰግዳለን ...እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል» (ዮሐ 4፡2) አላት፤ በመሰረቱ ሳምራዊቷ ሴትን ያገኛት ይሁዳን ለቆ ወደ ገሊላ ሲሄድ ነው፤ የተጓጓዘው በሰማሪያ በኩል ነበር፤ በዚያ ማሕበረሰቡ ቅይጥ ነበር፤ ቅይጥ ቢሆንም ያህዌን ያውቃል፤ የይሁዳ ሕዝብ እነርሱን ከመናቃቸው የተነሳ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዲገኙ አይፈልጉም፤ ቢገኙ እንዳረከሱ ይቆጥራሉ።

ሰማሪያኖች ግን በሰማሪያ ከፍ ባለው ተራራ ላይ በመውጣት ያህዌን ያመልካሉ፤ ኢየሱስ ሴቲቱን «ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ» ነበር ያላት። ላለማወቃቸው መገለጫ ምክንያት ከሆኑት አንዱ እግዚአብሔርን ከፍ ወዳለ ተራራ በመውጣታቸው ብቻ እርሱን እንዳገኙት መቁጠራቸው ሁነኛ ስህተት ነበር። በመሰረቱ እግዚአብሔር በተራራም ሆነ በሸለቆ ይገኛል። ኢየሱስ ቀጥሎ «እኛ ግን«... ለምናውቀው እንሰግዳለን» በማለት የእግዚአብሔርን ማንነት ገልፀላት እሱ መንፈስ ነው። ከዚህም የተነሳ በመንፈስና በእውነት ብቻ ይሰግዱለታል» አላት።

በመሰረቱ ከፍ ያለ ስፍራን ከፍ ላለው «እግዚአብሔር መስጠት» የሰው የግንዛቤው ልክ ወይም መጠን ነው፤ እግዚብሔርን የማወቅ ትምህርት ውስጥ እግዚአብሔርን የጋረዱ እንዳይታወቅ የከለሉ ገፅታዎች ወይም እምነቶች ቢኖሩ እነርሱንም ከግምት ማስገባት መልካም ነው።

«...በየከፍታዎቹ ጉባዎች (ተራራዎች) ግፍት ሚካኤል፣ ገርጂ ሚካኤል፣ ዋንዛ በረት ሚካኤል፣ ዶቃቅት ሚካኤል፣ ሳራምባ ሚካኤል፣ ራምሴ ሚካኤል፣ ማኒያምባ ሚካኤል፣ የልቶኪ ሚካኤል፣ ዋይሎ ሚካኤል፣ ሐራምባ ሚካኤል፣ ማይድ ሚካኤል፣ ወጀ ሚካኤል፣ በቁንዲ ዙሪያ በይፋትና ጥሙጋ ይገኛሉ... (አደፍርስ ገፅ 5) ይላል አደፍርስ።

በዚህም አንባቢው እምነቱን ሲፈትሽ ስለ አንድ ሚካኤል እንዲያስብ አይሆንም፤ ስለ በርካቶቹ በተለይም በየተራራው ሆነው የእግዚአብሔርን ድርሻ የሚቋዋቋዋሙትን እንዲያስብ ይፈታተኑታል። አቅሙንም አመንምነው እይታውን ይጋርዱበታል።

ብዙዎች በአዲስ አበባ ካለው ግቢ ገብርኤልና ብስራት ገብርኤል ማን ይበልጣል ቢሏቸው አንዱን ያለማመንታት በሙሉ ልብ ይመርጣሉ፤ ያንኑ ገብርኤልን አንስተው ከቁልቢ ገብርኤልስ? ቢባሉ በርካቶች ያለ ምንም ጥርጥር ቁልቢ ገብርኤል ይላሉ።

አንድ ገብርኤል ሳለ ብዙ ገብርኤሎችን አምኖ አንዱ ከአንዱ አበላልጦ የመገንዘብ አቅም በብዙዎች ይስተዋላል፤ በዚሁ ትይዩ ግን ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደገለጠው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ይናገራሉ አንዳንዶች የሚያወሩት ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ስለሆነው ኢየሱስ አይደለም ሌላ «ልዩ ኢየሱስ» ኖሯቸው በእርሱ ያምናሉ፤ እግዚአብሔር ያልሆነ ሌላ እግዚአብሔርን ተከትለው ከኖሩ የኖሩበት ቀንም ሆነ ዓመት ከንቱ ነው፤ ከዚህም የተነሳ ከወዲሁ ሕያው እግዚአብሔርን በማወቅ አቅምን መፈተሽ ተገቢ ነው።

ይህም መሆን ያለበት እግዚአብሐርን በማወቅ የሚገኝ ጥቅም ስለ አለ ነው፤ በኤፌ 1፡ 17 «...የክብር አባት የሆነውን የጌታችንንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበልጥ እንድታውቁት እፀልያለሁ...» አለ ይህም በአጭር ምጣኔ እግዚአብሔርን እንድታውቁት እፀልያለሁ ማለቱ ነው፤ ሐዋሪያው ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ይህን ለፃፈበት በቂ ምክንያቶች አሉት፡-

አንደኛው እሱ ራሱ የሚያመልከውን እግዚአብሔርን አውቆታል ያወቀው ደግሞ እግዚአብሔርን አውቅበታለው ካለበት የራሱ እና የሀገሩ እምነት በተቃራኒ ጌታ ራሱ ተገልጦለት ስለነበር ነው የእግዚአብሔር ቃል «ሳውል ግን ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ይጥር ነበር... (ሐዋ 8፡ 3) በማለት ነው የቀድሞ ሕይወቱን ያሳወቀን በድንገት ግን ከሰማይ ብርሀን አንፀባርቆ በምድር ላይ ወደቀ «ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ» የሚል ድምፅ ሰማ (9፡4) እሱም «ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ? አለው እርሱም እኔ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ» (9፡5) አለው ቀጥሎም ግልፅ የሆነ መመሪያን ሰጠው ለሀናንያም «እርሱ ስሜን ለአረማውያንና ለነገስታት፣ ለእስራኤል ሰዎችም የሚያሳውቅ የእኔ ምርጥ መሳሪያ ስለሆነ ወደ እርሱ ሂድ፤ እሱ ስለ እኔ ምን ያህል ብዙ መከራ እንደሚቀበል አገልጥለታለሁ» (9፡15-16) አለለት።

በዚህም እኔን ያሳውቃል ይህንንም ያለ ልዩነት ለአሕዛብና ለአይሁዳውያን፣ «ለተራው» ሕዝብና ለነገስታት አድራሽ ሊሆን እንዳለው ነገረው። እግዚአብሔር እንዳለውም በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ይህ እውነት ሆኖ ዘለቀ፤ ጳውሎስ ብርሀን ከመሰለ ጨለማ ወጥቶ ብርሀኑ በየቀኑ ወደሚደምቅበት ታላቅ ብርሀን ተሸጋገረ፤ ይህን ደግሞ ዕለት ዕለት ራሱን እያወቀ እግዚአብሔርን ደግሞ በማሳወቅ ፀና።

ጳውሎስ እግዚአብሔርን አውቆታልና ነው፤ «...ሁላችሁም በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ... ሁላችሁም ክርስቶስን ለብሳችኋልና በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነፃ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ (ገላ. 3፡26-28) የማለት አቅም ያገኘው፤ ይህንንም ኖሮበት ሌሎችም ይኖሩበት ዘንድ አዘዘ።





እንግዲህ እግዚአብሔርን ያወቁ የተሰጣቸውን ሐላፊነት በቅጡ ይረዳሉ፤ ያንንም ለመፈፀም ይተጋሉ፤ ዓላማዬ ያሉትንም ነገር ከዳር ሳያደርሱ አይመለሱም፤ እግዚአብሔርን የማወቃቸው አቅም ሞትን እንኳን ቢያመጣባቸው በሞት ጥላ መካከል ያወቁት እርሱ አብሮአቸው እንዳለ ያምናሉ፤ መከራም ሆነ ሞት ወደተሻለው አሻጋሪ መጓጓዣ መሆኑን በእርግጠኝነት ያምናሉ፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ሀሳብ የሆነውን ብቻ በመፈፀም ይደሰታሉ።

ሁለተኛው፡- እግዚአብሔርን የማወቅ አቅም፡- «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» በሚል ውሳኔ ውስጥ ራስን ማግኘት ነው፤ ይህን የጳውሎስ ንግግር ብዙዎች «እንዲህ እና እንዲህ ለማለት ፈልጎ እንጂ በእርግጥ እሱ ክርስቶስን መስሎ አልኖረም» በማለት ፅፈዋል፤ ይህ ግን የገዛ ደካማ ጎናቸውን ማባብያ ሊያደርጉበት ፈልገው ካልሆነ በቀር ያለው በትክክል ነው፤ በመሰረቱ መምሰል ሊመጣ የሚችለው በትክክለኛው መንገድ ላይ እግዚአብሔርን በአግባቡ ሲያውቁት ነው፤ በዚህ ጎዳና ላይ በመሄድ እኔን ምሰሉ ለማለት ሁሉም አማኝ ራሱን ማዘጋጀቱ በራሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ጳውሎስ ብቻ አይደለም ክርስቶስን የመሰለ፤ ዮሴፍ የያዕቆብ ልጅም እኔን ምሰሉ ባይ ነው። የዘፍጥረት መፅሐፍ ድንቅ እውነቶችንና ተግባራዊ የአኗኗር ስልቶችን አኑሮልን እኛን ለተጠያቂነት ያበቃ መፅሐፍ ነው።

ዮሴፍ፡- ከያዕቆብ የመጨረሻዎቹ ልጆች አንዱ ነው፤ አባቱ ከሌሎቹ ልጆች በበለጠ ያቀርበው፤ ይወደውም ነበር፤ የዚህም አብይ ምክንያቱ በስተርጅናው ስለወለደው ነበር፤ እርጅና ብቸኝነትን ይዞ ይመጣል፤ ጤናን አጓድሎ ይተሻሻል፤ ልጆች በቅርብ ሲገኙ መጠንከርን፤ ሲርቁ ደግሞ መድከምን የሚያመጣ ኑሮ ነው፤ በዋናነት ይህን ችግሩን ዮሴፍ ይቀርፍለት ስለነበረ እንዲሁም አብልጦ ከሚወዳት ራሄል ከመወለዱ የተነሳ ለልጁ የተለየ ትኩረት አድርጓል፤ በትይዩ ዮሴፍ ከአባቱ ጋር ካለው ቀይታም የተነሳ የያዕቆብን፣ አምላክ በቅጡ አውቆታል፤ ከዚህም የተነሳ ራሱን ከልጅነት ዕድሜው ጀምሮ ይመዝነው ስለነበር፤ ሁሉን በእግዚአብሔር መነፅር ብቻ እየፈተሸ ለጥቅሙ አውሏል።

የቀኑበት ወንድሞቹ ግን ከቤት ለዩት፣ አጉላሉት፤ ከዚያም ለአንድ የግብፅ ባላባት ሸጡት፤ ለጶጢፋር፤ በዚያ በሄደበት ባዕድ ሀገር እና ቤት ግን የእግዚአብሔር ጥበቃ አልተለየውም «...እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር፤ ስለዚህም በግብፃዊው አሳዳሪው ቤት ሲኖር ሁሉ ነገር ተቃናለት...»። (ዘፍ39፡2) ዮሴፍ የተሸጠ ባሪያ ነው ከዚህም የተነሳ መብቱን ማስጠበቅ አይችልም፤እንዲህ በሆነበት ግን ተሳካለት። የፈጠረው፣ የሚጠብቀው፤ የሚመራው እና ሞገስ የሚሆነው እግዚአብሔር አብሮት

ነበረ፤ ዮሴፍ በተከበረበት በዚሁ ቤት የጶጢፋር ባለቤት ግን «...ቁመናው የተስተካከለ እና መልከ መልካም ሰው ስለነበረ አፈቀረችው» (ዘፍ 39:7) ከዚህም የተነሳ «ና ከእኔ ጋር አብረን እንተኛ» አለችው ይህንንም ደጋግማ ጠየቀችው፤ እሱም አንድ መልስ ብቻ ኖረው «...ይህን አስከፊ ኃጢአት በመፈፀም እግዚአብሔርን እንዴት አሳዝናለሁ?» አላት። (39:10) ምስክር ሊገኝ በማይችልበት ስፍራ ተገኝቶ የልቡን የማድረስ አቅሙን በእግዚአብሔር መኖርና እሱን በማወቅ ራሱን መዝኖና ወስኖ ተገኘ፤ ይህ ነው እግዚአብሔርንማወቅ።

ይህ አቋም ደግሞ ምን ግዜም ፈተናን ይዞ ነው የሚመጣው ከዚህም የተነሳ የባለቤቱ ሚስት በተቃራኒው ዮሴፍ ለሩካቤ ስጋ ሊገናኛት እንደታገላት በማድረግ አስያዘችው፤ ከዚያም ወደ ዘብጥያ አስወረወረችው።

ዮሴፍ በዚህ ገጠመኙ ስለ ራሱ መሞገትን፣ ማጉረምረምን፣ መበሳጨትን፣ አልያም ራስን ለማጥፋት መሞከርን ወይም የመበቀል አዝማሚያን ከእርሱ አንመለከትም፤ ይልቅስ «...ዮሴፍ በእስር ቤት በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ዘላለማዊ ፍቅሩን አሳየው...» (ዘፍ 39:20-21) ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ልዑልነት ያበስረናል።

በመሰረቱ ዘላለማዊ ፍቅር በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ መውደድን ያሳያል፤ ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መኖር ዮሴፍን በተገኘበት ሁሉ ችግር ፈቺ በማድረግ ስራ ብዙ አደረገው።

እንደ እውነቱ ከሆነ የዮሴፍ ታሪክ ሰፊ ነው፤ የሸጡትን ወንድሞቹን ከአመታት በኋላ አገኛቸው፤ እሱም ራሱን በመግለፅ «ዮሴፍ የሸጣችሁኝ ነኝ!» አላቸው፤ በዚህ ግዜ በወንድሞቹ ላይ ድንጋጤ ወደቀ፤ «እግዚአብሔር ከእጁ ጣለን» የልባቸው ጩኸት ሆነ፤ በዚህ ወቅት ነበር «እኔ ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ነኝ፤ ነገር ግን ይህን በእኔ ላይ በማድረጋችሁ በመፀፀት አትበሳጩ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኔን አስቀድሞ የላከኝ የሰዎችን ሕይወት እንዳተርፍ ነው ...እግዚአብሔር አስቀድሞ ወደዚህ የላከኝ በዚህ በአስደናቂ ዘዴ የእናንተን ሕይወት በማዳን በምድር ላይ ዘር እንዲቀርላችሁ አስቦ ነው፤ ስለዚህ ወደዚህ የላከኝ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም» (ዘፍ45:7-8) በማለት አፅናናቸው።

እንኪያስ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እግዚአብሔር ሁሉን በማወቁ እና በማየቱ መታመን ማለት ነው። የዮሴፍ ኑሮ ሰው የሚሆነውን በመሆን የተገለጠ ነው።





- ትንሽ ልጅ ነው፣ በአባቱ ተወደደ፣ ወንድሞቹ የአባታቸው ፍቅር ወደ እርሱ ስላጋደለ ቀኑ፤
- በመላላክ አባቱን ደስ የሚያሰኘው ልጅ በተላከበት ሳይመለስ ቀረ፣
- ወንድሞቹ በአቅማቸው ልክ ስላሰቡ እሱን ከመሀላቸው መነጠል የአባታቸውን ትኩረት ማስገኛ ወይም ትንሹ ገዢ መሆኑን መከላከያ ይሆናል ብለው አመኑ፤ ስለዚህ ጉድጓድ ጣሉት፣ አውጥተውም ሸጡት፣
- ዮሴፍ በሕይወት እስካለ ድረስ ኑሮ ቀጣይነት ስላለው ራሱን በተጣለበት ጉድጓድ፣ በተሸጠበት ቤት፣ በታሰረበት ዘበጥያ፤ ሐላፊነት በወሰደበት መስተዳድር ሁሉ መሆን ያለበትን አደረገ፤ ለአደራረጉ መለኪያ ነበረው እግዚአብሔርና ፈቃዱ፣

ሀ. አቋራጭ መንገድን በነውር አለመጠቀም፣

ለ. ሊሆን ያለውንና እውነቱን ብቻ መናገር፣

ሐ. ራሱንና እግዚአብሔርን ከሚያስነቅፍ ድርጊት መራቅ፣

መ. በእግዚአብሔር እይታ ውስጥ በመሆን «የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም»ን ግንዛቤ መሻር፣

ሠ. ማንንም መርዳት፣ ማገዝ፣ ሌላውንም በማኖር ተልዕኮ ውስጥ መገኘት፣

ረ. የሁሉም ነገር መነሻና መድረሻ በእግዚአብሔር ዕውቅናና ተቆጣጣሪነት ውስጥ እንዳለ መገንዘብን ከዮሴፍ እንማራለን፤ በዚህም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ራሱን እግዚአብሔርን ማወቅ መሆኑንም ያስረዳል።

ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ «እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደፈቃዱም ለተጠሩት ሰዎች እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለጥቅማቸው እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን» (ሮሜ 8:28) ማለት የቻለው።

እንግዲህ ዮሴፍ እኔን ምሰሉ ባይ ነው እንመስልም ማለት እግዚአብሔርን በማወቅ መኖርን መቃወም ይሆናል።

<u>ሶስተኛው:-</u> እግዚአብሔርን ማወቅ በፍፁም አሳብ እግዚአብሔርን በመውደድ መፅናት ነው። አሳብ ብዙ ነው በአንድ ሰዓት የሚነሱ አሳቦች ባንድ አመት ከሚገኙ ሰዓታት ይበዛሉ፣ አሳቦች

ተንጋግቶ የሚሄድ መንጋ ወይም ቱር ብለው የሚበሩ ወፎች ወይም የሚባዝኑ ንቦችን ይመስላሉ፣ አሳብ ከዛፍ እንደተራገፈ ቅጠል አይቆጠርም፤ ይልቅ ሀሳብ በረጅም ሰንሰለት የተያያዙ እርስ በርሳቸው የሚሳሳቡ የሰንሰለት ቀለበቶችን ይመስላሉ፣ የማይታዘዝ በሀጢአት የደከመ ሰው ከቶ የማያርፍ ዘወትር የሚናውዝ ሁከተኛ ፍጥረት ነው፣ ሁል ጊዜ አሳቦች እንደ ዝንብ ዚዚ ይላሉ እንደ ገብያ ይጀናጀናሉ፤ ይኀንደኀዳሉ እንደ ሰዓት ይዞራሉ እንደ ጊዜ ይቀለጥፋሉ...» (ከኤሊ. ኦሪክሰን የአንድ <u>አራሽ ንግግር</u> ገፅ 28 1965) የተወሰደ።

ሀሳብን በተመለከተ ይህ ያነበብነው ሰውን በትክክል ይገልፀዋል፤ አማኞች እግዚአብሔርን ከምንም ተያያዥ አሳቦች በማስቀደም ሌሎቹን ከእርሱ ቀጥሎ የሚያስከትል አቅምን ማዳበር አለባቸው።

ማሰብ በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረ ለሰው ልጅ የተሰጠ ስጦታ ነው፤ በዚህ ስጦታ በጎውን፣ ፅድቅን እና መልካም የሆነውን ሁሉ ያስብበታል፤ አብሮም ከፉውን በማስተናገዱ ይጎሳቆልበታል፤ እርባናቢስ ሕይወትን በማራመድም ይጎዱበታል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እሱንና አብን ማወቅ የዘላለም ሕይወት ነው በማለት ማስተማሩን መፀለዩንም በቀዳሚነት አስከትለንም ጳውሎስም ሆነ የቀድሞው ዮሴፍ የምንም ነገር ማዕከሉ እግዚአብሔር መሆኑን በማፅናት ኖረው ከጌታቸው ጋር ተገናኝተዋል፤ ክርስቲያኖችም ይህንኑ ፈለግ መከተል ይኖርባቸዋል፤ ይህም በፍፁም ልባችን፣ በፍፁም ሀሳባችን፣ በፍፁም ነፍሳችን እሱን መውደዳችንን ማረጋገጥ መሰረታዊ ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል።

«...በሰው ውስጥ አሳቦች ያለመከልከል ኬላውን ያልፋሉ፣ ቀረጥ የሚጥልባቸው መንግስት የለም፤ ዳኑ ምንም ነፃ ሁነው ቀረጥ ባይከፈልባቸው ያለ ቅጣት መቼም አያልፉም ጥንታዊው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ስለ ከፉ አሳባችን ተከሰን ወደ ሸንጎ የሚጎትተን ሰው የለም በኋለኛው ፍርድ ግን ስላሳደርነው ስለ ከፉ አሳባችን ሁሉ ምላሽ ልንሰጥ በዓለም ሁሉ ዳኛ ፊት እንደምንቆም እርግጥ ነው (**ኦሌ ኤሪክሰን <u>የአንድ አራሽ ንግግር</u>** ገፅ 28)

እግዚአብሔርን በማወቅ ዕድገት ውስጥ ባለመታዘዝ ባሪያ ሆነን እንድንዘገይ የሚያደርገን የውስጥ ግጭት አለብን ስጋ በመንፈስ ላይ ሁሌ ይነሳሳል መሆን የሚገባው ግን፤ መንፈስ በስጋ ላይ እንዲያሸንፍ ማገዝ ነው፤ ይህ ትግል እግዚአብሔርን በማወቅ ወደ እርሱ በመጠጋት መፍትሄ ያገኛል።

ከውስጥ የሚመነጨው ግጭት መገለጫውም ሆነ መነሻው ከፉ አሳብ ነው «ከፉ አሳብ





ኃጢአትን የምትወልድ እናት ናት፣ ከፉ ሀሳብ የኃጢአት ቅልጥም ናት፤ ከፉ አሳብ መርዛሙ የኃጢአት መጠጥ የሚጠመቅበት ብቅል ናት፣ ከፉ አሳብ ሰይጣን ሰብቆ ለሚያወጣው ለፈተና ፍም እሳቱ የሚነድባት ጨርቅ ናት፣ በመናጫ ወተት ወደ ቅቤ እንደሚለወጥ እንዲሁ ረቂቅ አሳብ ብቻ ወደ ሥራና ወደ ድርጊት ይለወጣል። (**ኦሌ ኦሪክሰን <u>የአንድ አራሽ ንግግር</u>** ገፅ 5)

አማኞች አሳባችን ለእግዚአብሔር ያልተገለጠ አይምሰለን፤ እርሱ አልብ ውስጥ አዝልቆ የሚያሳይ ከቶ የማይዘጋበት መስኮት አለው፤ እኛ ንቦችን በቀፎ ቀዳዳ እንደምንመለከታቸው እንዲሁም የጌታ ዐይን በመንገዳችን ሁሉ ያየናል...ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ቅድሚያ በመስጠት በእርሱ ለመሞላት እየደከምን ከፉውን አሳብ ግን ከፉ መሆናቸውን፣ በቃሉ በተቀደሰው ህሊና እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እገዛ እያጠለልን ማራቅ እግዚአብሔርን የማወቃችን ማረጋገጫ ነው፤ «...ሌቦች በመስኮታችን አሹልከው በማየታቸው ከቶሙ ምንም ጉዳት አይደርስብንም፤ እያወቅናቸው ግን በራችንን ከፍተን ራት እንብላ ብለን ብንጠቃ ተጠያቂው ራሳችን ነን... ወፎች በላያችን ላይ እንዳይበሩ መከልከል አንችልም ግን በጭንቅላታችን ላይ ጎጆዋቸውን እንዳያበጁ ልንከለክላቸው እንችላለን።

እንግዲያስ እግዚአብሔርን ማወቅ ለከንቱ ለከፉ አሳብ በሩን ሳንከፍት እርኩስ አሳብ ከልባችን ሲመነጭ እንዲገዛን ሳናደርገው እንድንኖር እግዚአብሔር ይፈልጋል፤ የእግዚብሔር የሆነው አሳብ እሱንም የመውደድ መገለጫ አለው።

የአንድ አራሽ ንግግር አዘጋጅ የጌታ የሆነውን አሳብ ዶሮ ከንፎቿን በጫጩቶችዋ ላይ ዘርግታ እንደምታቅፋቸውና እንደምታሞቃቸው እኛም በጎ የሆነውን ሁሉ እንታቀፈው ይለናል (**<u>የአንድ አራሽ ንግግር</u>** ገፅ 30)።

ሐዋሪያው ጳውሎስ «እግዚአብሔርን ይበልጥ እንድታውቁት እፀልያለሁ» የማለቱም መሰረታዊ ቁም ነገር የሕይወት መገለጫ በዚህ ብቻ ስለሚፀና ነው፤ እንባብያን ሆይ! ልሁል እግዚአብሔርን በቃሉ እንረዳዋለን ብለን የምንቆምበትን ሕይወት አይደለም እግዚአብሔር የሰጠን ይልቅስ እግዚአብሔር ራሱን እንዲገልጥልን፡- በማስተዋል እንድናመልከው በትህትናና በፍቅር በመፀለይ የምንቀርበው አዳኝ እንዳለን ልብ ማለት ተገቢ ነው።

***

አንባቢያን ሆይ እርሳስ የሚሰራው ሰውዬ የሰራቸውን በርካታ እርሳሶች ወደ ገበያ ከማውጣቱ በፊት ሁሉንም በአንድ ላይ ሰብስቦ ከዚህ በኋላ ሊኖሩት ስለሚገባቸው አኗኗር መመሪያን

ይሰጣቸዋል። መመሪያዎቹ አምስት ናቸው።

1. ታላላቅ ስራዎችን እንድትሰሩ በሰዎች እጅ ጣቶች መሀከል ለመቀመጥ ሁል ጊዜ ፈቃደኞች ሁኑ፣
2. ከስራ በኋላ በየጊዜው በስለት ስትቀረፁ ትሰቃያላችሁ፣ ነገር ግን የምትቀረፁት የተሻለ እርሳስ እንዲወጣችሁ ስለሆነ እያመማችሁ ታገሱ፣
3. ምንም ዓይነት ስህተት ብትሰሩ ራሳችሁ ማስተካከልና ማረም ትችላላችሁ፣
4. የናንተ ጠቃሚውና ዋናው ሕልውናችሁ ወይም ማንነታችሁ ያለው ሁሌም በውስጣችሁ ስለሆነ ይህን አትዘንጉ፣
5. ከምትፅፉበት ቦታ ሁሉ ምልክታችሁን እያስቀመጣችሁ ማለፍን አትርሱ ምንም ዐይነት ችግር ቢገጥማችሁም መፃፋችሁን አታቋርጡ ይላቸዋል (**ፅዮን <u>ዘመን ተሻጋሪ ተረቶች</u>** ገፅ 16-18) እነርሱም ይህን ተገንዝበው ቃል ገብተውም ወደ ሳጥኖቻቸው ይገባሉ ይታሸጋሉ፤ ይሸጣሉም።

***

እኛስ ለምን እራሳችንን በእርሳሶቹ ቦታ አናደርግም ከዚያም በቀሪ ዕድሜያችን አምስቱን ትዕዛዛት አናከብርም ለምንስ በዚያ ውስጥ እግዚአብሔርን የማወቅን የፀሎት መልስ አናገኝም

- ✓ 1ኛ ተገቢውን ሥራ ትሰሩ ዘንድ እራሳችሁን በእግዚአብሔር እጅ ላይ አስቀምጡ እናም ሌሎች የእናንተን ስጦታና ችሎታ ይጠቀሙ፣
- ✓ 2ኛ በየጊዜው ብዙ ስቃይና ፈተና መጋፈጥ አይቀሬ መሆኑን በማመን ለመከራችሁ መንስኤ የሆኑትን እነርሱን ከመጥላት ይልቅ እንውደዳቸው፣
- ✓ 3ኛ ስህተት ብትሰሩ በሀጢአት ብትሸነፉ ሁልጊዜም ማስተካከል ትችላላችሁ ስህተትን ቶሎ ማወቅ ደግሞ ከድጋሚ ስህተት ይጠብቃል፣
- ✓ 4ኛ ከውጭ ገፅታችን በበለጠ ውስጣችን ሁልጊዜ ጠቃሚና ተፈላጊ መሆኑን በማወቅ እናቆሽሸው፤ እናበላሸው፤ እናበስብሰው፣
- ✓ 5ኛ በየትኛውም ቦታ ብትገኙ ልክ ኢየሱስ «በሰማይ ያለውን ያንተን ፈቃድ አሁን በምድር





እየፈፀምኩ ነው» በማለት አብን እንደ አመሰገነ እናንተ በቀኑ መጨረሻ ብትጠሩ እንኳ ብዙ አስታዋሾችን እና አልቃሾችን፣ ተደሳቾችንና አመስጋኞችን አብዙ።

ሐዋሪው ጳውሎስ «እግዚአብሔርን አብልጠን እንድናውቅ የመከረን የፀለየልንም ለዚህ አይነት ውጤት ነው፤ አሜን።

# እግዚአብሔርን እንድታውቁት . . . እፀልያለሁ

## ኤፌ.1:17

## ክፍል 3

ክርስትና በኢትዮጵያ መስፋፋቱን ከሚያመላክቱት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ:- በርካታ ስያሜዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሄደባቸውና ከኖረባቸው ጋር የተያያዙ ሆነው መሰየማቸው ነው። ሌላኛው በጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጉዞ የተደረሱ ስፍራዎችም በኢትዮጵያ ተጠቃሽ ተሰያሚ ሆነው ተገኝተዋል። በብሉይ ኪዳን የተጠቀሱም እንደ ደብረሲና፣ ደብረታቦር የመሰሉ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን የተዝወተሩ እንደ ደብረዘይት፣ ናዝሬት ኤፌሶን፣ አንፆኪያ እና የመሳሰሉ መጠሪያዎች ዛሬ ድረስ በሀገራችን አገልግሎት ይሰጣሉ።

እኔ በግሌ ከእነዚህ ውስጥ ለደብረዘይት የተለየ ትዝታ አለኝ፤ አባቴ እናቴን ያገኘው ከዚያ ከዝቋላ ነው፤ አከስቴ የአባቴ ታናሽ ኑሮዋን ያደረገችው ከዚያው ከዮሴፍ ወፍጮ ጀርባ ነው፤ ሶስተኛ ክፍል ሳለሁ አባቴ የሰራውን ቤት ሊያሳየኝ የወሰደኝም እዚያ ነው፤ ስሜን የሰጡኝ የአክስቴን ባለቤት ሀይሉ ወልደ ማሪያምንም ያገኘዋቸው በዚያ ነው፤ እናም እሳቸውንም ደብረዘይትንም እወዳለሁ፤ለነገሩ ለአባቴም የምትመቸው ረዳት ያዘጋጁለት እሳቸው አይደሉ።

እንዲህም ቢሆን ስለ ደብረ ዘይት በምሰማው ትረካ ውስጥ «ቆሪጥ» የሚባል ተጠሪ በድግግም ወደ ጆሮዬ መጣ፤ ስለ እርሱ በሰማሁ ቁጥር ፍቅርን ሳይሆን ፍርሀትን በውስጤ ጨመርኩ።





***

*«...ትዋሪነቱ ቢሾፍቱ አካባቢ ነው፤ ጃንሆይ ቅንድቡ የተጋጠመ ሰው ይገብሩለት ነበር፤ ጃንሆይ እኩለ ለሊት ላይ ሲመጡ ከሀይቁ መሀል የወርቅ ዙፋን ይወጣል ከዚያ እሳቸው ዙፋኑ ላይ ሲቀመጡ ዙፋኑ ይዞአቸው ወደ ውሀው ውስጥ ይሰጥማል፤ ከዚያም ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ይመለሳሉ...»* ይህ ቆሪጥ ከሚያደርገው አንዱ ነው:: (**<u>የቢሾፍቱ ቆሪጦች</u>** ገፅ 30)

*«...ቆሪጥ፤- ቆሪጥ የሚለውን ስም ያገኘው እግሩ ቆራጣ በመሆኑ ነው፤ እሱ ባለበት ትይዩ የሚኖሩት የጋራበሩ ሰዎች ደግሞ ቆሪጥ ከዝቋላ የተባረረ ጋኔን መሆኑን ያምናሉ፣ ቆሪጥ እንደ ሳጥናኤል ነው፤ ሳጥናኤል የሚተካከለኝ የለም ብሎ መፈንቅለ አምላክ የማድረግ ፍላጎቱ ሲደረስበት ከብሩን ተነጥቆ እንዲዋረድ ተደረገ፤ በቆሪጥ ላይመም አቦዬ ለጭንቅላቱ የወረወሩት መብረቅ አናቱን ትቶ የቀኝ እግሩን አግኝቶ ጎመደለት...* (**<u>ስፍቱ</u>** ቅፅ5 ገፅ 197 በእንዳለጌታ)

*«...እነርሱ ቆሪጥን በነፃነት ማነጋገር እንደሚቻል በእርግጠኝነት ይናገራሉ፣ ውይይቱ ግን በአካል በመተያየት ሳይሆን በድምፅ ማነጋገር ይቻላል ይህን ቆሪጥ ለማነጋገር ከሱዳን፣ ከጋና እና ከአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት እንዲሁም ከአዲስ አበባ እና ከመላው የኢትዮጵያ ክልሎች ወደ እርሱ ይመጣሉ... ለነገሩ በቆሪጥ ዘንድ አማኝነትም ደረጃ አለው በእርሱ ዘንድ አዲስ አማኝ የሚኮነው ጋራበሩ ላይ ነው፣ በዚያ እሱን የፈለገ ተገናኝቶት ከእርሱ ጋር ውል ይፈፅማል፤ ከዚህ ውል በኋላ ወደዚያ ቦታ አይመለስም በምትኩ በተደጋጋሚ የሚመጣው ሆራ ነው፤ ሆራ የነባር አማኞች የምሰጋና ማቅረቢያ ስፍራ ነው...*

*«...ታዲያ ይህን ለማስፈፀም ድልድይ በመዘርጋት አገናኝ የሆነች አማላጅ እና ካህን አለች፤ መኖሪያዋም ጋራበሩ ላይ ነው፤ ሴቲቱ ውሉ በአግባቡ መፈፀሙን ታረጋግጣለች የቆሪጥ ስብዕና በእርሷ ውስጥ እያደረ ለሚለማመኑት ተገቢውን ይነግራቸዋል ከተከታዮቹ የሚጠበቀው «የቢሾፍቱ ንጉሰን በሙሉ ልብ ማመን፣ ደግሞም እግዚአብሔርን መካዳት» ነው «...በአመት አንድ ቀን ቆሪጥ ይሰደባል በተቀሩት 364 ቀናት ይወደሳል፤ መጋቢት አምስት የአቦ ዕለት የጋራበሩ ሰዎች የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን የንግስ በዓል ለማክበር ወደ ዙቁዋላ ወርደው ቆሪጥን «ቆሪጥ ቆረጥራጤ አቦ ከዝቁዋላ ሲያሳድዱት የአያቶቻችን ጆሮ እስኪበጠስ ድረስ ነበር ኡኡታዋን ያቀለጠችው» እያሉ ያሸማጥጡታል፤ የዚያን ቀን ቆሪጥ በአደባባይ ይዘለፋል፤ በነጋታው መጋቢት ስድስት ቀን ግን ሁኔታው ሁሉ ተቀይሮ ቆሪጥን ማምለክ እንደ ከትናንት ወዲያ ንጉስነቱ ሳይቀር መወደሱ ዘላቂ ይሆናል* (**<u>ስፍቱ</u>** ቅፅ5 ገፅ 20)

*«...የቢሾፍቱ ንጉስ ሆይ ከአፍህ ስህተት አይገባም፣ ከንግግርህ ኩራት አይጠፋም ጋራበሩ*

*ባንተ ጥፍር ስር መሆንዋን እናምናለን፤ ያሻህን ትፈፅም ዘንድ ፃድቁ አቦ ፈቅደዋልና ሁሉም እንደ ስሜትህ ይሁን ኑሮዋችን ከፍቶ ማርን በኮሶ መዋጥ ቢሆንብንም አናማርርም...»* እያሉ ይመርቁታል ያዜሙለታል (ክፍት ቅፅ5 ገፅ 20)

*ቆሪጥን ለመከተል የወሰኑ ሰዎች «ይኸ ነው የሚባል ብሔር የላቸውም፤ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ትግሬ ደቡብ ሕዝብ ተብሎ የሚጠራ በዚያ የለም ፈፅሞ ተቀላቅለዋልና።*

*ታዲያ የቆሪጥ አገልጋይ «ቀይዋ ሸረሪት» ከሀምሳ ዓመት በፊት ነበር የሞተችው፤ አሁን ያለችው ቀይዋ ሸረሪት የሸረሪት ዘር ያለባት ነች፤ ቆሪጥ ሰርቋት ሀይቁ ውስጥ ካሳደጋት በኋላ አምጥቶ በሕዝቡ መካከል አኑሯታል፤ ይህች ሴት ወደ ሸረሪትነት የምትለወጥባቸው ጊዜያት አሉ፤ የመለወጧ ምክንያትም በየቤቱ ያሉ ሰዎች በቆሪጥ ላይ ክፉ ተናግረው ከሆነ ያ የሰሙትን ለእሷ ለመንገር እንዲመች ዋንኛው ቆሪጥ ሆን ብሎ ያደረገው አሰራር ነው፤ ይህ የቢሾፍቱ ሕዝብ ስለሚያውቅ ሸረሪቶችን አይገድሉም በቆሪጥ ላይም አጉል ነገር አይናገርም በስህተት ቢያወሩ «መቼም ስለ ጥቁር ውሻ ነው የሰማሁት» በማለት ሌላ ጣጣ እንዳይመጣ ከፉውን ወሬ ይቀይሩታል።*

ቆሪጥ እና ደብረ ዘይት በዚህ ጉዳይ ስለተያያዙ ደብረዘይትንና ሀይቆቹን ፈራኋቸው፤ ወደ አከስቴ ዘንድ ሔጄም የማያቸውን ነገሮች ሁሉ በጥንቃቄ ማጤንም ስራዬ ሆነ፤ ይልቁኑ ስም ያወጡልኝ አባባ ሀይሉ ስለ እሱ እንዲነሳ ፈፅመው ስለማይፈልጉ አንድ «ነገር ቢኖር ነው» አልኩኝ።

«የቢሾፍቱ ቆሪጦች» ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ቆሪጥን በአግባቡ ለማወቅ ወስኖ ዜና ለማጠናከር ከአዲስ አበባ ስለሄደው አንጋፋ ጋዜጠኛ ገጠመኝ ብዙ መረጃን በመፅሐፉ ውስጥ አኑሯል እሱን በተመለከተ እንዳለ ጌታ ከበደ ሲፅፍም *«አራት መቶ አመታት ያህል ቆሪጥ ሀይቃቸው ውስጥ ሲሰነባብት ከማጉረምረም ውጭ ሌላ ተስፋ እንዳልነበራቸው ልባቸውንም የቢሾፍቱ ሰዎች ለሁለት ከፍለው አቦዬንና ቆሪጥን እንዲያስተዳድሩበት በመንገር ሁሉም ግን የነፃነታችን ቀን እስኪትደርስ ያመለክነው መስለን እንሰግድለታለን ፃድቁ አቦ የልባችንን ያውቁታልና አያሰጋንም በዚያች የተሰፋ ዕለት አቦ እንደ ጀመሩ ሊያጠናቅቁት ሲመጡ የልባችንን ሁሉ እንተነፍሳለን ባዮች»* መሆናቸውን ጋዜጠኛው ፅፏል (ክፍት ቅፅ 5 ገፅ 197)

*ይህ ብቻ አይደለም የሚነገረውን ሁሉ «ተረት ነው» እያለ ቆይቶ መጨረሻ ላይ የሚያነጋግራቸው ሴቱዬ «ለንግስቲቱ ልንገርልህ እና አግኘው በደስታ ያስተናግድሀል ይህን ሁሉ ከምታናዝዘኝ ለምን ከራሱ ጋር አላገናኝህም» ይሉታል በዚህ ሰዓት ጋዜጠኛው ጦር ልቡ ላይ የተሰካ ያህል ደንግጦ፤ ያቃስታል፤ ፈጥኖም «ደብረ ዘይት ለመምጣት ስለማይመቸኝ ይቅርብኝ ብዙ ጊዜ ካገር ሀገር ስለምዞር አንድ ቦታ አልቀመጥም» ይላቸዋል እሳቸው ግን «ታዲያ ይህ ለቆሪጥ ምን*





*ችግር አለው እዚህ መምጣት ታልተመቸህ እሱ ታለህበት ሊመጣ ይችላል ለሱ የሚሳነው ምን አለ ብለህ? በቅሎ አይፈልግ አቶቢስ? እንደ ንስር ተንፋስ ጋር ነው መንገዱ፣ እኛ ሁለቴ ስንተነፍስ እሱ ተዚህ ተነስቶ አሜሪካ ይገባል ምን ይሳነዋል ብለህ ተፈቀድክ ለንግስቲቱ ልነግርልህ እችላለሁ ታለህበት ከተፍ ይላል...» ይሉታል በዚህ ግዜ «የለም የለም...ስራ ስለሚበዛብኝ ልገናኘው አልፈልግም ጠዋት የወጣሁ እስከማታ በስራ እንደተጠመድሁ ነው» የማሳልፈው ብሎ ሊገላገል ሲል ሴትዬዋ «ንጉሱ እኮ ብርሀን አይወድም ሌሊት መዘዋወር ነው የሚመርጠው ውድቅት ላይ ስራህን ስታበቃ ታለህበት ይምጣልህ» አሉት እሱ ግን «ምንም አያስፈልገኝም አሁን የነገሩኝ ይበቃኛል» ካላቸው በኋላ በመጨረሻም «አደራ ቢያገኙት እንኩዋ ስለ እኔ ምንም ነገር አያንሱለት ወደዚህም የመጣሁት ለሌላ ስራ ነው» ብሎ ከተማውንና ቢሾፍቱን ለቆ ወጣ፤ ደብረዘይትን።* (ተስፋዬ ገብረአብ የቢሾፍቱ ቆሪጦች ገፅ 1-54)

***

እያንዳንዳችሁ «ቆሪጥን» ለማወቅ ከፍተኛ ጥናት እያደረጋችሁ ባለበት ሰዓት ላገናኛችሁ የሚላችሁ፣ ላስተዋውቃችሁ፣ ፊት ለፊትም ተነጋገሩ ብትባሉ የሚኖራችሁ ምላሽ ምንድነው? አሁን በልባችሁ የሰጣችሁት ምላሽ እሱ አቅማችሁን፣ እምነታችሁንና ዕውቀታችሁን ያጣቁማል፤ ጋዜጠኛው ደብረዘይትን ለቅቆ ቆሪጥ ይኖርበታል ከተባለበት ስፍራ ሸሸ፤ ከእናንተ እያንዳንዱ እዚያው ሄጄ እተዋወቀዋለሁ፣ እፋለመዋለሁ፤ እርፎ መቀመጥ ሳለ የምን መነካካት፣ ደብረዘይት ያሉ ክርስቲያኖች ምን ሰርተው ሊኖሩ፣ የኢየሱስ ስም በእጄ እያለ ምን አሮጠኝ ከዚሁ አነጣጥሬ እገለብጠዋለሁ፣ በሕብረት ሆነን እሁኑኑ እንገስፀው፣ ፍርሀት የፈጠረው ተረት እንጂ የዕውነት ቅንጣት በውስጡ የለም፣ የመሳሰሉ ምላሾችን እንደምትሰጡ እገምታለሁ፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ ግን፡-

> *«...ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል? ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ ሁሉን ነገር ከእርሱ ጋር እንደምን በልግስና አይሰጠን እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከሳቸው ማን ነው? የሚያፀድቅ እግዚአብሔር ነው፣ ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው? የሞተው እንዲሁም ከሞት የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል፤ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው?... ምንም አይለየንም በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፤ ሞትም ይሁን ሕይወት መላዕክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው ወይም ማንኛውም ኃይል ከፍታም ይሁን ጥልቀት ወይም የትኛውም ፍጥረት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም...»* ሮሜ 8፡31-39)

ይህ የሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት ለሮሜ ሰዎች ብቻ ተልዕኮ አልቆመም ዛሬም ሳይሸራረፍ እውነቱ ፅኑ ነው፤ ክርስቲያን አማኝ በቆሪጥ፣ በዲያብሎስና በአጋንንት ሁሉ ላይ መንፈሳዊ መሰል ተግዳሮቶች ሁሉ ላይ ቆም ብሎ ራሱን ማየት ራሱን ማወቅ አለበት፤ ትክክለኛው ራስን ማወቅ ደግሞ እግዚአብሔርን በማወቅ ይለካል፤ይረጋገጣል። በመሰረቱ ሁለት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ግንዛቤዎች ወይም እምነቶች በክርስቲያኖች ዘንድ ይታያሉ የሁለቱም መንደርደሪያ ልውል እግዚአብሔርን፣ ዕቅዱንና የሰራውንም ስራ ጭምር ካለማወቅ የመጣ ጣጣ ነው።

አንደኛው፡- ዲያብሎስም ሆነ አጋንንት ምንም ዐይነት ጉዳት እንደማያደርሱ ማወጅና እነርሱ እንደሌሉ አድርጎ ማሳየት፤ ማስተማር እንዲሁም በዚሁ ሀሳብ ህይወትን መምራት ሲሆን፤

ሁለተኛው፡- ዲያብሎስና አጋንንት የሁል ጊዜ ስራቸው በየጊዜው ከሚገጥሙን ማንኛውም ችግሮች ጀርባ እነርሱ መሸገው ኑሮአችንን ምስቅልቅሉን እንደሚያወጡት አምኖ መኖር ነው(የእረኛው ምርኩዝ ቅፅ 1 ገፅ 296) እነዚህ ሁለቱም ሚዛን የለሾች በመሆን ከእግዚአብሔርና ከተገለጠው ከሕያው ቃሉ ጋር ይቃረናሉ።

በ«ለእውነት እንቁም» 62 መጣጥፎች ውስጥ ተ.ቁ 49 እና 50 «ትችት በመለኮታዊ ራዕይ ሲያል ሲገለፅ» ላይ እና «ቀልባችን አጋንንት ላይ ያልሰፈረበት ምክንያት» በማለት ማሳሰቢያዬን አኑሬያለሁ።

**«በመለኮታዊ ራዕይ ሲያል ሲገለጥ»** መፅሐፍ ውስጥ፤ አንዲት ሴት አየሁት ያለችውን በመፃፍ ያቀባበለችበት ስራ በዚያ ይገኛል አንድ እሁድ ሰባኪው እሱን ብቻ ሰብኮ ወረደ ሕዝቡም «መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልን?» የሚለውን ለአፍታም ሰፍራ ሳይሰጥ አብሮት አድንቆ ጨረሰ፤ በዚህን ግዜ ነበር እኔ መፅሐፉን ገዝቼ ለማንበብ የወሰንኩት «ሴቲቱን ሜሪ ባክስተርን ኢየሱስ ነፍሷን ከስጋዋ ለ40 ቀናት እያወጣ ገሀነም በመውሰድ የሲኦልን፣ የአጋንንትንና የዲያብሎስን ሚስጢር ይገልጥላታል፤ ያንን የገለጠላትን እንድትፅፈው ያዛታል። (ገፅ 1) ከፃፈችው ውስጥ፡-

- የሲኦል እሳት ኃጢአተኞችን ሲያቃጥል ዲያብሎስንና አጋንንቱን አይነካም (ገፅ 81)
- ሴቲቱ ድንገት ከኢየሱስ በመሰወር በዲያብሎስ ቁጥጥር ስር ውላ በሰንሰለት በመታሰር በእሳት ትቃጠላለች አፅሟም በትል ይሞላል (67፤102)
- ከዚያም የዲያብሎስ ጭፍሮች ከእሳት ወደ ውሃ ከውሃ ወደ ሙቀት ያሸጋግሯታል (68)
- ኢየሱስ ከሴጣን ካወጣት በኋላ እምነት ያጣ ደንነቱን እንደሚያጣ ያስተምራታል





(17፤32፤33)

- ሴጣን ወደፊት የሚታሰረውም የቅዱሳን ፀሎት የጠነከረ ሲሆን ብቻ መሆኑን ያብራራል (ገፅ 92)
- ለሴቲቱ ኢየሱስ የሚመለስበትን የመጨረሻ ጊዜም ይገልፅላታል (82፤91)
- በቅድመ ዝግጅትም ኢየሱስ ሴጣንን ለመቋቋም በቅርቡ «ቅዱስ የጦር ሀይል» የሚባል ከአገልጋዮች የተውጣጣ፣ ከሰራተኞች፣ ከእመቤቶች፣ ከወንደላጤዎች፣ ከሴት እመቤቶች እና ከትምህርት ቤት ሕፃናት ተውጣጥቶ እንደሚገነባ ይተነብያል (ገፅ 81) ይህን የመሰሉ ብዙ ብዙ ፃፈች።

***

በወቅቱ እግዚአብሔርንና የዘላለም ዕቅዱን በማወቅ ያልፀኑ በዚህ ትምህርት ነሁልለው ነበር፤ ይህ ግን ከእ.ኤ.አ.1996ወዲህ የመጣ ነበር እሱን ቀድሞ እ.ኢ.አ.በ1960ዎቹ የነበረው የወንጌል ስርጭት ስልትም የክርስቶስን ፍቅር በመግለጥ ሳይሆን በገሀነም ማስፈራሪያነት ሰዎችን በማስደንገጥ እጅ እንዲሰጡ የሚያመቻች ነበረ በዚያን ግዜ በሀገራችን በስፋት የተበተነው ትራክትም **«ሕርባ ሰምንት ሰኦት በገሀነም»** በማለት ብርሀኑ ከበደ የተረጎመው የጀርጅ ሌየክስ ራዕይ ሌላው ስራ ነበር፤ ዕሉፉ እንደ ጉድ ተበትኗል፤ ተነቧልም፤ እ.ኢ.አ.ከ1970 በኋላ የመጣው ዲያብሎሳዊ እንቅስቃሴ እኔን በብርቱ ታግሎኝ አልፏል፤ በትምህርት ገበታ ላይ ራሳቸውን በመጠበቅ ተውበው የሚታዩትን ሴቶች ባየሁ ቁጥር «በኢየሱስ ስም» በማለት ለመገሰፅ ሞክሬያለሁ፤ መከላከሌ «ሴቲቱ ከጥልቁ ከወጡት እንዷ ናት» በማለት ነበር፤ ለዚህ ደግሞ በጊዜው በናይጀሪያ ሌጎስ ተገለፀልኝ የሚለው «የአማኑኤል አሞፅ» ሰፊ ምስክርነት ሰፊ ሽፋን አግኝቷል፤ በዚህም ጊዜ ነበር በወንጌላውያኑ ዘንድ «ዲያብሎስን ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል» የተባለ ያህል ስለ እርሱ እየተነገረ ዲያብሎስ ተፈራ፣ ተከበረም፤ ይልቁኑ በእነዚያው ዓመታት በጌታ ያሳድገኝ የነበረው ወንድም ከፍተኛውን ጦርነት ከዲያብሎስ ጋር በማድረግ ላይ እንደነበር ቀንና ሌሊት ይነግረኝ ጀመር፤ በተለይም አብረን ተኝተን በንስር እንቁላል መልክ ወደ እርሱ ተጠግቶ የመጣው ዕንቁላል ተፈርክሶ አስፈሪውን ሴጣን በማውጣት ወደ እርሱ መራመድ በጀመረ ጊዜ የዚያ ወንድም ምላሽ የደረጀ ቡጢ ከመቀደሙ በፉት ይሰጠዋል፤ ታዲያ በዚያው ቅፅበት ግድግዳውን አከሮ በመምታቱ በእጁ ላይ ጉዳት በተደጋጋሚ ይገጥመው እንደነበር አስታውሳለሁ።

ይህን ሚዛን የሳተ እምነትን ለመቋቋም ነበር ከገፅ 336-343 «ቀልባችን አጋንንት ላይ

ያልሰፈረበት ምክንያት» በማለት ማስታወሻ በመፅሐፉ ላይ ያቀበልኩት በዚህም የዲያብሎስ እና የአጋንንት ህልውና በተረት ተረት የሚፈረጅ ወይም እንደሌለ ያህል በመቁጠር የሚዘናጉበት ሳይሆን ያለ እና ያሉ መሆናቸውን በወጉ መረዳት እንዲሁም በትይዩ በእንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ውስጥ አዋኪው የሴጣንና የአጋንንት ስራ ነው ብሎ በፅንፈኝነት በማመን ይህንንም ከልክ በላይ ማራገብ ስህተት መሆኑን ማወቅ እንዲሁም ትክክለኛው ግንዛቤ እግዚአብሔርን ከማወቅ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ልብ ማለት ተገቢ ነው።

***

በዚህ ዝግጅት ሁለት መሰረታዊ ጥቅሶች ሁሉን ሆነው ሊቆሙልን ይችላሉ፡- «...ሙታን ሳላችሁ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኃጢአታችንንም ሁሉ ይቅር አለን፤ ሲቃወመንና ሲፃረረን የነበረውን የዕዳ ፅሕፈት ከነሕግጋቱ በመደምሰስ በመስቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው የአለቆችንና የባለ ስልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነስቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ...» (ቆላ 2፡13-15 አመት) ቀዳሚው ጥቅስ ነው።

ሌላኛው «...እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፣ ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል...» (ያዕ. 4፡7 አመት) ሁለተኛው ጥቅስ ነው።

ሁለቱም ክፍሎች አማኞች እግዚአብሔርን በማወቅ አቅማቸው፡- ዲያብሎስንና አጋንንትን እንዴት በመረዳትና በመገንዘብ የየገዛ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በመጠበቅ የሚዘልቁበት የፍሬያማነት መነሻነትን ሁሉ ያበስራሉ።

ተረቶች ቢሆኑ፣ እውነተኛ ታሪኮች ቢሆኑ፡- ስለ ቆሪጥም ዘከርን ስለምንም ትውፊት ብንናገር ሁሉም የሚጠሩት እና የሚለዩት በእግዚአብሔር መለኪያ ነው፤

ቆላስያስ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ስራው ያመጣውን ወደር የለሽ ድል ያበስራል፤ ይህን ማወቅ ነው ዳግም ለተትረፈረፈ ሕይወት መነሻም መደምደምያም የሚሆነው።

*«...የአለቆችንና የባለ ስልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነስቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ...»* ቆላ 2፡15

***





ሐዋሪያው ጳውሎስ ዲያብሎስን ጨምሮ በክፋት ዓለም ውስጥ ያሉትን መናፍስት አለቆችና ስልጣናትን ድል በመንሳት ኃይላቸው እንዴት እንደተገፈፈ ለማብሰር የሮምን ጦር ሰራዊት ወታደራዊ ልምድን ነው በዋቢነት ያመጣው።

የሮም ወታደሮች አንድን ጦርነት በድል ሲወጡ መሪው ጄነራላቸው ድል የነሱትን የጦር መሪ ጄነራል ይዘው ማዕረጉን ይገፉታል፤ ከዚያም ከእርሱ ጋር የተማረኩትንም ወታደሮቹን በሰንሰለት አስረው እርሱ ተቀምጦ ከሚሄድበት ሰረገላ ኋላ ኋላ በእግር እንዲከተሉት ያደርጋል።

ይህ ምሳሌ የተሸነፈው ጠላት (ዲያብሎስ፣ አለቆችና ስልጣናቱ) የሽንፈት ሃፍረታቸውን ተከናንበው በሕዝቡ ፊት መሄድ፣ የክርስቶስን ድል አድራጊነትንም በአግባቡ በደንብ በማሸነፍ መርታቱ ሁልጊዜ በሁለት ሀይላት መካከል በሚደረግ ብርቱ ፍልሚያ ይገለፃል፤ በማሸነፍ ምርኮ መሰብሰብና ተማርኬያለሁ በማለት አቅመ ቢስ ነኝ ብሎ እጅ መስጠትን ያረጋግጣል፤ ይህም የሁልጊዜው የሮም የጦርነት ታሪክ ነው፤ በ1945 በጃፓኖች እና በአሜሪካኖች መካከል የተደረገ የመራራ ጦርነት ፍፃሜ ያገኘው በአሜሪካንና በአጋሮቿ የበላይነት ነበር የጃፓን ጄኔራል ለአሜሪካዊው ጦር ጄኔራል ለማክአርተር እጁን መስጠት ነበረበት።

ይህም በቶኪዮ የባህር ዳርቻ ላይ ተከናወነ፤ በወቅቱ የተሸነፈው የጃፓን ጦር አዛዥ ጄኔራል ሙሉ ማዕረጉን እንዳደረገ ከጦር መርከቡ ላይ ወረደ፤ ከእርሱም ጋር ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው ወታደራዊና ሲቪል ባለስልጣኖች ተከተሉት።

የጃፓን ጄኔራል የጃፓንን የጦር ሀይሉን የሚወክል ሲሆን ጄኔራል ማክአርተር ደግሞ የአሜሪካንን ጦር ኃይል ይወክል ነበር፤ ሁለቱም አንድ ስፍራ ላይ ፊት ለፊት ተፋጠው ቆሙ፤ ከዚያም ጄኔራል ማክአርተር የጃፓኑ ጄኔራል የለበሰውን የማዕረግ ልብስና ያንጠለጠላቸውን የጦር ሜዳ ሜዳሊያዎች፣ ጥብጣቦችንና ወታደራዊ ጌጦቹን ሁሉ ከላዩ ላይ በመቀነስ እየቆራረጠ ተራ በተራ ወረወራቸው፤ ሁሉን ካጠናቀቀ በኋላ ምንም አይነት ስልጣን የሌለው ተራ ሰው መሆኑን" ምንም ሀይል የሌለው መሆኑን በመግለፅ አንበረከከው፤ አዋረደው።

የዚህ ጄኔራል እጅ መስጠትንና የማዕረጉ መገፈፍ እንዲሁም መንበርከክ ውክልና አለው፤ ግላጭነቱ የተሸነፈው፤ በአጠቃላይ የጃፓን ጦር ኃይል መሆኑን ለሁሉ ማብሰር ነው፤ የጃፓን የአየር፣ የምድርና የባህር ኃይል ሁሉ እጅ መስጠቱንና መሸነፉን ያረጋግጣል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በመስቀል ላይ በመፈፀሙ ዲያብሎስን፣ አለቆችን፣ ስልጣናቱንና ኃይላቱን ከስልጣናቸው ጋር በመግፈፍ ድል አድርጓቸዋል፤ ይህንንም በማስተያየት

ጳውሎስ የድሉን ልቀት ያፀናል፤ የጄኔራሉ ድል የመላው አሜሪካውያንና የሕብረቱ ድል እንደሆነ ሁሉ የኢየሱስ ድልም የእርሱ ብቻ አይደለም እርሱን የሚወድና የሚያገለግሉት የሁሉ ልጆቹ ድል ነው።

እኛ ቆሪጥን ለማነጋገር ፈራ ተባ ባለ ሕይወት እንድንኖር ወይም ማምሻም ዕድሜ ነው ብለን ከደብረዘይት ልንኮበልል ሳይሆን የተጠራነው፤ ኢየሱስ ስለ እኛ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ በመስቀል ላይ መሞቱ ለእኛ ድል አድራጊነት እና የነፃነት ሕይወት ቁልፍ ድርጊት ነው።

ዲያብሎስ ከክርስቶስ ስራ የተነሳ በአማኞች ላይ ምንም ስልጣን የለውም፤ አማኙ በዳግም ልደት ሕይወቱ አንድ ወር፣ አመት፣ አስር፣ ሀያ፣ አምሳ፣ ስልሳ አመት የኖረ፤ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበረታም ሆነ አልሆነ ዳግም ከመወለዱ የተነሳ ሴጣን እንደ ልቡ ሊፈነጭበት አይችልም።

ጃፓኖች አንድ የአሜሪካ ተራ ሀምሳ አለቃ፤ በጦርነቱ ውስጥ ማርከው ዘብጥያ ጥለው ያሰቃዩት ነበር፤ ከአመት በኋላ ግን አሜሪካ በማሸነፉ ታሪክ ተገለበጠ፤ ድሉን የሀምሳ አለቃውና ታሳሪዎቹ እንደሰሙ ፈጥነው ነፃነታቸውን አወጁ። በተራቸው የጃፓኑን የእስር ቤት ከፍተኛ መኮንን ተቆጣጠሩ።

ሐዋሪያው ያዕቆብ እንዲህ ስለተዋረደው ዲያብሎስና አጋንንት ያላቸው ሀይልና ስልጣን በኢየሱስ የማሸነፍ ብቃት መተካቱን እያወቀ በተያያዥ የተሸነፉትንና የተዋረዱትን በጎሪጥ መመልከት ተገቢመሆኑን አስተማረ።

ይህንንም «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል» (ያዕ 4:7)በማለት የአማኞችን የሁልጊዜ ሀላፊነት አሳወቀ። በመሰረቱ ለእግዚአብሔር መገዛት ራስን ለበላይ ባለስልጣል ሙሉ ለሙሉ መስጠት ነው።

ለእግዚአብሔር ስንገዛ በእርሱ ስልጣን ስር ስንሆን የእርሱ ስልጣን በእኛ ላይ ይሆናል። እኛም የእግዚአብሔር ስልጣን ስር በመሆን ዲያብሎስንና አጋንንቱን በፅናት ቆመን መቃወም እንችላለን።

መቃወም፡- የዲያብሎስን ስራ እምቢ ብሎ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እሺ ማለት እና እርሱን ብቻ በመታዘዝ መኖር ነው፤መገዛት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ መፅናት ነው፤ መዝለቅ፤ ይህም እሱን የማወቅ አቅምን ይፈትሻል፤ ብዙዎች ዲያብሎስ በሁሉ ቦታ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ የፈለገውን ማድረግ እንደሚችል በማመን ዲያብሎስንና እግዚአብሔርን እኩል አድርገው ይኖራሉ። በዚህ እምነትና አደራረግ ውስጥ እንድንገኝ እግዚአብሔር አይፈልግም ዲያብሎስም አጋንንቱም





ሆነ በደብረዘይት አለ የተባለው ቆሪጥም ሁሉን አያውቁም፤ በየትም አይገኙም፣ ሁሉን ማድረግም ፈፅመው አይችሉም።

እርግጥ ነው ዲያብሎስና በአጋንንት አማኞች የእግዚአብሔር የሆነውን ፈቃዱን እንዳይፈፅሙ ይተጋሉ፣ ያስታሉ፤ ያታልላሉ፤ ይህ ግን ወደ እግዚአብሔር በመቅረብና እሱን በማወቅ መረታት አለበት፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ 2:10-11 በቆሮንቶስ ያሉ ሰዎች ይቅር ለማለት ባቃታቸው ሰው ላይ ሲወዛገቡ እሱ ግን የመከራቸው «...ይቅር የምለው ስለ እናንተ ስል ነው ይህንንም የምናደርገው ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝነው፤ የእርሱን ዕቅድ አንስተውም» ነበር ያላቸው፤ እግዚአብሔርን ማወቅ እና የሴጣንን ሀሳብ መረዳት አብረው የሚገኙ መገጣጠሚያዎች ናቸው።

ማርቲን ሉተር በፅለት ኑሮው እግዚአብሔርን እያወቀው በመጣ ቁጥር ዲያብሎስን እንደ ቀደመው ጊዜ መፍራት ተወ፤ ምንም ዓይነት ብርሀን በሌለበት መኝታ ክፍሉ በሸራ አልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ በውድቅት ሌሊት ከእንቅልፉ ሲነቃ ዲያብሎስን ከክፍሉ ጥግ ላይ ቆሞ አየው፤ ሉተር በዚህ ጊዜ አልደነገጠም፤ ይልቅስ ያለው «እሺ አጅሬ አንተው ነህ እንዴ» በማለት ተመልሶ ተኛ።

ታዲያ ይህን ግለ ታሪኩን ያነበበው ሰው ይህንን ገጠመኙን መሰረት አድርጎ «መጋቢያችን ሉተርስ ይህን አለው አንተ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?» ባለው ጊዜ የሰውየው ምላሽ «ወንጌላዊውን እጠራለሁ» የሚል ነበር (**የክረኛው ምርኩዝ** ቅፅ 1 ገፅ 292)

እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ የምንም ጥገኛ አያደርግም፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ክርስቶስ በዲያብሎስ ላይ ያገኘውን ዘላቂ ድል በማወቅ ተጠቃሚ መሆን ነው፤ በክርስትና ሕይወትም የነጠረ ዕውቀት፣ እምነትና አቋም በመያዝ ተቋቋሚ ጉልበት እንዳለን በመገንዘብ መኖር ነው።

የተሸነፈ፣ የተማረከ እና የተዋረደ፤ ስልጣን የሌለውን ስብስብ በሙሉ ሀይሉ እንዳለ በማመን መኖር ስጋትን፣ውድቀትንና ተሸናፊ ሆኖ ማለፍን ስለሚያስከትል፤ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብሮ ማበር ተገቢ ነው፤ እሱ ለእኛ ምን ያልሆነው ነገር አለ? ምንም።

እንግዲህ... የተሸነፈውን፣ ዲያብሎስ እንደ አሸናፊ ቆጥረን እንዳንኖር በክርስቶስ ያገኘነው ድል በሕይወታችን የተገለጠ ይሆን ዘንድ ንቃታችን ከፍ ያለ ይሁን፤የዲያብሎስ ተንኮል እና መገለጫው ዛሬም በመስራት ሊዘልቅ ይችላል፤ እኛ ግን ብርቱ በሆነው በኃይሉ በመጠንከር የዲያብሎስን የተንኮል ስራ መቋቋም እንችል ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ እንድንለብስ ታዘናል። ኤፌ 6:10-11 እግዚአብሔርን በማወቅ ኑሮ ውስጥ ሆነን ይህንን ሁሉ ተግባራዊ እናድርገው።

# እርሱን እንስብካለን

*«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን እኔም በብርታት በውስጤ በሚሰራው በእርሱ ኃይል ሁሉ እየታገልሁ ለዚህ ዐላማ እኖራለሁ...»* ቆላ. 1፡28-29።

መልዕክቱ በቆላስያስ ላለች የክርስቶስ ለሆነች ቤተክርስቲያን የተፃፈ ነው፤ ዘመን ተሻጋሪ መልዕክት ስለሆነ ግን ሳይሸራረፍ ዛሬም ላለችው የክርስቶስ ለሆነችው ቤተክርስቲያንም ይሆናል።

በግሌ ከጥቅሱ ጋር ትውውቅ የኖረኝ አዲስ ኪዳንን ከዳር ዳር ባነበብኩት ጊዜ አልነበረም ያኔ ንባቤ መደዴ ስለነበረ መጽሐፍቱን ለመተዋወቅና ለመጨረስ ነበር እንጂ የውስጡን ወቅታዊ መልዕክት ለመረዳት አልቻልኩም፤ ይህ ደግሞ በጌታ በተጠራሁበት ጊዜ የሆነ ነው።

በ1980ዎቹ ደግሞ በጌታ በነበርኩባት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የመንፈሳዊ እድገት ባይጎላም የቁጥር ዕድገት ግን ታየ፤ ለዚህ ደገሞ መፍትሔው ትመማ ሆኖ ተገኘ።

ትምህርተ መለኮትን ማስፋፋት (ትመማ) ዝግጅቱ በአፍሪካ እና በሌሎች ሀገራት ወንጌል ተስፋፍቶ ግን የማደጊያ መንገድ በታጣባቸው ቦታዎች አገልጋዮች ሰዎቹ ወደ አሉበት በመሄድ በተዘጋጁት መፅሐፍት በሳምንት አንድ ቀን ተገናኝተው ይወያዩ ጀመር፤ ይህ ተግባራዊ ሆኖ በዘለቀበት ስፍራ ሁሉ መልካም ውጤት ተገኘ።

በትመማ ክርስቲያኖች በየቀኑ የተሰጣቸውን ስራ ይሰራሉ፤ በሳምንት ተገናኝተው





በአካባቢያቸው ካለው ከአስተባባሪው ጋር ይሰራሉ፤ ይህ ፕሮግራም ነበር ከፍተኛ ለውጥ በተጠቃሚዎቹ ሁሉ ላይ ያመጣው።

የዚህ ዓለም አቀፍ ፕሮግራም መሪ ጥቅስ ቆላ. 1፡28 ነው። «እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርጎ ማቅረብ...»።

***

በመሰረቱ በአገራችን መስከረም አንድ በሆነበት እለት «ከዘመነ... ወደ ዘመነ ... አደረሳችሁ እንባባላለን»።

በኢትዮጵያውያን አዲሱ ዓመት ሲመጣ በውጭ ያሉ በ«ዲያስፖራ» ስም ተጠሪዎቹ «መስከረም ሲጠባ ወደ ሀገሬ ልግባ» ይሉበታል፤ በሀገሪቱ ያሉት ደግሞ «የጎመን ድስት ይውጣ! የገንፎ ድስት ይግባ» ይሉበታል።

በቀደሙት አመታት መስከረም ሲገባ በዋዜማው ወይም በዕለቱ ማለዳ ብዙዎች ተልባ ወይም ፌጦ አዘጋጅተው ይጠጣሉ፤ በዚህም ሆዳቸው ንፁህ እንዲሆን ያደርጋሉ፤ ንፅህናው ባለፈው ዓመት የነበረ እጓጉል አስተሳሰብ፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ቅናት፣ ምቀኝነት ቢሆን በአዲሱ ዓመት እንዳይመለስ «በተምሳሌትነት» የሚደረግ ነው። ይህም አዲሱን አመት በአግባቡ ተዘጋጅቶ ለመቀበል የሚደረግ ዝግጅት ነው።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድም መስከረም 1 ከመግባቱ በፊት ባሉት 5 እና 6 ቀናት በጳጉሜ የፀሎት፣ የምክክር፣ የንስሀ ጊዜ በጌታ ፊት ይወሰዳል፤ በዚህም ከመስከረም አንድ ለሚጀምረው አመት የአቀባበል ዝግጅት መሆኑ ነው።

ይህ መስከረም አንድ ግን፡- እውደ አመት፡- ርዕሰ አውደ አመት፤ ቅዱስ ዮሐንስ፡- (መጥምቁ ዮሐንስ)

እንቁጣጣሽ፡- (እንቁ ለጣጥሽ ንግስት ሳባን አስመልክቶ) የዘመን መለወጫ በመባልይጠራል፤ በዚህም ኢትዮጵያውያን አራት ያህል መግለጫ ለአመቱ መጀመሪያ አለን፤ ፈረንጆቹ ግን «NewYear» ከማለት ባሻገር ሊሉት የሚችሉት ነገር የለም።

እውደ አመት ሆኖ በአመት አንድ ጊዜ ሲመጣ፡- ወቅቱ ራሱ አመላካች መገለጫን ይይዛል የአደይ አበባ ይወጣል፤ የመስቀል ወፍ ካለችበት ተጉዛ በኢትዮጵያ ምድር ትታያለች፤ ይህ በዓል በአመት አንድ ጊዜ ዞሮ መምጣቱ ከሌሎች በዓላት ጋር እንዳይጋጭ በዓሉ ርዕስ ወይም ራስ መሆኑን

ለመግለፅ አግዟል፤ ከዚህም ተነሳ ርዕሰ አውደ ዓመት መባሉ ተገቢ ነው።

አንዳንድ ሊቃውንት ርዕሰ ያሰኘው፡- «ዓመተ ምህረት ያስባለውን አቅም በጌታ ልደት ስላስገኘ ነው» ይላሉ፤ ይህም ኢትዮጵያውያን ገናን የጌታን ልደት በፈረንጆች ታህሳስ 28/29 ላይ ከማክበር ተገቢ አመት በዓላቸው መስከረም አንድ ቢሆን ጥሩ ነበር» በማለት አግባብነት ያለው ሙግት ያነሳሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ በመባሉም የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ይተሳሰራል «እኔ ላንስ እሱ ሊልቅ ይገባዋል...» ያለለትን ከተግባር በማዋል፤ የአዲስ ኪዳን መሰረት ጣይ የሆነውን ኢየሱስን ለማክበር ይህን ባስተዋወቀው ዮሐንስ በየአመቱ ይጠራል፤

የሳባ ንግስት ከኢትዮጵያ ተነስታ ወደ ንጉስ ሰለሞን በመሄድ እሷም በስጦታ አስደነቀችው፤ እሱም ለጣቷ የእንቁ ፈርጥ አድርጎ አስደመማት፤ ይህም ወቅት በመስከረም መነሻ ላይ ሊሆን ይችላል በማለት «እንቁጣጣሽ» (እንቁ ለጣትሽ) ሆነላት፤ በማለት አዲሱን አመት ከአማርኛው የቃላት ቅንብር ጋር የሚያዋጡበት ጊዜ ይኸው የመጀመሪያ ቀን መስከረም አንድ ነው።

የዘመን መለወጫ አመት አልፎ በሌላ አመት መተካቱን ማሳያ በመሆን ማገልገሉን እንዲሁም ዘመኑ እየተለወጠ እየተጨመረ ወደ ዘመን ማጠቃለያ እየተቃረብን መሆኑን ማረጋገጥ በራሱ ተስፋ ስለሆነ መስከረምን እያሰብን እንኳን ለዘመን መለወጫ አደረሳችሁ እንባባላለን።

***

እንኪያስ ይህን ርዐሰ ጉዳይ በዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ላይ ተገኝተን እንዳነበብነው እንቁጠር፤- ያኔ ሐዋሪያው ጳውሎስ ቆላስያስ ተብላ ለምትጠራው ዛሬ የቱርክ ዋና ማዕከል ለሆነችው ሀገር ፃፈ፤ እሱ በኤፌሶን በነበረው የሶስት አመት ቆይታ ለቆላስያስ ሸክም ያለውን ኤጳፍራን አገኘ፤ እሱ ወደዚያ ሄዶ ክርስቶስን አስተዋወቀ፤ ጳውሎስም አገዘው። በዚያ ከአይሁዶች ይልቅ የሚበዙት አህዛብ ናቸውና የከተማዋ አስተሳሰብ በብዙ በ «ጊዜው ዘመናዊ ግንዛቤዎች» ተሞልቶ ነበር።

በቆላስያስ ያሉ አማኞች ከፊሎቹ ወግ አጥባቂዎች ነበሩ (2፡16-17፣ 2፡11፣ 3፡11)፤ ለሀይማኖት በዓላት፤ ለአመጋገብ ስርዓት፤ እንዲሁም ግዝረትን ለሁሉ ለማድረግ ይደክሙ ነበር፤ (2፡21-23)።

እነርሱ አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካ በማለት ኢጋጅ የመለያ ስርዓቶችን ሁሉ ቀየጡ፤ ከፊሎቹ መላዕክትን ልናከብር ልናመልክም ይገባል (2፡18) በማለት «የምን ከፋት አለበት» እንቅስቃሴ





ጀምረው ነበር፤ ይህንን ለማመንም መላዕክት እግዚአብሔር በነበረበት ጊዜ አብረው ይኖሩ ዘንድ የተፈቀደላቸው ናቸው በማለት ተበረታቱ። ከፊሎቹ ክርስቲያን ነን እያሉ ለክርስትናቸው መሰረት የጣለውን ክርስቶስን ይንቁ ነበር (1፡15-20፣ 2፡2-3) ወልድ እግዚአብሔር መሆኑን ልብ ባለ ማለት ያለ ፍርሀት ይኖሩ ነበር፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ ግን ክርስቶስ እሱ የተሰወረ የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ እንዳለ ገለፀ።(2፡18)

ከፊሎቹ በሰው ጥበብና ወግ መታመንን (2፡4-8) እንደ ትልቅ ነገር በመቁጠር መደገፊያ አድርገው ይኖሩበት ነበር። ይህ ግንዛቤ ዓይነቱ ሊለያይ ይችል ይሆናል እንጂ ባንባቢያን ሁሉ ዘንድ ከእነዚህ አንዱ ወይም ሁለቱ አልያም ሁሉም ሊገኙ ይችላሉ።

በሀገራችን የምትገኝ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የትልቋ ኢትዮጵያ ትንሻ ክፍል ነች፤ ትንሿ ኢትዮጵያ ናት፤ በዚያ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሚያደርሱ ወጎች ይጠበቁ ይሆናል፤ ያለ ዕድገት የሚያስቀሩ «ክልክል ነው» የምንላቸው ብህትውናዎች ይኖሩ ይሆናል፤ የብዙዎች የቀደመው ዕውቀትና እምነት ከመላዕክት ጋር የተያያዘ ሆኖ «ምን አለበት ለክርስቶስ ቅድሚያ ሰጥተን ከዚያ እነርሱን ብናስከትል የሚል ሚዛኑን ያልጠበቀ አኗኗር ይኖር ይሆናል። በትይዩ የኢየሱስ ሰውነት ብቻ ጎልቶ መለኮትነቱን ያፈዘዘ እምነትም ይኖር ይሆናል፣ ብዙዎቻችን ሰውን በመታመንና ወግን በልሙጡ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ በመውሰድ የእግዚአብሔርን ልዕልናንም ችል እንል ይሆናል።

እነህ እርሾዎች በየትም ተገኝተው ቢሆን የምስራች፡- መልካም ዜና አለልን፤ እሱም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑን (1፡15)፣ ፈጣሪ መሆኑን (1፡16)፣ ከሁሉ በፊት የነበረና ሁሉም በእርሱ የተጋጠመ መሆኑን (1፡7)፣ ከሞት በመነሳት የመጀመሪያ መሆኑን (1፡18)፣ በአካል የተገለጠ የመለኮት ሙላት መሆኑን (1፡19፣ 2፡9)፣ አስታራቂ መሆኑን (1፡20-22)፣ በማስተዋል አቅምን መፍጠር እና እምነትን ማሳደግ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ በሐዋሪያው የተገለፀው። «...እኔም በብርታት በውስጤ በሚሰራው በእርሱ ኃይል ሁሉ እየታገልሁ ለዚህ ዐላማ እጥራለሁ...» (ቁ.29) ይላል፤ በዚህ ቁጥር ላይ ሶስት ሀረጋትን ማስመር ያስፈልጋል።

1. <u>እኔም፤</u> 2. <u>በእርሱ ኃይል፣</u> 3. <u>ለዚህ ዐላማ</u>

ጳውሎስ ከመላው ክርስቲያን መካከል ራሱን አውጥቶ በብቻው ማንነቱን ያያል፤ እኔ በማለት የራስን ሁነኛ ኃላፊነት በመወጣት ራስን መጥቀም እና ለሌሎችም መትረፍ መቻሉን ያስተምራል።በዚህም የኃላፊነትንና የተጠያቂነትን አግባብም ያስረዳል።

መልካሙ ዜና በየአመቱ እኔ ስራ ፊት አይደለሁም! ስራ አለኝ ስራዬ «ደግሞ ልሰራው ላደርገው የምችለው ነው እንድል ያዘጋጀኛል። «ጳውሎስ ይህ ደግሞ «...በውስጤ ስራውን እንድሰራ የሚያደርገኝ የእርሱ ኃይል በእኔ ዘንድ በመኖሩ ይሳካልኛል» ይላል።

በመሰረቱ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ያድር ዘንድ እግዚአብሔር አድርጓል፤ በውስጡ ያለው እሱ ኃይል ሆኖ ስራውን ያሰራዋል፤ ከዚህም የተነሳ በገዛ ጉልበታችን በብዙ ድካም፣ በንጭንጭ የምንሰራው ስራ የለንም ይልቅስ እግዚአብሔር ነው አቅማችን፤ ይህ ሁሉ ግን የሚሆነው ሐዋሪያው ዐላማ(ግብ)እንዳለው ተረድቶ ለዚያ ሰርቶ ለማለፍ መነሳቱ ነው። ይህን ደግሞ አጣጥሞ ለማብራራት ሁነኛ መረጃ ለስጥ፡-

***

በነሀሴ 2004 እ.አ.አ. አብዬ አረፈ፤ አብዬ የምለው እንደታላቅ ወንድም ሆኖልኝ ስለነበር ነው፤ ሰለሞን ሰዩም የታላቅ እህቴ የአካሌ ባለቤት ነው። እነርሱ፡- ሶስት ሴቶች ልጆችን ወልደዋል፤ መንደርደሪያ ያደረኩት ይህ ሰለሞን የእናታችን ሞት መፅናኛ ነው፤ ለአባታችን ደግሞ እውነተኛ ምርኩዝ ነው፤ ለቤተሰባችን በነፍስ ወከፍ አመላካቻችንም ነው፤ ሰለሞን፤ ለባለቤቱና ለልጆቹ አፍቃሪ ባልና አባት ነው፤ ያሳየን ዘላቂ ፍቅር ሙዋቿነቱን ፈፅሞ አስረስቶናል፤ ታዲያ እሱን ተከትሎ ወደ ጌታው የተጠራው ወንድሜ ጳውሎስ ታደሰ ደግሞ ከንጋቱ 12 ሰዓት ላይ «ሰለሞን ስለአፈነው ቤቴል ሆስፒታል ኑ» ብሎ ደወለ፤ ወደዚያ ለመብረር እየተጣደፍን እንደገና «ወደቤቱ ኑ አለ...» እናም በስልኩ ውዝግብ «ሰለሞን አረፈ » መርዶአችን ሆነ።

ሰበብ የሆነው አስም ግማሽ ሰዓት ባልሞላው ጊዜ ሲያሳጣን፤ ተቀጣጥረን ሳንተያይ ስንቀር እና የማይታየው ምርኩዝ ሲታጣ መዋተት ተፈጥሮአዊ መገለጫ ሆነ። እንዲህም ቢሆን አባታቸው ወደጌታ በሄደ በ15ኛው ቀን ከሁለተኛዋ ልጁ ከኤደን ሰለሞን ጋር ምክር ያዝን «በረታሽልኝ ወይ? ቢሮ ስትገቢ ስራው ተደራርቦ ጠበቀሽ ወይ? የስራ ባልደረቦችሽ እንዴት አስተናገዱሽ?» አልኳት።

የሀያ ሶስት አመቷ ኤደን፤ እኔን አጎቷን ትክ ብላ እያየች « ቅዳሜ ሊያርፍ አርብ ዋዜማ በእኔ አስተባባሪነት ለሚደራጁት ከ30-40 ለሚደርሱ ወጣቶች ቃል የማካፈል ተራው የእኔ ነበር፤ በዚያን ምሽት ያካፈልኩት «ጳውሎስ በመኖር የተለየ ፀጋ ተሰጥቶት የኖረ ሰው ሳይሆን ሰው የሆነ ሰው ነው፤ እሱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ እየጣረ ኖረ «...*ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ...ደግሜም እላለሁ በጌታ ደስ ይበላችሁ...*» (ፊሊ. 4፡4) አለ፤ ክርስቲያን ሁኔታዎች በሚያስገኙለት ስኬቶች ይደሰት ዘንድ አልተጠራም፤ ስንማር፣ ስንመረቅ፣ ስናገባ፣ ስንወልድ፣ ቤት ስንሰራ፣ ስናገኝ...በሚሆኑ ነገሮች ላይ ደስታን እንደ የመጨረሻ መደምደሚያ ካደረግን እነርሱ ሲጎድሉ፣ ሲጠፉ ያኔ ሀዘንተኞች





እንሆናለን፤ ከዚህም የተነሳ የእኛ መለኪያ እና የመኖር አላማ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈፀምን በመኖር ደስታችንን በጌታ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን ይህ ሲሆን እንደ ጳውሎስ ትልቁን አደራ ተወጥተን ለመገኘት አቅም ይኖረናል። ባልኩ ንጋት ነው አባቴ ያረፈው፤ አባቴ በእጄ ላይ ነው ያረፈው፤ እሱን በማጣት ውስጥ ያስተዋልኩት፤ አባቴ አሁን ከጌታ ጋር መሆኑን እኔም መከተሌን አውቃለሁ። የሚገርመው ከሳምንት በኋላ ወደ ቢሮዬ ስገባ ሁሉም ተደንቆ የነገረኝ ደግሞ «ኤደን እንደ ቀድሞው ፍልቅልቅ ሆና ስራውን በአግባቡ አትሰራም›› ብለው ገምተው ነበር ሲያዩኝ ግን ተገረሙ ዛሬም ተስፈኛ እና ደስተኛ ነኝ ሲጠይቁኝም ያልኩት በጌታ ደስ የመሰኘትን ምንነት መግለፅ ነበር ። ኤደን ሰለሞን በውስጧ የሚሰራውን እያሳወቀችኝ ለዓላማዋ ተጋች።

ለዚህ ዐላማ ጳውሎስ «እጥራለሁ» ነው ያለው፤ ጥረት እና መጋደል ያልተቋረጠ ተግባር ነው፤ ወረት የለበትም፤ ጀምሮ መተው አያውቅም ፤ ሁልጊዜ ስለዚያ ማሰብ ለዚያም መኖር መለያው ነው፤ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች በብዙዎች ውስጥ ተደብቀው ይኖራሉ፤ ከዚህም ተነሳ የግላቸው የሆነ ምንም ጥረት የላቸውም፤ ኑሮአቸው ቃሉ«አድርጉ» እንደሚለው ሳይሆን በሆነው ባልሆነው ሰምተው እንዳልሰሙ ይሆናሉ።

ዐላማ አደራን ከዳር ለማድረስ የሚኖር ሕይወት ነው፤ ጳውሎስ እኔ ዐላማ ስላለኝ ለዚያ እጥራለሁ፤ በማለቱ ይህ ዘንድሮ ላለነው ለእኛ በእያንዳንዳችን ውስጥይኖርብን ዘንድ ሐዋሪያው ፅፏል፤ በቆላስያስ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያ ባሉት ዳግም ተወላጅ ክርስቲያኖች ዘንድ ምክሩ ኑሮው ነውና ለውጥ የለውም።

በመሰረቱ «ለዚህ ዐላማ እጥርለታለሁ...» ያለለትን መርህ በቁጥር 28 ባያስተዋውቀን ኖሮ ግራ በተጋባን። እሱ ግን «...*እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን...*» (ቆላ 1፡28) አለ።

«እኛም እያንዳንዱን ሰው...» በማለት ጳውሎስ ራሱን አካቶ የሚፅፍላቸውን ቆላስያሳውያንና ሌሎች አማኞችን በማካተት መልካም ዜናን ወይም የምስራቹን መንደርደሪያ ያስተዋውቃል፤ እኛ በክርስቶስ ሆነናል፤ እኛ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰናል፤ እኛ በእግዚአብሔር አብ ተመርጠናል፤ እኛ ተለይተናል፤ ይህ ሁሉ በገዛ አቅም የተገኘ «የብዙሀን ያሸንፋል» ምንነት ሳይሆን እኛ ለማለት እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሰራው ስራ መሰረት ነው። ከዚህም የተነሳ ለሁላችን ከተደረገልን ብዙ ነገር የተነሳ ኑሮአችን እያንዳንዱን ሰው በተናጥል ደራሽ ሊያደርገው ይገባል፤ ይህ ለእያንዳንዱ ሰው ያለልዩነት የተነደፈ መርህ ግብር ነው፤ የክርስቲያች ማህበር በዘር፣ በቀለም፣ በሀገር፣ በወንድ፣ በሴት፣ በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ አንዱ ሌላውን የሚለይበት ምንም ምክንያት የለውም፤ በሁሉም

መካከል መሀከለኛ የሆነ አንድ ክርስቶስ አለ፤ እሱንና የእሱን ስራ በተመለከተ ሁሉም እያንዳንዱን ሰው የመድረስ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፤ ያ ተልዕኮ ለቆላስያስ ቤተክርስቲያን ይድረስ እንጂ ያለ ለውጥ ለኤፌሶን፣ ለገላትያ፣ ለሮም በየትም ላሉ ሁሉ ያለ ልዩነት ይሰራል፤

እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ አለብን ይህን ደግሞ ሁላችን መቻል አለብን ጳውሎስ የግል ድርሻውንና እርስ በርስ የሚተያዩበትን የጋራ ድርሻ ነው ያሳወቀው።

ጳውሎስ ነው እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ ያለው፤ ይህ ደግሞ የክርስቶስን ፈቃድ በመፈፀሙ እና ሌሎች የዚህ ተጋሪ ሆነው በመኖራቸው ይገለፃል። ለዘንድሮ ሰዎች ይህ ቃል መልካም ዜና ነው፤ የምስራች ነው፤ ጳውሎስ መሆን የሚችለውን እና የምንሆነውን ነው የሚነግረን፤ ይቻላልም።

ያ ደግሞ እያዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም ማድረግ ነው፤ ይህን ደግሞ ተግባራዊ ለማድረግ «... ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን...» ይህ ገለፃ ሙሉ መብራራት ያገኝ ዘንድ የእንግሊዝኛ ትርጉሞችን አስከትዬ አቅርቤያለሁ

«... Whom we preach, warning every man and teaching every man <u>in all wisdom</u> that we many present every man perfect in Christ Jesus (KJV)

«...Him we preach and proclaim, warning and admonishing every one and instructing every one <u>in all wisdom</u> (Amplified)

«...And we proclaim Him, admonishing every man and teaching every man <u>with all wisdom,</u> that we may present every man complete in Christ (NASV)

«...we proclaim him, admonishing and preaching every one with <u>all wisdom,</u> so that we many present every one perfect in Christ...» (NIV)

*«...እርሱ እኛ የምንነግርበት ሰውን ሁሉ እየገሰፅነ፣ <u>በጥበብም ሁሉ</u> እያስተማርነ ሰውን ሁሉ ፍፅም አድርገን እናፀና ዘንድ በክርስቶስ የሱስ (1879-አባሮሜ)*

*«...እርሱም ኢየሱስ ክርስቶሰን በማመን፣ ፍፁም የሚሆነውን ሰው እናቀርበው ዘንድ እኛ የምናስተምርለት፣ ሰውን ሁሉ ወደ እርሱ የምንጠራለትና የምንገስፅለት ስራውንም <u>በጥበብ ሁሉ የምንናገርለት ነው</u>* (ስማንያ አሀዱ 2000 ኢአተቤክ)





*«...ስለዚህ በደረስንበት ሁሉ ለሚሰሙን ስለ ክርስቶስ እንናገራለን በዚህም <u>በተሰጠን ጥበብ ሰዎችን</u> እያስተማርን፣ በክርስቶስ ፍፁማን ሆነው እንዲገኙ ለማድረግ እንተጋለን...»* (**ሕያውቃል** 1988)

*«እኛም በክርስቶስ ፍፁም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ እየገሰፅን፣ ሰውንም ሁሉ በጥበብ <u>ሁሉ እያስተማርን፣</u> የምንሰብከው እርሱ ነው፤ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሰራ እንደ አሰራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ* (*ቀኃሥ* 1955)

የእንግሊዝኛውንም ሆነ የአማርኛውን የፈተሽኩት «ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ» የሚለው መዋቅር እንዲገባኝ ነው ሰዎች (አማኞች) ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ኑሯቸው ማቆሚያ አልተበጀለትም፤ ኑሮ ዓላማ ኖሮት ቀጣይ ነው፤ ቀጣይነቱ በክርስቶስ ፍፁማን እስከሚሆኑ ድረስ ይዘልቃል።

ይህ አዘላለቅ ግን «ጥበብ»ን በዋነኝነት ይፈልጋል፤ ጥበብ የተዘራው ዘር በሰው ውስጥ በቅሎ እንዲታይ የሚያደርግ ስልት ወይም ዘዴ ነው፤ ጥበብ የተገኘውን እውነት ወይም የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ እያንዳንዱ ሊጠቀምበት የሚችልበትን ሁኔታ ማድረስ ወይም ማምጣት ነው።

እያንዳንዱ የወል ስም መጠሪያ ሊኖረው ይችላል ሰው ወይም ክርስቲያን ተብሎ። ግን ይህን መጠሪያ የያዘው ማህበር የግለሰቦች ስብስብ ነው፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ እያንዳንዱ እያንዳንዱን በመድረስ ማደግ እና ወደ ፍፁምነት እንደሚደርስ ይናገራል፣ ያውጃል፤ ለዚህ ማጓጓዧያው ጥበብ ነው፤ በጥበብ እንመክራለን፣ በጥበብ እናስተምራለን፣ በጥበብ እንሰብካለን። ምክሩ፣ ትምህርቱ እና ስብከቱ ግን ክርስቶስ ነው።

ክርስቶስ የሆነበት ምክንያት ደግሞ «...እርሱ ከጨለማ ስልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም፣ እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን። እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ስልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው።

*«እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና።*

*«እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ በፊት የተለያችሁትን ከፉ ስራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁ አሁን በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።*

*«ይህም ተመሰርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት (በእምነት) ፀንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፤ ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ...*(ቆላ 1፡13-23) አሜን።

ክርስቶስን በመስበክ ሁሌም መኖር የምስራች ዜና ነው፤ እንደ አገራችን አቆጣጠር መስከረምን አንድ ብለን በጀመርን ቁጥር የጀመርነው አመት ሁሉ ርዕሰ አውደ አመት ፤ ቅዱስ ዮሐንስ እና የዘመን መለወጫ መሆኑን ልብ እንበል።



# አገልጋዮቹን ጠርቶ

ጳውሎስ ፈቃዱና ሶፋኒት ታመነ ባገቡ ዕለት እኔና ዳዊት ፀጋዬ ጎን ለጎን ተቀምጠን ነበር።

በስነ ስርዓቱ ማጠቃለያ ላይ፡- የሻማ ማብራት ስርዓት ሲካሄድ ሁለቱም «የእኔ» ብለው ካሉት ከሚበራው ሻማ በማንሳት ወደ ትልቁ ላይ አጋቡ የመሀሉ ሻማም ብርሀን ሰጠ፤ ከዚያም ሁለቱም ተጠንቅቀው ዞር ብለው የየራሳቸውን አጠፉት፡- መጠንቀቃቸው በገዛ ንፋሳቸው የመሀሉ እንዳይጠፋም በመጨነቅ ነው፤ ከዚያም ትልቁን በጋራ ይዘው አስተዋወቁን አጨበጨብን፤ ጭብጨባውን ተከትሎ ቃል ኪዳን አስፈፃሚው አሁን በጋራ «ትልቁን» የሻማ ብርሀን ያሳዩናል፤ አለን፤ አደረጉት፤ እኛም ደስ አለን።

የዳዊትና የእኔ ሹክሹክታ ግን «ለምን የየራሳቸውን ያጠፉታል? እንደበራ ቢቀጥልስ እነርሱ በግል ያበሩትን እና ለእኛ ያስተዋወቁንን ማጥፋትን ምን አመጣው? ተባባልን በመሰረቱ የአማኞች ተፈጥሮአዊ ስጦታም ሆነ በድነት ያገኙት የፀጋ ስጦታ እያንዳንዳቸውን ልዩና ተፈላጊ አድርጓቸዋል፤ ያንን በነጠላም «ሲያበሩ» ኖረዋል፤ በዚህም መቀጠል አለባቸው።

እርግጥ ነው ከዚህ በኋላ ቤተሰብ ተመስርቷል «እግዚአብሔር ያጣመረውን ከእንግዲህ ሰው አይለየው» የተባለለት ጥምረት በእነርሱ ዘንድ አለ፤ ሁለት ሰዎች ወንድና ሴት ተገናኝተውበታል።

ታዲያ እነርሱ ተጋብተው ሲኖሩ፣ ተጠጋግተው ሲኖሩ የሚቀባበሉት ብዙ ብዙ ነገሮች አሉአቸው።

- እየተግባቡ የበለጠ ይግባባሉ፣
- እየተጋጩ ይስማማሉ፣
- እየተለያዩ ይገናኛሉ፣
- እየተወቃቀሱ ይበረታታሉ፣
- እየተዋደዱ ይፋቀራሉ፣

የመሀሉ ወፍራም ሻማ ይህን አቅም በትዳር ውስጥ ለመፈፀም እና ብርሀኑን ለማድመቅ የጋራ ጥረት በሚጠይቀው የቤተሰብ ስራ ውስጥ መገባቱን የማረጋገጫ ተስፋ መሆኑን አመለከቱዋል።

ከዚህ የተነሳ «ሶስቱም በርቶ ቢተው አሁን ምን አለበት» ተባብለናል፤ ያልበራውን አብርቶ ሌላው እንደበራ ቢቀጥልስ።

***

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንግስትን ምንነት ለማብራራት በቀዳሚነት «ሙሽራ ለመቀበል ስለወጡ ልጃገረዶች» በምሳሌ አስተማረ ዘልቆ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግስት ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ሊኖራቸው የተገባውን ሀላፊነትና ተጠያቂነት በመግለፅ አብራራ ይህም በማቴ 25፡1-30 ተፅፏል።

*«...ወደ ሌላ ሀገር የሚሄድ አንድ ሰው አገልጋዮቹን ጠርቶ ንብረቱን አስረከባቸው» ይላል። ለእያንዳንዱ እንደ ችሎታው በማካፈል ለአንዱ አምስት ሺህ ብር ለአንዱ ሁለት ሺህ ብር ለአንዱ ደግሞ አንድ ሺህ ብር ሰጠና ወደ ሌላ ሀገር ሄደ...» ቁ.14-15 በማለት ይዘልቃል።*

ገለፃው፡- ወደ ሌላ ሀገር መሄድ ላይ ትኩረት አድርጓል፤ ተጓዡ ብዙ ይቆያል፣ ለወራት እንደ ሁኔታው ለአመታት። ከዚህም የተነሳ ሰውየው ከመሄዱ በፊት ተገቢውን አደረገ በዚህም፡-

1. መሄዱን አረጋገጠ እና ከርሞ መምጣቱን አወቀ፣
2. አገልጋዮቹን ጠራ፤ በስራው ያግዙትና ይረዱት የነበሩትን፣
3. ንብረቱን ሁሉ አስረከባቸው፤ ሁሉን ሰጣቸው፤
4. ሲሰጥ በግምት አላከፈለም ይልቅ እንደየችሎታው አደላደለ፣





5. በመሰረቱ እንደየችሎታው ለማካፈል እነርሱን ማወቅ ይጠይቃል፤ ማንነታቸውን መረዳት ያስፈልጋል፤ ፍላጎታቸውንም መለየት ተገቢ ነበር።

ይህንን ባገናዘበ ሁኔታ ስላካፈ ለጌታው ፍትሀዊ ነው፤ የድርሻ ልዩነት የኖረው አንዱን በመጥላት ሌላውን በመቅረብ ሳይሆን ውጤታማነትን ከተገቢ ተጠያቂነት ጋር ለማጣጣም የሆነ ነው።

«...ለአንዱ አምስት ሺህ ብር ለአንዱ ሁለት ሺህ ብር ለአንዱ ደግሞ አንድ ሺህ ብር ሰጠና ወደሌላ አገር ሄደ» ቁ.15

***

ልብ እንበል ሰጥቶ ነው፣ ወደ ሌላ አገር የሄደው፤ መቼም አሰሪ ወደ ሌላ ሀገር ሲሄድ ከዐይን ይርቃል፤ ከዚህም የተነሳ አብረውት የነበሩት የአገልጋዮቹ አቋም በፈተና ውስጥ ይወድቃል!

ጌታቸውን፡- - ከመታዘዝ/ ካለመታዘዝ

- ከማፍቀር/ ከመጥላት
- ከአሸታ/ ከእምቢታ
- ከአትኩሮት/ ከፈዛዛነት
- ከወዲያው/ ከያደርሰኛል አቋም ራሳቸውን መለየት ይኖርባቸዋል፤ ይህንንም ጌታ ኢየሱስ እንደሚከተለው ገለፀ፡-

«...አምስት ሺህ ብር የተቀበለው ወዲያውኑ ሄደ ነገደበትና ሌላ አምስት ሺህ ብር አተረፈ፤ ሁለት ሺህ ብር የተቀበለውም እንዲሁ (ወዲያው ሄደ) ነግዶ ሌላ ሁለት ሺ ብር አተረፈ» (ቁ.16-17)

***

ጌታቸው የታመነባቸው አገልጋዮች ወዲያውኑ ወደ ስራ ገቡ፤ የተቀበሉት ሊሰራበት የሚችል ሀብት ነው፤ ከዚህም የተነሳ የጌታቸውን ንብረት በብዙ ጥረት በእጥፍ አሳደጉት።

በእጥፍ ማሳደግ፡-

- ✓ ለውጥን ያመለክታል፤ ዕድገትን ያሳያል፤

- ✓ የታማኝነት ምንነትን ይገልፃል፤
- ✓ እንደ ችሎታቸው መስጠቱን ያረጋግጣል።

ግና አሰሪው (ጌታው) የማይወቀስበትን አገልጋዩ ግን የሚዘለፍበትን ስራ የሰራ አንድ ሰው ተገኘ፡-

*«...አንድ ሺህ ብር የተቀበለው ግን ሄደና መሬት ቆፍሮ የጌታውን ገንዘብ ቀበረ...» ቁ. 18*

***

ሁለቱ ሄደው ወደ ስራው ገቡ፤ ይህም እንደ እነርሱ መሄዱን ሄደ፤ ግን የሄደው መሬት ቆፍሮ ለመቅበር ነበር፤

ይህ አገልጋይ የቀበረው፡- - ራሱን ባያውቀው ይሆናል፤- ችሎታውን ልብ ሳይለው ቀርቶ ይሆናል፤- በቸርነቱ ያገኘውን አልተገነዘበው ይሆናል፤ ተፈጥሮአዊ ችሎታውን፤ እንደ አማኝ የፀጋ ስጦታውን አላወቀ ይሆናል። ይህን ሁሉ አለማወቁ ግን ራሱን ካለማየቱ የመጣ የገዛ ጣጣው እንጂ የማንም ጥፋት አይደለም።በትይዩ ሰውየው ሆን ብሎ አደራ የተቀበለውን ሐላፊነት ላለመፈፀም ወስኖም ይሆናል።

ይህ ደግሞ፡-

- ➢ ለሌላው ጌታ ታማኝ ለመሆን በመፈለግ፣
- ➢ ለሌላው ገዢ ባሪያ ለመሆን በመምረጥ፣
- ➢ በጌታውና በንብረቱ ባለመታመን፣
- ➢ ራሱን «በመናኛ» አኗኗር በመምራት፣
- ➢ «ቀላል» ኑሮን መርጦ በመዝለቅ ለመኖር ፈልጎ ይሆናል።

ከዚህም የተነሳ፡- የተሻለው ውሳኔው ከዕለታት አንድ ቀን ጌታው ይመለሳል፣ በዚህ ግዜ «የሰጠውን እንዳለ በመመለስ ታማኝነቱን» ያረጋግጣል፤ ይህ ውሳኔ ግን አዋጪ አይደለም፤ አይሆንምም፤

«...ከብዙ ጊዜ በኋላ የነዚያ አገልጋዮች ጌታ መጣና ከአገልጋዮቹ ጋር መተሳሰብ ጀመረ...» (ቁ.19)

***





አገልጋዮች ኃላፊነት አለባቸው፤ ተጠያቂዎች ናቸው፤ ይህ ደግሞ የሚሆንበት የሚመዘንበት ግዜ መጣ፤ ያም የጌታቸው መመለስ ነው፤

***

ጌታቸው ወዲያው ወደስራው ገብተው እየሰሩ የደረሰባቸውና በአግባቡ ሪፖርት ያቀረቡትን፤ የሚታይ ስራ የሰሩትን አመሰገናቸው፤ አከበራቸው። «...መልካም አደረግህ አንተ በጎ ታማኝና ደግ አገልጋይ በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ ስለተገኘህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሀለሁ...» ቁ.21 የሚለውን ቃል ደገመ፤ አላቸው።

***

ሌላኛው ግን ተነቀፈ፤ ተዘለፈ፤ እንደ ችሎታው የተሰጠውን ተነጠቀ።

***

ጌታ ኢየሱስ ይህን መልዕክት ያስተላለፈው የመንግስቱ ዜጎች ያላቸውን ኃላፊነት ለማብራራት ነው። የመንግስቱ ዜጎች፡- በዚህች ምድር ላይ በመኖር የእግዚአብሔርን መንግስት እያሰፉ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር እንዲሰፍን የሚጥሩ ሕዝቦች ናቸው።

የዜግነት ሐላፊነት፣ የተጠያቂነት ምንነት የሚለካው፤ የሚሰራው፣ የሚጠናቀቀው፣ ተጠያቂ በማድረግም የሚገለፀው በዚሁ ምድር በተከናወነ ክንውን ነው።

ከዚህም የተነሳ ራሳችንን እንፈትሽ ዘንድ የጠራን፣ ያዳነን፣ ጌታ ከእርሱም ጋር አንድንሰራ አጋሮች አድርጎናል፤ እያንዳንዳችን የየበኩላችንን ሐላፊነት በመወጣት አደራን ተወጪዎች ነን፤ እንግዲያስ... ዕድሜያችን ፍሬያማ በመሆን የሚዘልቀው በስራ ላይ ስንገኝ ብቻ ነው።

በመግቢያዬ ያነሳዋቸው ባልና ሚስት በአንድ መኖር ይጀምራሉ፤ በዚህም ቤተሰብ ይመሰረታል፤ ሁለቱም የሚያበሩት ብርሀን ቀጣይነት ይኖረዋል። በጋራ ሆነው ቤታቸውን ሲመሩ ደግሞ እግዚአብሔር አቅማቸውን እና ችሎታቸውን አይቶ አጣምሯቸዋልና የግልና የጋራ ሐላፊነት ወስደዋል፤ በዚያ ሊኖሩበት ይገባል።

እነርሱ ራሱን ማየት እንደተሳነው ሰው መሆን የለባቸውም ይልቅኑ ጋብቻ መንፈሳዊ ሕይወት የሚሞረድበት የሚቀረፅበት ሁነኛ ስፍራ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።

በጋራ የተለኮሰው ሻማ በመተዋወቅ፣ በመተማመን፣ በመተሳሰብና በመፈቃቀር መገለፅ ይጠበቅበታል።

በዚህ ዘላቂ ኑሮ ውስጥ በርካታ እንቅፋቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነርሱን ማረም ማስወገድ ተገቢ ነው።

***

ጓደኛሞቹ የተሳፈሩበት መርከብ በማዕበል ተጎዳች በመጨረሻም ተንኮታኮተች፤ በዚህ ግዜ ሁለቱ ጓደኛሞች ብቻ ሲተርፉ ሌላው አለቀ።

ከሁለቱ አንድ በጣውላው ላይ ከሰባት ቀን መንሳፈፍ በኋላ «እግዚአብሔር ሆይ ሕይወቴ የተበላሸ መሆኑን አውቃለሁ፤ ለባለቤቴና ለልጆቼ ታማኝ አልነበርኩም ፤ የአንተን ፈቃድ ባውቀውም ግን አልኖርኩበትም ዛሬ ሕይወቴን ካተረፍክልኝ በሁሉ ነገር እታረማለሁ፤ አብልጬም...» እያለ ሳለ ጓደኛው ፀሎቱን አቋርጦ «ቆይ አትቸኩል አንድ መርከብ ከርቀት አይቻለሁ» ይለዋል።

እንዲህ ዐይነት ሰዎች በሕይወት ውስጥ ሁሌም ሊገጥሙን ይችላሉ፤ እነዚህ ንስሀን አቋራጮች ናቸው፤ የቀደመውን አጓጉል ሕይወት አኑዋሪዎች ናቸው፣ የተሻለውን ፅድቅ የሆነውን እንዳናደርግ በየምክንያቱ የሚያቋርጡን ናቸውና ከእነርሱ እንጠንቀቅ፤

***

ቤተሰብ ዘላቂነት ያለውን ስራ ለመስራተ የተዘጋጀ መሆኑን ከወዲሁ ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ በመጨረሻም ህፃናት ያቀረቡትን አቤቱታ አቀርባለሁ «ህፃናት ችግር ላይ ነን ሁለት ዓመት እስኪሞላን ድረስ ወላጆቻችን መራመድንና መናገርን ያለመታከት ያስተምሩናል፤ ከሁለት ዓመት ዕድሜያችን በኋላ ግን አርፈን እንድንቀመጥና ዝም አንድንል ያስገድዱናል» ብለዋል። ኋላ ላይ ተው ለማለት፤ ኋላ ላይ ዝም በሉ ማለት ላይ ትኩረት አድርገን ከኖርን ጥፋትን እናጭዳለን። ከዚህም የተነሳ ያለፍንበት ቀጣይነት እንዲኖረው በጥንቃቄ መስራትና መማር አለብን።

***

የሚገጥሙን የትኞቹንም ጉዳዮች ከራሳችን ተሞክሮ፣ ዕድገትና ልምድ ጋር ብቻ እያይዘን ለመተርጎም አንነሳ፣ ሰዎች ከምን አንፃር ተመለከቱት ብሎ «ለሁሉም ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው፤ በታክሲ ውስጥ የምናነባቸው ጥቅሶች ለዚህ ሁነኛ ተጠሪ ናቸው «ፍንዳታ ተሳፋሪን ከሁለት





ፌርማታ በላይ ልንወስድ አንገደድም፣ የሀበሻ ቀልድ ቀንድ አለው፣ ለሰው ቅን እንጂ ቅንቅን አትሁን፣ እንደጋዳፊ እንዳትዋረድ በቶሎ ውረድ፤» የመሰሉ አባባሎች የተሳፋሪን ማንነት ያላገናዘበ፣ መብትህን አላግባብ የነጠቀ «በማዝናናት ስም ያነወረ» ገለፃ ነው።

***

«የስጦታ ትርጉም ምንነቱን ያልተረዳ ሰው በምድር ካሉት ምስኪኖች የመጀመሪያው እሱ ብቻ ሊሆን ይችላል» ይባላል፤ ስጦታ ያለ ድካም ከሰጪው ቸርነት የተነሳ ለእኛ የሚሆን ሀብት ነው፤ አልከፈልንበትም፤ አልደከምንበትም፤ ከዚህም የተነሳ ሰጪውን በማመስገን ስጦታውን ደግሞ በጥንቃቄ በመያዝ ውበቱን መጠበቅ የተቀባይ አደራ ነው።

ምን ያልተሰጠን ነገር አለ? የምንተነፍሰው አየር፣ የምንራመድበት ምድር፣ የሚሞቀን ፀሐይ፣ ወቅቱን እየጠበቀ የሚመጣ ዝናብ፣ ወላጆቻችን፣ ልጆቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣ ይልቅኑ ከአብ የተሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የተቀበልነው ተፈጥሮአዊ ስጦታ፣ ያገኘነውን የፀጋ ስጦታ ሁሉ አክብሮ መያዝ በእነርሱም መጠቀም ተገቢ ነው።

# የምን ጎደሎነት

***

እርግጥ ነው ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ ያለ ሴት «ጎዶሎ» ነው ሙሉ መሆን ቢፈልግ ሚስት ታስፈልገዋለች፤ ለአቅመ ሔዋን የደረሰች «ሴትም» ሙሉ መሆን ብትፈልግ ወንድ ያስፈልጋታል፤ ይህ አያሻማም «ሁሉም ያግባ» ብዬ ቀስቃሽ ቃል ባላነሳም ለዚህ ንባብ ግን «ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለም። ስለዚህ ተስማሚና ረዳት ጓደኛ እፈጥራለሁ» (ዘፍ 2፡18) ያለው ጌታ ለጋብቻ መሰረት ባደረገው ዋና ጉዳይ ላይ እንምከር። አስቀድሞ ለጋብቻ የመግቢያ በር ስላልሆኑት ግን ነን ብለው ሊማርኩን ስለ ተዘጋጁት ጥቂት እንናበብ።

**አንዱ**፡- የማያምነውን (የማታምነውን) ለማግባት የሚደረግ ውስጣዊ ቅድመ ዝግጅት ነው።

«በውኑ ያምናሉ የተባሉ ሴቶች ወይም ወንዶች ለማመናቸው ምን መተማመኛ አለ? ከትናንት ወዲያ በመንፈስ የተቀጣጠለ ጎበዝ ዛሬ ተቃራኒውን ሕይወት በተግባሩና በቃሉ ካስመሰከረ፤ በትይዩ ትናንት ከትናንት ወዲያ ክርስቶስን እንደምመስል «እኔን ምሰሉ» ያለች ሴት ዛሬ ቀድሞም ልመዝናችሁ አደረኩት ስትል ብትሰማ፣ ከዚህም ችግር የተነሳ ከጌታ ጋር ያልተገናኘችውን፣ ያልተገናኘውን ማግባት ነውር የለውም በሚል ውሳኔም ክርስቲያኑ በተራ ሀሳብ ቢሞላ፣ ሌሎቹ ደግሞ «አስተሳሰባችን የሰፋ ይሁን ዘመናዊነትን እንከተል ፅንፈኛ አንሁን» ቢሉ 1ቆሮ 9፡5 ሆነ 2ቆሮ 6፡14 ም «እንደ የአካባቢው ሊተረጎም ይችላል» የሚል ማህበረሰብ ቢፈጠር፣ ድፍረቱም እስከ አሳምናለሁ ድረስ ገፍቶ ቢመጣ እና ተግባራዊ ቢሆን፤- የዚህ ውጤት በገደል አፋፍ ላይ ቤቱን እንደ





ሰራው ሰው መሆን ነው።

**ሁለት**፡- በሰው ግፊት አግብቶ መገኘት፤- ሰው ከሰው ጋር ነው የሚኖር በቤተሰቡ፤ በትምህርት ቤቱ፤ በሥራው ቦታ፤ በቤተክርስቲያኑ የሃሳብ፣ የእውቀት፣ የልምድ ልውውጥ በሚያውቀው መንገድና በማያውቀውም ጭምር ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ተሚጋች ሀሳብ ጣልቃ እየገባ፣ አልያም ጊዜ ተይዞለት የተቀራረቡ ወዳጃሞች ሴቶች ከሴቶች ጋር ወይም በተቃራኒው ወይም በድብልቁ ተገናኝተው ይመክራሉ፤ በውጤቱም «ቆሞ መቅረትን» ለመቅደም ወደ ሩጫው ሁሉም ገብቶ የያዘውን ይጠቀልላል።

**ሶስት**፡- በየአቅጣጫው ከየሰው ጋር ተረጋግታችሁ ጨዋታ ስትጀምሩ የበረታው የደከመውን አፅናንቶ ወይ አተካክዞ መጨረሻው ላይ ወይም ገና ከመነሻው «ችግር አለ» ይላችኋል፤ በቤት ችግር፣ በስራ ቦታ ችግር፣ በቤተክርስቲያን ችግር፣ በመንገድ ችግር፣ በየትም ችግር ራሱ የረገጣችሁት እግራችሁ ያረፈበትም ስፍራ ችግር! ችግር! ችግር!የሚል ድምፅ እስከሚያሰማችሁ ያደርሳችሁዋል። ከዚያ እንዴት እናስወግደው? ቀጣይ ጥያቄ ሆኖ ይቀጥላል። የዚህም ምላሽ ከትዳር ጋር ይያያዛል፤ የጋብቻ መስመርም ውስጥ ሳናስተውለው ይከተናል፤ እንጋባለን።

**አራተኛ**፡- «ጋብቻ እኮ ያስከብራል!አንቱ ያሰኛል» ለመሪነት ለመብቃት ሚስትወይም ባል አስብሎ ስፍራ የሚያሰጥ ይሆናል ምርጥ ምርጡን ለባለትዳሮች የሚያሰኝ መፈከር ያስወጣም ለዚህ ጋብቻ ተጠሪ ይሆናል።

**አምስተኛ**፡- በእመኘኝ አምናለሁ መሐላ ቢተኙ በኋላ መሐላው ድንገት ፈርሶ ቢነጋ ነህ ቢቀድ የህሊና ወቀሳቸው፤ ፀፀቱ፤ ይቅርታ መጠያየቁ መተፋፈሩ ንስሐ መግባቱ ሁሉም እንደ ተጠበቀ ይከተላል ውሎ አድሮ ደግሞ እርግዝናው ቢከተል ለዚህም መፍትሔው ወደ ጋብቻ ማቆብቆብ ይሆናል።

ምን ይደረግ ቀድሞም አብረው ታይተዋል ከዚህ የተነሳ ለዚህ ችግር በመፍትሔነቱ «እንጋባ፤ ሕይወቴን አበላሽተኸዋል ምንም አማራጭ የለኝም» ሌላው አብይ ጉዳይ ይሆናል ከነዚሁ ጋር ተያይዞ የቤተክርስቲያን ንፅህናም ጎድፏልና ስለዚህ ነገም ብትፋቱ ዛሬ ግን ተጋቡ መፍትሄ ሆኖ ይዘከራል።

**ስድስት**፡- ልጆችን ማግኘት ቀዳሚ አጀንዳ የሆነባቸው ሰዎች አሉ፤ እነርሱ በራሳቸው ሀይልና ጥረት ብቻ ልጅን ማግኘት ስለማይችሉ ባልን ያሰባሉ ሚስትንም። ለዚህም ጋብቻን ዋነኛውና ተጠሪ አድርገው ለትዳር (ለጋብቻ) በርን በመክፈት ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፤ ጋብቻ ለእነዚህ ሰዎች

ልጆችን ማፍራት በመውለድ ዘርን መቀጠል ነው፤ በመውለድ የራስን ምስል ማስተዋል፣ በመውለድ ውርስን ማስተላለፍ የሚለው ፍቺ ይጎላባቸዋል፤ በዚህ ጎዳና ላይ መሀንነት ከመጣ ጣጣው የበረታ ይሆናል።

እግዚአብሔር «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ» አለ እንጂ ይህን አስከትሎ የግድ ልጆችን ይወልዳሉ አላለም። የጋብቻ የመግቢያ በሩ ልጆችን ለመውለድ በሚል እውቀት ከተሾለከ ውጤቱ ዝቅተኛ ነው።

**ሰባት:-** ወጣቶች ወንጌል ለማድረስ ፈጣኖች ናቸው፤ እነርሱ እርስ በርስ ለመቀራረቡም እንደዚሁ፤ታዲያ ይተዋወቁና ልንጋባ ነው በማለት ፈተና ይሆናሉ፤ ቤት የላቸው ድስት የላቸው፤ ጥገኞች። ቋንቋቸው ግን በእምነት ይሆናል፤ በማለት እምነትን አስታከው ሁሉን አልሰማ ብለው ቢጋቡ ቀጥሎ የሚከተለው ጥጋብ ሳይሆን ረሀብ እራስን መቻል ሳይሆን ጥገኝነት ነው።

**ስምንት:-** የወደደ መውደዱን በሚከፍለው ዋጋ ይገልፃል የክርስቶስ ፍቅር ደሙን እስከ ማፍሰስ አድርሶት ሞትን አስቀምሶት ነው እወዳችኋለሁ ያለን። የጋብቻ ፍቅርም ይህንኑ ይጠይቃል ይህን መቅመስ ያልወደደ ባል ልሁን ባይ ወንድ ሚስት ልሁን ባይ ሴትም «ፍቅር ወደ አንቺ አልመራኝም ይልቅስ መንፈስ አስገድዶኝ እንጂ» ይላል፤ ትላለችም፤ በመገለጥ እና ራዕይ ስም «ባል ልሆን» ነው... ሚስት ልሆን» ነው አሰኝተው ወደ ጋብቻ ቢያስሮጡ፤- ነበዝ እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ይላል «መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ ጎልማሶቻችሁም ራዕይ ያያሉ» ያለው የኢዮኤል የትንቢት ቃል ለወንጌል ሩጫ መሆኑ ቀርቶ ለጋብቻ መለያ እንዴት ሆነ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

እግዚአብሔር ወንድና ሴትን አፍቃሪና ተፈቃሪ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል እንግዲያስ የሚወድ ከሀይሉ ከእውቀቱም ከጊዜውም ቆርሶ መስጠትን ሲጀምር ራሱን ሊሰጥ ሲቆርስ ያኔ ነው ፍቅር የሚገለጥ።

የቀደሙት ስምንቱም ለጋብቻ ሙሉዕነት መልስ የማይሰጡ ጎዶሎዎች ናቸው። እግዚአብሔር የማያምነውንና የማታምነውን እንድንጋባ፣ ወይም በግፊት ብቻ ተነሳስተን እንድንጋባ ወይም ቁሳዊ ችግራችንን ለመፍታት እንድንጋባ ወይም በጋብቻ ውስጥ አልፈን የክብርን ስፍራ ለመያዝ እንድንጋባ ወይም ለጋብቻ መሰረት የሆነው ፍቅር ፈፅሞ ሳይኖር የመጣን እርግዝና ለመሸፈን እንድንጋባ፣ አገልጋይ ስለሆንን ከዝሙት ጠንቅ ለመዳን እንድንጋባ፣ ልጆችን ለመውለድ እንድንጋባ፣ በሕልም፣ በራዕይ፤ በትንቢት በር ሾልከን እንድንጋባ ብሎ ጋብቻን አልፈጠረም።





ከላይ ያየናቸው ሁሉ የትዳር በር እኔው ነኝ ይሉናል መረጃዎቻቸውን እያቀረቡ እንኪያስ ለትዳር የመግቢያ በሩ እንደ ደህንነታችን አንድ ብቻ ከሆነ በሩ ፍቅር ነው። መውደድ ራስንም መስጠት ነው ቀዳሚው፤ ሌላው እንደ ሁኔታው ተከታይ ሊሆን ይችላል።

# ምን ፍከጋ ካግባ!

ቤተ ክርስቲያንን ከክርስቶስ ነጥሎ በብቻዋ ለማጤን ማሰብ ሚስትንም ከባልዋ ለይቶ ለማወቅ መጣር በውጤቱ ድካምን ማጨድ ይሆናል፤ ሁለቱም ላይነጣጠሉ አንድ ስለሆኑ፤ ይህን በየብቻው የነበረ የብርቱካንና የአናናስ ጭማቂ ወደ አንድ መጠጫ ተጋብቶ እንደተዋሀደ ያህል መቁጠር ተገቢ ነው፤ ማብራሪያዬን ከክርስቶስ ላድርግ፤ በጤንነቱ ሙሉ የሆነውን ኢየሱስን «ጨርቁን ሲጥል ትንሽ የቀረው እብድ» ብለውት ነበረ፤ «እውነትን እየገለፀ ከብርሀን ጋር ሲያገናኝ በሃሰተኛ መስካሪ ምላስ «ቀጣፊ የሐሰት ቁንጮም» ተብሏል። በአጋንንት ስልጣን ስር የነበሩትን ሲፈታ «ብኤልዜቡል» እንደረዳው ተነግሮበታል። አልፎ ተርፎ በሞቱና በትንሳኤው ኃይል ላይ ተነሳስተው ደቀመዛሙርቱ ሌቦች በመሆናቸው አስከሬኑን ሰርቀው ጠፉ እስከ ማለት ደርሰዋል።

ግና ይህ ሁሉ በኢየሱስ ላይ ሲፈራረቅ ቅዱስ መጽሀፍ እንደሚል ስለሙብቱ ሳይከራከር፣ ሙግት ሳይጭር ፤ ወደ ፍርድ ቤት ሳያዘግም፤ በምትኩ ትህትና የተሞላበትን ከሰዎች ጋር የመገናኘት አገልግሎቱን፡- ማስተማሩ፣ መፈወሱን፤ ቀጠለ፤ ከመጣበት ዓላማ ወደ ኋላ የሚጎትተውን ሳንካ በመናቅ ወደ ፊት አለ!ኢየሱስ የሩቅ ግቡ ምን ቢሆን ነው ይህንን ለመሆን የፈቀደው? ለሰው ሰው ሆኖ እስከ መምጣትስ ምን አዘለቀው? ምላሹ በፍቅሩ ቤተክርስቲያንን ለራሱ ሊያደርግ ወስኖ ነበርና ነው።

«የወደደ መውደዱን በሚከፍለው ዋጋ ይገልፃል» ፍቅርና መስዋዕትነትም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ሆነውይገኛሉ? እንኪያስ ከዚህ ተነስተን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥረት ፍሬያማ መሆኑን በዐይናችን ዐይተናል፤ ዳሰንም አረጋግጠናል።





ፍቅር እስከሞት እንዳደረሰው ሲነግረን! እንደወደደን ሲያበስረን ሳናቅማማ ለእርሱ ምርኮኞች ሆንን፤ ቤተክርስቲያኑ ከዚህ የተነሳ ስለ ክርስቶስ መናገር ብቸኛው መገለጫዋ ሆነ ይህም አልለያይ ብሎ ተዋሀደ። ታዲያ ስለዚህ ውህደት ቀድሞ ደራሹ በተግባር የተገለፀው መስዋዕትነትን የጠየቀው የክርስቶስ ፍቅር መሆኑ እንዳይዘነጋ።

ሚስትንም ከባልዋ ለይቶ ለማወቅ መጣር ውጤቱ ድካምን ማጨድ ነው፤ ይህንንም ያስባለን ምሳሌ የተወልን ኢየሱስ ክርሰቶስ ነው፤ እንግዲህ የደረሰ ወንድ ባል ሳይሰኝ፣ ሴትም ሚስት ሳትሆን ከጋብቻ በፊት **ማቀጥቀጥ ስለሚገባው የፍቅር የመስዋዕትነት ምግነትን** አብረን እንመልከት። ልክ እንደ ክርስቶስ።

ወንድ ወዳጅ ሴትም ተወዳጅ ሆና ወንድ ወደ ማስተዋል አምጪ ቀስቃሽ ሴትም አስተዋይ ሆና ተቀስቃሽ መሆኗን በተግባር ብቻ መግለፅ ይቻላል።

ግብሩ አልፎ አልፎ ከሴት ወደ ወንድ ሊሆን ቢችልም አብዛኛውን ድርሻ ወስዶ ራሱን በዚህ የሚገልፀው ወንድ ነው፤ የሩቅ ግቡ ጋብቻ የሆነ ይህ ሰው ከወዲሁ ከብዙ ሴቶች መካከል አንዷን ይወዳል፤ ለመውደዱ መነሻ ምክንያት ልጅቱን ማየቱ ደግሞም በማታስተውለውመንገድ ሁሉ መሰለሉም ነው፤ ታዲያ ይህቺን ልጅ የራሱ እንድትሆን የሚያበቃለት የልብ ወዳጁ፣ ጓደኛ ወይም ወላጆቹ ሳይሆኑ የሚያበቁለት ጊዜና ራሱ ይሆናሉ።

ጊዜ ስል «ወድጄሻለሁ» ብሎ በአንድ ጀምበር አይቶ የሚተነፍሰውን ቃል ሳይሆን ጠብ፣ ጠብ፣ ጠብ እያለ አለትን ሊሸረሽር እንደቻለ ውሃ በቀን በቀን የእወድሻለሁ ቃል ከአንደበቱ ሳይሰማ ተግባሩ «ምን አለ እሱን የመሰለ ባል ጌታ ቢሰጠኝ» ለሚያሰኝ ምኞት የሚያበቃውን ጊዜ ሲሆን ራሱም ሲባል እሱኑ ራሱኑ በብቻ ማለት ነው። እሱነቱን ለነገ ብሎ ሳይቆጥብ ከመንፈሳዊ ነገሩ፣ ከጊዜው፣ ከእውቀቱ፣ ከምስኪንነቱንም ጨምሮ ለሩቅ ግቡ ለእሷ ዛሬም ነገም ሁሌም ሊያደርገው፤ ቅር ሳይሰኝ ሕይወቱን ሲቆርስ ሲለግሳት ተወዳጅነቷ እየጎላ ተቀስቃሽነቷ እየደመቀ ይመጣና «እወድሻለሁ ላገባሽ እቅጃለሁ»ን የምስራች ቃል ሊያስጠብቃት ይጀምራል፤ የዘገየ ከመሰላትም «እወድሃለሁ ለምን ለመጋባት እናስብም» እስክትለው ያሳስባታል፤ ይህ በጤንነት የተሞላ ትክክለኛ ጥበቃ እና ውሳኔ ነው።

ልክ ኢየሱስክርስቶስ ፍቅርና መስዋዕትነትን ሳይነጣጥል ወደ እኛ ሲመጣ ተቀስቅሰን ነቅተን ወደ እርሱ እንደተሰበሰብን ሁሉ የወንድም ፍቅር እኒህን አሟልቶ ወደ ሴቲቱ ሲደርስ እየነቃች ትመጣለች ለ«እወድሻለሁ ስለ ጋብቻስ ምን ታስቢያለሽን?» ጥያቄ መልስ ለመስጠት ብዙ ፆም ፀሎት አታበዛም ምርኮኛ ትሆናለች፤ ፈጠን ብላ።

በዚህ ጎዳና ላይ ተራምዶ የመጣ ፍቅር በጋብቻም ውስጥ እልፎ አንድ ስጋ አድርጎ መፍሰሱን ይቀጥላል ይህን ግዜ ነው ተዋህደዋልና ሊለያዩ አይችሉም የሚሰኘው የትኛው የብርቱካን ፈሳሽ የትኛው የአናናስ መሆኑ የማይለየው።

ግና አሁንስ ቢሆን በማግባት ውስጥ በዋናነት ምንን ለማግኘት ነው መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ፍቅር ያስፈለገው? መረዳዳትና መተሳሰብን ለማግኘት ወይስ በችግርና በመከራ አብሮ ማለፍን? ወይስ ብቸኝነትን ለመግደል አልያም በህብረተሰቡ ውስጥ «አንቱ» ለመሰኘት? ወይስ የብዙ ተባዙን አምላካዊ ትዕዛዝ ለመፈፀም? በከፊል ሁሉም መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በሙሉነት ግን ሰው በራሱ ፈፅሞ ሊያሟላው የማይችል ከተጠቀሱት ውስጥ ከተገኘ ለእርሱ ቅድሚያን በመስጠት የተቀሩትን በእርሱ ጥላ ስር ለማሳደር መቻል ብልህነት ነው።

መረዳዳትንና መተሳሰብን ጋብቻ ውስጥ ለማግኘት የሚችለው ቀዳሚ ቢሆን ይህ በግላዊ ኑሮና በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ በብቻ የምናከናውናቸው ጉዳዮች እየጠበቡ የሰው እርዳታን የሚጠይቁ የእቅም፣ የአስተሳሰብ፣ የመንፈሳዊ ነገሮች መፈላለግን አቅም ካጣው ሰው ሲመጡ መፍትሄ ሆኖ የሚመጣው በሌላ መረዳትና መታሰብ መታገዝም ነው። ይህንን ደግሞ ለማከናወን ከሚስት ወይም ከባል ሌላ የድጋፍ ፈላጊው ጓደኛ፣ ወላጅ፣ ምክር ሰጪ ሰው ወይም በተዘጋጁት የእውቀት መድብሎች በመታገዝ እና ሴቲቱን ወይም ሰውየውን ወደ ጋብቻ ሳያመጡ ከወዲሁ በእነዚህ ሊረዱ ይችላሉ፤ በጋብቻ ሕይወትም ውስጥ ከሚስቲቱ ወይም ከባልየው በተጨማሪ ሆነው ሊደግፉ ይችላሉ፤ ከዚህ የተነሳ ሰው በራሱ ፈፅሞ ሊያሟላው የማይችለው ችግር ተደርጎ ግንዛቤ ውስጥ አይገባም።

ችግርንና ዘላቂ መከራን አብሮ ለማሳለፍ ማግባት የሚለው ቅድሚያ ሊሰጠው እንደማይገባ ኢዮብን በማስተዋል መግታት ይቻላል የሚስት አብራ መኖር ትርጉም ሳይሰጥ ቀርቷልና መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ቁመት በማደግና በእግዚአብሔር ፀጋ፣ ይህን መቋቋም እንደሚቻል ገልፃል። በሌሎችም ሰዎች ድጋፍ ችግርንና መከራን መግፋትና ማራቅ እንደሚቻል አሳውቋል።

ብቸኝነትን ለመግደል ማግባት የሚለውም:- «ሰው ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም» የሚለው መለኮታዊ ቃል ተጠሪ ቢሆንለትም እርግጥም ደግሞ ሰው ብቻውን ዘላቂ ዕድሜውን መግፋቱ ተገቢ አይደለም መባሉ እውነት ቢሆንም ግን ሰው ከሰው ጋር እየኖረ፣ ባል በሚስቱ እቅፍ ሚስትም በባሏ ውስጥ ሳለችም እልፎ እልፎ የብቸኝነትና የነጠላነት ስሜት ሲመጣ ይስተዋላል፤ ባልና ሚስት በአንድ ጣራ ስር እየኖሩ አካልን እያሳዩ «አጠገብህ ነኝ እያሰኙ» ግን በድን ከሆኑ እሱን ለመግደል መጋባት አያስኬድም፤ ይልቅ ብቸንነት በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ለዘላለም መኖር ሊረታ ይችላል።





ከሕብረተሰቡ «አንቱታን» ለማግኘት ማግባት ሌላው ተነሺ ነጥብ ነው፤ ለመጋባት በጋብቻ ሕይወት ያለፉ በሕብረተሰቡ ዓይን ተቀባይነትን አግኝተው ከላጤዎቹ ይልቅ ቅድሚያንና የከበሬታን ስፍራ ከተሰጣቸው የዚያ ሕይወት ተካፋይ ለመሆን ማግባት መልካም ይሆናል፤ ግና ሰውን «አንቱ» የሚያሰኙ ከመጋባት ሕይወት ሌላ «አንቱ» ሊያሰኙ የሚችሉ መገለጫዎች «እኛም አለን» ይላሉ ካሉ ደግሞ «አንቱ» ለመሰኘት ማግባት ሚዛን ደፊ አይሆንም።

የብዙ ተባዙን አምላካዊ ትዕዛዝ ለመፈፀም ማግባት ደግሞ:- በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ሊኖር የሚገባ ጠንካራ ጉዳይ ነው፤ ይህ ግን ሁልጊዜ አይሆንም መሆንነት እየተከሰተ ሳይባዙ በትዳር መዝለቅ ይኖራል ይህ ደግሞ ለመጋባት የቀደምትነቱን ስፍራ ያሳጣዋል።

አንድ ስጋ ለመሆን ማግባት ግን:- ቅድሚያ የሚሰጠው ጃን ጥላ ነው ከላይ ሲዘረዘሩ የቆዩት በዚህ ትልቅ ጥላ ስር በማደር ጋብቻን የሚያደራጁ ደጀኖች ናቸው፤ ይህንኑ በእግዚአብሔር ቃልና ከሕብረተሰቡ ማህበራዊ ኑሮ አኳያ ማጠናከር ይቻላል፤ በራስ ግላዊ ጥረት፣ በወዳጆች አይዞህ ባይነት፣ በብዙ ዕውቀት፣ ሊፋታ የማይችል ነገር፤ **ራስን በራስ መዳር አለመቻል** ነው፤ ይህ ሰውን ጎዶሎ ያደርገዋል፤ እግዚአብሔር ግን ጎድሎ ሆኖ እንዲቀር አልፈቀደም የሚሞላለት ከእርሱ አካል ውጭ ከሌላ ዘንድ አኖረ፤ ያንንም ድንቅ ስራ እግዚአብሔር ራሱ አዘጋጀ፤ ዝግጅቱንም በሰው ዘር ጅማሬ ታሪክ ላይ በመገኘት ወንድን ከሴት ጋር በማጋባት ጋብቻን አቋቋመ፤ አንድ ስጋም ሁኑ አለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በፍቅር በር በመግባት ጎዶሎነት በጋብቻ ሕይወት ውጤታማ ሆነ። ይህንንም በተከታዩ ማስታወሻ እንጠቅልል

**ሀ.** እግዚአብሔር በዘፍጥረት መፅሀፍ ስለዚህ ጃንጥላ ሲናገር፤- «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ፤ አዳምና ሚስቱም ሁለቱም እራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር» አለ፤ እግዚአብሔር የወል የሆነ ስም ተጠቀመ፤ ሰው፤ ይህም መልዕክቱ ለሁሉ እንዲደርስ አዳምን በራሱ ሚስት መሆን አለመቻሉን ሔዋንንም በራሷ ባል መሆን አለመቻሏን አስረግጦ ገለፀ፤ ይህን ማድረግ ባለመቻላቸው አንድ ስጋ በመሆን አዳም በሴቲቱ በኩል እንዲያድር ሔዋንም በወንዱ ሕይወት ውስጥ በአካል አንድነት በኩል እንድታድር ተራክቦ ስጋ አስፈለገ።።

**ለ.** ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ስለዚህ ጃንጥላ ሲናገር ፈሪሳውያን ስለ ፍቺ ሲጠይቁት እርሱ ማግባትን አስመልክቶ የጋብቻን ዋና ክፍል ገለፀ፤ የዘፍጥረትንም ሃሳብ አስከትሎ ጎዶሎነትን ለመሙላት ሁሉም ሊያገባ ይገባዋልን አጠነከረ፤ የማያገባ ቢገኝ ምክንያቱ የጎዶሎነት ፍላጎትን የሚያነሳሳለት ዘር ወይም አካል ከመነሻው የተነፈገ ከሆነ እርሱ በዚህ አይጠየቅም በዚህ እውነቱ ላይ ሰው ሰልቧቸው ጎዶሎነታቸውን የተረዱትንም ጨምሯል።

ስለ መንግስተ ሰማይ ሲሉ ዘርና የአካል ብልት ኖሯቸው ፍላጎቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በራሳቸው ቁርጠኝነት ራሳቸውን የተቋቋሙትንም ያለ ማግባት መብቶቻቸውን ጠብቆታል «ሊቀበል የሚችል ብቻ ይቀበለው» ብሎ፤ ይህን ሳልሻገር በዚህ «የስልብነት ዐይነት» ውስጥ ሰዎች ለመንግስተ ሰማይ ሲሉ ሳይሆን ግን አልፎ አልፎ ዘርን የሚያበላሹ ጠንቆች (በሽታዎች) ለስጋ አንድነት የሚረዳቸውን ሀይል እና ጥንካሬ በማሳጣት «የአካል ብልትን ፉዞ» እንዲሆን በሚያደርግ በሽታ መጠቃት ይኖራል፤ ይህ በዘላቂነት ሳይታረም ከተከሰተ ራስን እንደ ስልብ በመቁጠር ወደ ጋብቻ አለመምጣት ተገቢ ነው። ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ግን ማግባት በራስ ዘንድ የሌለውን ለመሙላት እግዚአብሔር ያዘጋጀው ተአምራዊ ተግባር ነው ወሲባዊ ግንኙነት።

**ሐ.** ጳውሎስ ስለዚህ ጃንጥላ ሲናገር *«በዝሙት ኃጢአት ላለመውደቅ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው እያንዳንዲዋም ሴት የራስዋ ባል ይኑራት...ራሳችሁን መቆጣጠር አቅቶአችሁ ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ አብራችሁ ሁኑ»* (1ቆሮ 7:5) በተጨማሪም «በሥጋ ምኞት ከመቃጠል ይልቅ ማግባት የተሻለ ነው» (1ቆሮ 7:9) ደግሞም

*«አንድ ሰው... እጮኛው ለጋብቻ የደረሰች ብትሆንና የስጋ ፍትወትን ለመቆጣጠር ባለመቻሉ ሊያገባት ቢያስብ ያግባት...»* (1ቆሮ 1:36) ይላል።

የእነዚህ ጥቅሶች ሙሉ ሀሳብ ጨምቀን ብናወጣ ሊለን የወደደው «ማግባት ያስፈለገው በስጋ አንድነት ጎዶሎነታችንን ሙሉ ለማድረግ» የሚል ነው።

**መ.** በውስጡ ያለንበት ሕብረተሰብ ስለ ጃን ጥላው የሚለው ደግሞ ሰዎች የእግዚአብሔርን አሳብ ባለመረዳት ወይም ተረድተው ለገዛ ፈቃዳቸው በመገዛት ለፍትወት ስጋ ሲጣደፍና በተገቢው መንገድ ሳያልፍ የጋብቻን ህግ ሲጥሱ፣ የፍቅር መስዋዕትነትን ሲሸሩና የማግባት ፍቺን ሲያጠፉ መታየቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለ መሰረታዊ ችግር ነው፤ ይህም ቢሆን በብዙዎቹ ሕይወት ውስጥ ግን መቀራረብ፣ መዋደድ፣ በመዋደድ መተጫጨት፣ እስከትሎም ወደ ጋብቻ የመድረሳቸው ሚስጥር በሰውሁሉ ዘንድ የተገኘውን ጉድለት ለመሙላት ሲባል ነው።

እንኪያስ የጃንጥላውን (የቀዳሚውን) ጉዳይ ስንጠቀልል እግዚአብሔር በወንድና በሴት ህይወት ውስጥ ጠንካራ ፆታዊ መፈላለግን አስቀመጠ፤ ይህንንም ፍላጎት በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ፈፀመው፤ ከዚህም የተነሳ ፍቺን ፈፅሞ ተቃወመ፤ እንኪያስ በደጅንነት ያነሳናቸውን ነጥቦች በዚህ ጃንጥላ ስር ሊተዳደሩ ይችላሉ፤ እርግጥ ጃንጥላውን ለማቅለል በሰዶማዊት እና በመሰል መንገዶች ይህን ጉድለት መፈፀም ይቻላል የሚሉ መኖራቸውን እናጣም ይህ ግን እመፀኝነት እና በእግዚአብሔር አምሳል ሊፈጠሩ ያሉትን የሰው ልጆች ለማቋረጥ የሚደረግ ስራ ስለሆነ አያዋጣም።



# ካልተጣጣሙ ቢፋቱስ?

በድህረ ጋብቻ ሕይወት ውስጥ ሊታሰብባቸው ከሚገባቸው መሰረታዊ ጭብጦች መካከል አንዱ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ መነጋገር ነው።

***

እግዚአብሔር በወንድና በሴት ሕይወት ውስጥ ጠንካራ ፆታዊ መፈላለግን አስቀመጠ፤ መፈላለጉንም በጋብቻ ሕይወት ፈፀመው፤ ጋብቻ ሁለቱን አንድ ስጋ ስላደረገ ፍቺን ፈፅሞ ተቃወመ፤ አንድ ስጋ የመሆን ምስጢርንም ለመጋባት ዋነኛ ምክንያት ሆነ።

የስጋ አንድነት ወይም የስጋ ተራክቦ ግራ ቀኙን ካልቃኙት ምንም መፍትሔ የላቸውም የሚያሰኙ ችግሮችን ሊፈጥር መቻሉን ማጤን ግን ተገቢ ነው።

**አንደኛው:-** ጠንካራ ፆታዊ መፈላለግ ዕድሜ ሲገፋ ወይም ከተጋቢዎቹ አንድ በበሽታ ተጠቅቶ ሲደከም አቅሙ ቀዝቀዝ ሊል ይችላል። በዚህ ወቅት ተመስርቶ የነበረ ጋብቻ ምን ይሆናል? የሚል ነው፤ ለዚህ ፈጣኑ ምላሽ መፋታት የሚል አይደለም። እግዚአብሔር አዋህዶ አንድ ያደረገውን የዕድሜ መግፋትና በሽታ ሊለየው ስለማይችል ይልቁኑ በዚህ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ ትዳር ዕድሜው በረዘመ ቁጥር መረዳዳቱና መተሳሰቡ በሁሉም አቅጣጫ እያደገ የተግባቦቱ መጠን በመንፈሳዊ፣ በማህበራዊ፣ በአእምሮአዊ፣ በስሜታዊ እና በአካላዊ ነክ ጉዳዮች ሁሉ ላይ የተገለጠ ስለሚሆን በተጋቢዎቹ መካከል ያልተረበሸ አንድነት ይኖራል።(1ቆሮ 13:4-8)

**ሁለተኛው:-** *የሥጋ አንድነት ለማግባት ዋንኛው ምክንያት ከሆነ የተጫጩ ወይም ለጋብቻ*

ቅድመ ዝግጅት የሚያደርጉ ወጣቶች ዘላቂ የትዳር ሕይወታቸውን ከመጀመራቸው በፊት ካላቸው ፆታዊ መፈላለግ የተነሳ እና በኋላም በኑሮ ውስጥ የማያግባባቸው የግንኙነት ችግር እንዳይመጣ ከወዲሁ ሩካቤ ስጋ መፈፀም አይገባቸውም ወይ? የሚል ፈተና ሊቀርብ ይችላል፤ ጥያቄውን በብቻው አይተን እንመልስ ከተባለ አዎ ተገቢ ነው የሚያሰኝ ምላሽ ላይ እንደርስ ይሆናል፤ ቅኝት የሞላው ተገቢው መልስ ግን አይደለም የሚል ነው፡- ያልሆነበት ምክንያት ደግሞ፡-

**ሀ.** ምርጫችን ትክክለኛ ወንድ ወይም ሴት መሆኑን መሆኗን ከወዲሁ ካረጋገጥን በመረጥነው/በወደድነው ሰው ሕይወት ውስጥ እርስ በርሳችን ያዋደደን የፍቅር ባህርይ የማይታገስ፣ ተስገብጋቢ፣ ተጠራጣሪ፣ ሥርዓተ ቢስ ባለመሆኑ ይኸው ፍቅር በሁለቱ መካከል በእርግጥ ካለ ተጋቢዎቹ ሁሉን በቅደም ተከተሉ ያደርጉታል፤ በሰዎች ሁሉ ዘንድ እንዲታይ እግዚአብሔር የተወልን የፍቅር ባህርይ ይህን እንድንሆን ያስገድደናል፤ የግዴታ ደንቡም ከጋብቻ በፊት የስጋ ተራክቦ ዝሙት መሆኑን አስረግጦ ማሳወቅ ነው።

**ለ.** እግዚአብሔር ከነርሱ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አሟልተው በተመራረጡ ተጫጪዎች ሕይወት ውስጥ የስጋ አንድነት በጋብቻ ውስጥ የሚያመጣው ቋሚ ጭብጥ ተራክቦ መልካም መሆኑ ነው (ዘፍ 1፡31) እግዚአብሔር መልካም፡ መልካም፤ መልካም ሲል አምስት ቀናትን ከርሞ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ነው እጅግ መልካም ነበረ ያለው። ይህ መልካምነት በወቅቱ የሚፈፀም ፆታዊ መፈላለግና በስጋ አንድነት ውስጥ የሚገኘውንም ሕይወት ይጨምራል።

**ሐ.** አንዳንዴ የተዋደዱ ሁሉ አይፋቀሩም የተጫጩም የማይጋቡበት ጊዜ አለ በሌላም ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የስጋ ተራክቦ ጉዳቱ ሚዛን የደፋ መሆኑን ማወቅ ራስን በመቻል ባልተደራጁ ተጫጪዎች ሕይወት ውስጥ ተራክበው ልጅን ያመጣል፤ ለችግር የተጋለጠን ሰው፤ በወላጅ ሕይወት ውስጥ ደግሞ የህገ ወጥነት ስሜትን ከወንዱ በበለጠ በሴቷ ላይ ይፈጥራል፤ እርግጥ ወንድየውም ቢሆን ከዚህ መንገዱ የሚተርፈው ምንም የለም፤ ይልቁኑ ስግብግብ ያልሆነውን ፍቅር ተስገብጋቢ በማድረግ የራስን ፍላጎት ቢያሟሉበት የተዋደዱት ለኋላ ለነገ ያስቀሩት ምንም ነገር ስለማይኖር መተያየታቸው ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ወደ ሌላ ለመዞርና «ስንጀምርም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልነበረ ታውቆኛል» ለማለት ተሽቀዳዳሚ በመሆን የወደፊቱን የጋብቻ ሕይወት ተረት አድርጎ ያስቀረዋል።

ከእነዚህም በበለጠ እግዚአብሔር «ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም... ሰውነታችን ለጌታ ኢየሱስ፤- ጌታ ኢየሱስም





ለሰውነታችን ስለሆነ ሰውነታችንን ለዝሙት ማዋል አይገባንም» (1ቆሮ 6፡13, 19) አለ። ይህ እውነት በሰውነታችን ላይ የእኛ ፈቃድና ሃሳብ በብቻው ሊሰለጥንበት እንደማይገባ ያስረዳናል፤ በምትኩ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ብልቶቻችን ለተቀደሰ ተግባር በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ብቻ መዋል እንዳለባቸው ይገልፃል። ከዚያ ውጭ ዝሙት ነው፤ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን መልካም ዕቅድ መቃወም ነው፤ እንኪያስ እነኚህ ያነሳኋቸው ሁሉም ለመግባባትም ሆነ (ለመጣጣም) ወይም ለሌላ አላማ የስጋ ተራክቦ ከጋብቻ በፊት ክልክል መሆኑን ያፀናሉ በምትኩ በጋብቻ ጅምር ውስጥ የማያግባባ «ችግር» ቢከሰት በሁሉ አቅጣጫ በማቆጥቆጥ ላይ ያለውን መግባባት በማሳደግ መርታት ይቻላል።

**ሶስተኛው፡-** የስጋ አንድነት በትክክለኛው መስመር በጋብቻ ተፈፃሚነት ኖሮት ባልና ሚስት በትዳር ሕይወት እየተመላለሱ በመሐከላቸው አለመግባባት ነግሶ ንትርክና ብጥብጥ፣ ኩርፊና ዝምታ፣ በአንድ ቤት ስር በአንድ የመኝታ ስፍራ እያደሩ የተለያዩ የሚሆኑበት ጊዜ ቢበዛ የዚህ ችግር አብይ ምክንያት ደግሞ በስጋ አንድነት አለመግባባት ቢሆን የእነዚህ ተጋቢዎች የወደፊት ተስፋ አሁንም ፍቺ ሳይሆን አብሮ መዝለቅ ነው። መዝለቅ እንዴት? እኛ በእኛነታችን ምክንያት ያበላሸነውን በማረም ችግሩን መርታት ቀዳሚው መፍትሄ ነው። ለዚህ ገለፃ የተጋቡ ሰዎችን በተመለከተ የገጠማቸውን ችግር እና መፍትሄያቸውን እናመላከት።

**ሀ.** ብዙ ጊዜ የስጋ አንድነት ከመፈፀሙ በፊት ሊሆኑ የሚገባቸውን ቅድመ ዝግጅቶች መተው ችግር ያመጠል፡፡ አንዱ ሁነኛ ምሳሌ እናንሳ ወደ ጫጉላ ቤት ሚዜዎች ሙሽሮችን ከሸኙ በኋላ ሙሽሪት ወደ መታጠቢያ ቤት ገብታ ትፀዳዳለች፤ በአእምሮዋ «ሕልምና እውን ምን አይነት መጣጣም እንዳላቸው እያሰበችና ከባልዋ ጋር የሚኖራትን የፍቅር መጣጣም እያሰላች፤ ለድርጊቱም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሊዛመድ የሚችልላትን ጥቅስ እየፈተሸች ተውባ ትጨርሳለች፤ ከዚያም ግር ባለ መንፈስ ከመታጠቢያ ክፍሏ ስትወጣ ሙሽራ (ባል) ደግሞ ዘገየች በሚል መንፈስ የድርጊት ሰው ለመሆን ተመቻችቶ ያደፍጣል፤ ዐይኖቹ ከበሩ እንቅስቃሴ ጋ እሷን በመጠበቅ ተግተዋል፤ እናም ወጣ እንዳለች ተቀበላት ከዚያም ለእንቅልፍ አልዘገየም አሸለበ ተኛ እስከረፋዱ ድረስ፤ ይህ ለእሱ ስግብግብ ስሜቱን ማርካት ቢሆንም ለሙሽሪት ግን «መደፈር ነው» መብቷን መግፈፍ የዚህ አይነቱ ገጠመኝ በተጋቢዎች መካከል በድግግም ሊመጣ ቢችል የሴቲቱ የኋላ ፍላጎት ፍቺን መናፈቅ ሊሆን ይችላል፤ ለዚህ ግን መፍትሔው መግባባት ነው፤ እርስ በርስ መነጋገር መመካከር።

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ወሲብ ትዳርን ለማጣፈጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከድርሻው ዋንኛው የስጋ አንድነት ከመፈፀሙ በፊት ሊሆን የሚገባቸውን ቅድመ ዝግጅቶችን ጠንቅቆ ማወቅ እርሱንም መለማመድ ነው። ሚስት የስሜት፤ የእውቀት ሁሉ ባለቤት ነች፤ ከዚህም የተነሳ አነሳሽ ተግባሮችን ማስቀደም ተገቢ ነው። ለምሳሌ፡-

ሀ. ነፃ ና የተፍታታ የመዝናናት ስሜትን በመፍጠር በአካል መቀራረብ፤ መደናነቅ፣ ፍቅርን በቃላት መግለጥ፤ ይህን ባል ሚስትን ካመቻቸ (አንዳንዴ ሚስትም ልታመቻቸው ትችላለች) በኋላ «እጅግ መልካም ነበረ» እርግጥም ነው፤ ይሰኛል።

ለ. አንዳንዴ የስጋ አንድነትን በመፈፀም ዝግጅት ላይ ባሎች ወቅቱ ሳይደርስ ዘራቸው ለመፈትለክ ይጣደፋል፤ ይህ በወንዶቹ በድግግም ቢከሰት በግላዊ ሕይወታቸው ውጣ ውረድን ይፈጥራል፤ ፍርሐትን፤ ጭንቀትን ወይም ያለመብቃትን ክፉ ስሜትን ያስተናግዳል።

ይህ ግን ለረዥም ቀናት የስጋ አንድነት ሳይፈፀም ቆይቶ ሊጀመር ሲል ሊሆን ይችላል፣ በድንግልና ሕይወት ኑሮ ለግንኙነት አዲስ ሲኮን ከግንኙነት ዕለት ጀምሮ ለጥቂት ወራት በድግግም ሊገጥም ይችላል፣ ለሚስቱ ያለው ታማኝነት በወንጀለኝነት ስሜት ተውጦ የቀድሞውን በደሉን እያሰበ ለመገናኘት ሲዘጋጅ ይህ ሊገጥመው ይችላል፣ ሚስትንም በስሜት የተነሳሽነት መዘግየት የችግሩ መገለጫ ሊሆን ይችላል ይህን ደግሞ መርታት የሚቻለው ተቃራኒውን በመኖር ነው።

ከምንም በላይ የሚወዳት ሚስቱ የምትወስደው የፍቅር እርምጃ ችግሩን ቀላል ያደርገዋል።

ሐ. በስጋ አንድነት ዝግጅት ላይ የወንዱ ስሜት መድከም፤ ይህ አልፎ አልፎ ከአስር ባሎች በአንዱ ላይ ሊከሰት ይችላል፤ በሴቶችም ሕይወት ውስጥ በሌላ ገፅታው የበረዶ ያህል በመቀዝቀዝ፤ ምላሽ ቢስነት ሊከሰት ይችላል፤ ይህም:-

ጥንካሬን በምንመገበው ተመጣጣኝ ምግብ በማደርጀት፣ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ የአልኮል ሱሰኝነት ካለ ከእነአካቴው በመተው፣ አስተሳሰብን በመጫን በነፃነት እንዳናስብና እንዳንኖር የሚያደርግ የሁል ጊዜ ሸክምን ቀስ በቀስ በማስወገድ፣ የጋብቻ አማካሪዎችንና ባለሙያ ሐኪሞችን በማማከር፣ እንዲሁም ችግርን አፍኖ ለግንኙነት ፍላጎት እንደሌለው ሰው ለማስመሰል መሞከርን በመተው፣ የአልጋ ላይ ጨዋታዎችን መንፈሳዊነት እንደሌላቸው መቁጠርን በማስወገድ በዋናነት ሚስትን የጉዳዩ ተካፋይ በማድረግ ችግርን መርታት ይቻላል።

መ. በስጋ አንድነት ዝግጅትም ሆነ ተግባር ላይ የተሸሸጉ «ስውር ፍርሐቶች»:- ራሳቸውን ሲገልጡ የሚመጣ ችግር ለምሳሌ ወንድየው ባለቤቱን ቅር እንደሚያሰኝ ገና ከትጭጭቱ ጀምሮ ይህንኑ ቢያብሰለስል ሴቲቱም ባሌን አላስደስተውም በሚል ስጋትን በውስጧ የማንገስ ድብቅ ፍርሀት ቢኖራት ይህም በግንኙነት ላይ ችግርን ቢፈጥር መፍትሔው መነሻው ምን ይሆን ብሎ መመርመር ተገቢ ነው። የዚህ መሰል ችግር በአብዛኛው ምንጫቸው በድግግም የምንሰማቸው፣ የምናነባቸውእና የምናያቸው ግነትን የተሞሉ ከገሀድ እውነታ የሸሹ ትረካዎች (ተረቶች) ንባቦችና ፊልሞችን አሜን





ብሎ ልክ ነው ብሎ ከመቀበል ይመጣል፤ ይልቁኑ የአንድ ለአንድን ጋብቻ ካቀደው ከእግዚአብሔር ሃሳብ አኳያ ሳይለያዩ አንድ አድርጎ በሚያዋህዳቸው ባልና ሚስት ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ይህን አጓጉል አልፈጠረም። እኛው ፈጠርነው እንጂ ይህ ከሆነስ ስውር የፍርሐት ስጋታችንን እያወጣን ያለመታሰቢያ እናስቀራቸው።

ሠ. በስጋ አንድነት ጊዜ የተረጋጋ ስፍራና ሁኔታ ማጣት በባልና ሚስት ሕይወት ውስጥ ስጋትና ጭንቀት በመፍጠር ችግር ሊያመጣም ይችላል፤ ይህም በድግግም በተጋቢዎች ሕይወት ውስጥ ሊከሰት ይችላል፤ ለዚህ መፍትሔው ባልና ሚስቱ ችሎታቸውን ተጠቅመው ስፍራውንና ሁኔታውን በማመቻቸት ችግሩን ማቅለል ነው።

እንግዲህ በሶስት ተከፍለው የተነሱት ችግሮች እነህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፤- ችግር አይጠፋም ሞልቷልም፤ ግን ተጫጪዎችም ሆኑ ባለትዳሮች በጋብቻ ሕይወታቸው ዋንኛው የስጋ አንድነት እስከሆነ እንጣጣም ይሆን? ወይም አልተጣጣምንምና ከወዲሁ እንለያይ? ወይም እንፋታ ሊሉ አለመቻላቸውን ለማስገንዘብ የተፈለገ ንባብ ነው።

እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሰራሽ ችግር ሊለየው ባለመቻሉ በመጨረሻም ተጫጪዎችም ሆኑ ባልና ሚስት ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን «እኛ ልባችንን በሰፊው ከፍተን ስሜታችንን እንደገለጥንላችሁ እናንተም ልባችሁን ከፍታችሁ ስሜታችሁን ግለጡልን» (2ቆሮ 6፡ 13) እንዳላቸው ሁሉ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ግልፅነት በመንፈሳዊ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ፣ በአእምሮአዊ፣ በአካላዊና በስሜታዊ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ሁለቱ ልባቸውን አስፍተው ሊተዋወቁ ይገባል፡ ይህ በአደገበትና በፀናበት የእግዚአብሔር ፍቺን አፀየፋለሁ ቃል ጽኑ መገለጫ ይሆናል።

# ቃል ኪዳንና ምንነቱ

ቀን የተለየ ክብር ይኖረዋል የሚል እምነት የለኝም፤ እምነቴ በቀኑ ውስጥ የተከናወነው ተግባር ቀኑን የተለየ ሊያደርገው ይችላል፤ ከዚህም የተነሳ፡-

መስከረም አንድ፣ መስከረም አስራ ሁለት እና ታህሳስ ሀያ ስድስት የግሌ መታወሻ አላቸው። ቀናቱ ለዚከ ለባለቤቴና ለእኔ የተለያዩ ክንውኖች ተፈፅመውባቸዋልና አይረሱም።

ከዚከ ጋር በጋብቻ ጉዳይ ላይ ተሳስበን ወደ ማጠቃለያው የተንደረደርነው ትውውቁን በጀመርን በስድስት ወራት ውስጥ ነበር፤ እሷ የምትገለጥ ብቻ ሳይሆን ቶሎ ቶሎ የምትነበብ መፅሐፍ ስለሆነችልኝ የትጭጭቱ ጊዜ አጥሯል።

ለማጠሩ በወቅቱ የነበረው መጋቢዬ ይስሐቅን በማንሳት አብርሀም የላከው ሎሌ ለጌታው ልጅ የምትሆነውን ስላገኘ ያለው ቃል «አታዘግዩኝ » የሚል ነበር፤ ይህን ታሪክ መጋቢው በማብራራት በጣይቱ ሆቴል ባህላዊ አዳራሽ ውስጥ «የምትዘገዩበት ምንም ነገር የለም» የሚል ውሳኔን አሳለፈ፤ ከዚህም የተነሳ ታህሳስ 26/1989 የሰርግ ስርዓታችን በእቴጌ መነን አዳራሽ ተገኝተን ፈፀምን።

የዛን ዕለት ፍስሀ ደጀኔ ቃል ኪዳን አስገባን፤ ጌታቸው በለጠም ቃለ እግዚአብሔርን በማቅረብ አያያዘን። የወንድማገኝ ታከለ አመራርና የቦሌ ባፕቲስት መዘምራን ከፒተር ማርዬ ዝማሬ ጋር ያንን ቀን አደመቁት።

***

ከዚህ ቀን በፊት ያሉ ሁለት ቀናትም ለእኛ አይረሴ ናቸው፤ እነርሱም ወግን የሸራረፍንበት





የመስከረም አንድ ማለዳ አንዱ ሲሆን ሌላው በወንጌላውያን ዘንድ እንግዳ ግን በአግባቡ ከተሰራበት ጠቃሚ ሊሆን የሚችልን ክንውን በቤዛ ባፕቲስት ቤ/ክ መስከረም 12 ላይ አደረግን።

በዕለተ የዘመን መለወጫ ዚከ ወደ እናት አባቴ ቤት መጣች፤ በዓል ነው፤ አዲስ አመት፤ በዚያን ቀን ሁለታችን ፈጥነን መከርንና «ዛሬ ብንናገርስ» ተባብለን ወዲያው ተስማማን፤ እናም በእኔ አጋፋሪነት በእርሷ ዐይን አፋርነት «የማገባትን ልጅ ላስተዋውቃችሁ» አልኩኝ።

በዕለቱ ተመከረ፤ ደስታም ተፈጠረ፤ ሁሉም አወቀ፤ ከዚህ በኋላ መስከረም አስራ ሁለት ነው ተከታዩ፤ እሱ ደግሞ በቤተክርስቲያኑ መሪ በፍቅሩ ገበየሁ ተመርምረን ሲያበቃ መጋቢው ወደ ጉባኤ በማምጣት «በጋብቻቸው ላይ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ተቃውሞ ካለ ተናገሩ» አለበት፤ ሆነም ያኔ በዕለተ እሁድ «ጥሎሽ ይጣላል ወይ? ትውውቁ እንዴት ተጀመረ? ማን ቀድሞ የማፍቀር ጥያቄ አነሳ?» የመሰሉ ጥያቄዎች ቀረቡ፤ ሁሉም በአግባቡ ተመልሰው ሌላው የደስታችን እሁድ ሆኖ አለፈ፤ በቤትም በቤተክርስቲያንም ይለፍ የተባለ ትውውቅ ነበረን፤ ይህን አንረሳውም።

በዚህ መጣጥፍ ደግሞ ተያያዥነት ስላለው ቃልኪዳን ላይ መናበብ እንደሚያስፈልግ አምኛለሁ፤ይህን ደገሞ ከተጋቢዎች ማንነት ላይ በመነሳት ጥቂት ልበል። ተጋቢዎቹ ሁለት ሰዎች ናቸው፤ ወንድ እና ሴት፤ መልካቸው፣ አፈጣጠራቸው፣ ልምምዶቻቸው፣ የተማሩበት፣ የኖሩበት፣ ያደጉበት፣ የሚያመልኩበት፣ ሁሉ የተለያየ ሁለት ሰዎች ናቸው፤ ይልቅኑ እንደ ሁኔታው ለተግባቦት የሚበቁበት ቋንቋቸውም ጭምር ይለያያል።

ይህን የመሰለ ግንኙነትን አስመልክቶ ፍቅር እስከመቃብር ታወሰኝ፤ ይህ መፅሐፍ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ለንባብ የቀረበ የዶክተር ሀዲስ አለማየሁ መፅሐፍ ነው፤ መላው ኢትዮጵያ የተዋወቀው መፅሐፍ ነው ብል አልሳሳት ይሆናል፤ ይማሩበታል፤ ይተርኩታል፤ ራሳቸውን ያዩበታል፣ ይተነትኑታል፤ የዚህ መፅሀፍ ምዕራፍ ሁለት «በዛብህ» በማለት ተሰይሟል፤ በምዕራፉ ውስጥ ባልና ሚስቱ ትዳርን እንዴት ጀምረው እንዳዘለቁ ይዘረዝራል።

«አቶ ቦጋለ መብራቱ ወይዘሮ ውድነሽ በጣሙን ባገቡ በሁለተኛው አመት መጨረሻ ወንድ ልጅ ተወለደላቸው ብቻ ሁለቱ የሁለት አለም ሰዎች ስለነበሩ ይልቁንም ገና የጋብቻ ኑሮአውን እንደጀመሩ በመሀከላቸው ግጭቱም ኩርፊያውም ይበዛ ነበረ። ነገር ግን እግዚአብሔር እድሜ ከሰጠ ለለማድ በቂ ጊዜ ከተሰጠው እንኩዋን ሰውን ጅብና አህያን ነብርንና ፍየልን አብረው እንዲኖሩ ለማድረግ ስለሚቻል ጊዜ ባለፈ መጠን ባልና ሚስት እርስበርሳቸው እየተዋወቁ እየተለማመዱ እየተዋደዱ የመተሳሰብ ማሰሪያቸው እየጠበቀ ሄደ...» (ሀዲስ <u>**ፍቅር እስከ መቃብር**</u> ገፅ 19) በማለት ይገልፁታል።

በመሰረቱ በእሳቸው ልብ ወለድ ውስጥ በርካታ ቁም ነገሮች ታጭቀውበታል፤ በቀዳሚው በዚህኛው ምዕራፍ በፅናት የመከሩበት ሁነኛ ቃል፤ ሰውይለምዳል፣ ይዋደዳል፣ ያፈቅራል፣ አብሮም ይኖራል፤ ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር እርዳታ እና በተጋቢዎቹ ጥረት ፍሬያማ ይሆናል የሚል ነው።

ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ከመወለዳቸው ጋር ተሳስሮ ቃለ እግዚአብሔር እና ቤተክርስቲያን ኖራቸው ካደጉማ እንዴት የዚህ ልከኛ መገለጫ ተጋሪ አይሆኑ፤ እናም «እግዚብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» ያለበትን የአዋጅ ቃል ለማብራራት መጣርም ተገቢውም ተፈላጊውም መንደርደሪያ ይሆናል።

መጋቢያን፣ አስተማሪዎች፣ መካሪያን፣ እውነተኛ የቤተሰብ አቀንቃኞች በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ ቤተሰብ እንዲመሰረት ያስተምራሉ፤ ይፅፋሉ የማስተማራቸው መነሻም መድረሻም የእግዚአብሔር ሀሳብ ነው። ሀሳቡና ፈቃዱ ደግሞ በቅዱስ ቃሉ ላይ ተገልጧል፤ ያንን በአግባቡ በመግለጥ አቅጣጫ ማስያዝ የሚመለከተው ሰው ሁሉ አደራ ነው።

እንኪያስ መጋቢያን፣ አስተማሪዎችና የጋብቻ አማካሪዎች ተገቢ የሆነውን ለመግለጥ በመነሻነት ራሳቸውን ማየት ደግሞም በቅጡ ሁሉን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ልዑል የሆነው እግዚአብሔር አዳም ብቻውን ይሆን ዘንድ ባለመውደዱ ነው፤ ሔዋንን የሰጠው፤ በዚህም የባልና ሚስት ኑሮ ተጀመረ፣ ቤተሰብ ተቋቋመ፤ ይህ ቤተሰብ የቤተሰብ መነሻ ወይም የመጀመሪያ ስለነበረ በመኖር ውስጥ ይበዙ ዘንድ ታዘዙ፤ ቤተሰብ መነሻውን በባልና ሚስት ላይ ያደርጋል፤ ከዚያም ከእነርሱ ጋር ተከትሎ የሚመጣ ምንም ነገር ቢኖር በቤተሰብ ምንነት ውስጥ ይካተታል።

በስርዐተ ጋብቻ ጊዜ ሁለት ወንዶች ሊጋቡ አይመጡም፤ ሁለት ሴቶችም በቤተክርስቲያን የጋብቻ ጥያቄን ይዘው አይገኙም፤ በጌታ የሆኑ ወንድና ሴት ግን ለመጋባት ፈቅደው ከፍቅር ሕይወትና በጌታ ከመሆን የኑሮ ፈሊጥ ጋር ተጋምደው ይመጣሉ፤ በዚህ ግዜ የሚመለከታቸው ሁሉ ቀጣይ ሕይወታቸው እንዴት ሊመራ እንደሚችል በመጠቆም ያደረጇቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች መሳለቂያ እንዳያደርጉት የፈራለትን ሰው በምሳሌ መምከሩ ለዚህ ነው...ሊሰራ **ጀምሮ ኪደመድመው ኣቃተው . . .** በማለት መንገደኞቹ እንዲያፌዙ የቅድመ ትዳር እና የድህረ ትዳር ምንነትን በቅጡ አብራርቷል።

ቤተሰብ የባልና ሚስት ጉዳይ ነው፤ የህብረተሰብ መገንቢያ፣ የሀገር ሕልውና የእህጉር መገኛ እና የዓለም ቋንቋ ነው፤ የቤተሰብ ሕልውና መከበርና መጠበቅ አለበት፤ በዚህም ጉዳይ





ሁላችንም በየአጥቢያዎቻችን እንድንመከር ይገባል።

ቤተሰብ ባይመሰረት እና ባይኖር «ምንም» አይኖርም ነበር፤ ይህ ተቋም ፍሬያማ በመሆን እስከፍፃሜው እንዲዘልቅ መገንባት የዛሬ ስራችን ነው። የ2004ቱ «በግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ ኢትዮጵያ» የተዘጋጀው ምጥን ፅሑፍ ትኩረቱ ጋብቻን በማፅናት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ተማርኬበታለሁ።

አፅንኦቱ ለሚመለከታቸው ሁሉ ቢሆንም ትኩረቱ ግን ቃልኪዳን ላይ ነው፤ይህም፤- *«እኔ እንተን/እንቺን ከዚህች ዕለት እንስቶ ልወድህ/ሽ ላከብርህ/ሽ የሚያስፈልግህን/ሽ ሁሉ ላደርግልህ/ሽ በመልካም ጊዜም ቢሆን በክፉ ጊዜ፣ በማግኘት ቢሆን በማጣት፣ በጤንነት ቢሆን በሕመም እስከ ሕይወቴ ፍፃሜ ድረስ ላልለይህ/ሽ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባኤ ፊት ቃል እገባለሁ»* ከሚለው ቃል ይጀምራል፤ በመሰረቱ ይህን ቃል ባልና ሚስቱ በተፈላለጉበት፣ በተፈቃቀዱበት፣ በተዋደዱበት ጊዜ ላይ ሆነው የሚሉት ስለሆነ በወቅቱ ልብ ላይሉት ይችላሉ፤ ልብ ላለማለታቸው በቂ ምክንያት ያኖረው ይሆናል፤ ወይ አባባሉ ያለለውጥ ለአመታት በየትም አጥቢያ በመደመጥ የዘለቀ ስለሆነ ሰሚው አዝናኝ ሙዚቃ ብቻ ሆኖለት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት እፈፅመዋለሁ ያለውን ቃል ልብ ላይለየውና ላያውቀው ይችላል፤

አልያም ግዜ ይፍታው ብሎ/ብላ ደስታውንም ችግሩንም እንዳመጣጡ አስተናግደዋለሁ በሚል ተስፋ ተጋቢዎቹ ከግምት ላያስገቡት ይችላሉ።

ቤተሰባዊ ሕይወት ግን በትምህርት ቤት የሚመስል ተቋም ስለሆነ ሁለቱ በገቡበት ትምህርት ቤት የጋራ ኮርሶችን ይወስዳሉ፤ በዚያ የሚሰጡ ትምህርቶች ሁሉ ቃኪዳኑን ያጣቁማሉ። ለዚህ ደግሞ ልብን ከራስ ወዳድነት በመጠበቅ እግዚአብሔርን ለሚያከብር ጤናማ ትዳር መዘጋጀት ቅድሚያውን ይወስዳል።

> *ቃሉ፡- «በቀረውስ ሁላችሁም አርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ የሌላውን ሰው ችግር እንደራሳችሁ አድርጋችሁ አስቡ በወንድማማችነት ፍቅር ተዋደዱ ደጎችና ትሁቶች ሁኑ፣ መርቁ እንጂ ክፉውን በክፉ ፈንታ ስድብንም በስድብ ፈንታ አትመልሱ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት ይህን በማድረግ በረከትን ለመውረስ ነው...» (ጴጥ 3፡8-9) ይላል*

ይህ ገለፃ ቃል ኪዳን እውነት የሚሆንበትን ስፍራ ያመለክታል፤ ሁለት ሰዎች የተዋደዱ ሆነው ቢጀምሩም ኑሮአቸው ወደ ሚመዘንበት፣ ይቅርታን ሁሌም ወደሚቸሩበት ሕይወት ገና አልገቡም፤

ከገቡም አንድ የሆኑበት ቀን ነው ተቆጣሪው፤ ከዚህ በኋላ ተጋቢዎቹ በርካታ ተግዳሮቶች አሉባቸው፤ አሉላቸው፤ ይህን ግን «...ሕይወትን የሚወድድና መልካም ቀኖችን ማየት የሚፈልግ ሁሉ ምላሱ ከፉ ነገር እንዳይናገር ከንፈሮቹ ተንኮልን እንዳይናገሩ በመከልከል ከክፉ ነገር በመራቅ መልካምን ነገር ብቻ በማድረግ ሰላምን በመፈለግ እራሱን ሊከተል ይገባል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ፃድቃን ይመለከታሉ ጆሮዎቹም ፀሎታቸውን ለመስማት ተከፍተዋልና» (1ጴጥ 3፡10) በማለት ያብራራል።

እነዚህ መለኮታዊ ገለፃዎች ተፈትሸው የሚያልፉት ቤተሰብ ውስጥ ነው። በተመሰረተ የባልና ሚስት ኑሮ ውስጥ።

ሌላኛው የዘላቂ ትዳር መገንቢያ «የትዳር አጋርን ሙሉ ለሙሉ መቀበል ነው» ይህ ጥረት ይጠይቃል። ሰው መሆን ደግሞ ማህበራዊ፣ አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስሜታዊና ተነካኪ በርካታ ገፅታዎች አሉት፤ በእነዚህ ሁሉ የተፍታታ ግንኙነት ይኖር ዘንድ ከመነሻው መተማመን ተፈላጊ ነው።

ይህ ሲሆን የ«ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ» (ዘፍ 2፡2) የተፈፃሚነቱ አቅም በየጊዜው ያድጋል። እውንም ይሆናል። ይህ ገለፃ የሩካቤ ስጋን ተመልከቶ አይቆምም፤ ይህ መነሻውም መድረሻውም አይደለም፤ ይልቅስ ይህንና አብሮ ተጓዦቹን አካቶ የአንድ ስጋ መሆኑን ጭብጥ ያፀናል።

ዘፍ 2፡25 «አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር» ማለቱም የዚሁ የመቀባበል መሰረት ላይ የቆመ ነው፤ በሁሉ ነገር ራቁት መሆንን እግዚአብሔር ከመነሻው አብስሯል፤ ሀጢአት ወደ ሰው በመግባት መተፋፈርን ይዞ ቢመጣም በዚሁ መተፋፈር ውስጥ ዘርፈ ብዙ የሆነ «እርቃንነት» አስፈላጊ ነው። ባልና ሚስት ከነበራቸው የትናንት አስተዳደግ የሚደብቁት ወይም መግለጥ እንዳለባቸውም ከግምት የማይከተት ብዙ ነገሮች ቢኖሩም ይህ ግን በትምህርት ቤቱ ውስጥ እስካሉ ድረስ በአግባቡ እየተገለጠ መዝለቅ አለበት።

ሌላው የዘላቂ ትዳር መገንቢያ ከሆኑት ውስጥ አንዱ «እውነተኛ የሆነውን አንድነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእምነት መለማመዳቸውን መቀበል ነው፤ የዚህ ደግሞ መሰረቱ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በመገንዘብ ተግባራዊ በማድረግ መኖር ነው፤ ይህ አኗኗር ሁልጊዜ በሁለቱ ሰዎች ዘንድ ተመጣጥኖ መታየት አለበት።

ኢየሱስ በስልጣን ከተናገረባቸው መገለጫዎቹ ውስጥ አንዱ የልባሙና የሰነፉ ሰው ቤት አሰራር ነው«...ይህን ቃሌን ሰምቶ በስራ ላይ የሚያውለው ሁሉ ቤቱን በአለት ላይ የሰራውን





ብልህ ሰው ይመስላል፤ ዝናብ ዘነበ ጎርፍም ጎረፈ፣ ነፋሰም ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ይሁን እንጂ ቤቱ በአለት ላይ ስለተመሰረተ አልወደቀም ይህን ቃሌን ሰምቶ በስራ ላይ የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሰራውን ሞኝ ሰው ይመስላል፤ ዝናም ዘነበ፤ ጎርፍም ጎረፈ፤ ነፋሰም ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ቤቱም ወዲያውኑ ወደቀ፤ አወዳደቁም እጅግ የከፋ ሆነ...» (ማቴ 7፡24-27) ይህ የኢየሱስ ገለፃ በሚመሰረተው ቤት ላይ በባልና ሚስቱ ሕይወት በእኩል ደረጃ ሊገለጥ ይገባዋል።

ቤተሰብ መመስረቱ የትውልድ ቀጣይነትን በበጎ ለማኖር መወሰኑ ነው፤ ኑሯአችን ከራሳችን ያለፈ መሆን አለበት፤ ትውልድ እንደ ሰንሰለት የተያያዘ ቢሆንም ትውልዱ ግን የዱላ ቅብብልን በሚመስል ኑሮ ተገላጭ ነው፤ ዘመኑ በእግዚአብሔር ሀሳብ የተሞላ ሆኖ መስፋፋት አለበት፤ ይህ ደግሞ መስራት የሚችለው በቤተሰብ ውስጥ ነው።

«...በብዙ ምስክሮች ፊት ከእኔ የተማርኸውን ትምህርት ሌሎችን ለማስተማር ችሎታ ላላቸውና ለታመኑ ሰዎች አስተላልፍ» በማለት ኑሮአችን ከቀጣዩ ትውልድ ጋር የተሳሰረ መሆኑ ሐላፊነቱን ያከብደዋል፤(2ጢሞ 2፡2)«...ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትዕዛዛት አትርሳ እነዚህኑ ትዕዛዛት ለልጆችህ አስተምራቸው በቤት ስትቀመጥም ሆነ በመንገድ ስትሄድ ዕረፍት በምታደርግበትም ጊዜ ሆነ ስራ በምትሰራበት ጊዜ ሁሉ እነህን ትዕዛዛት ዘወትር አሰላስል...» (ዘዳ 6፡1-10) ከቀድሞም መባሉ ቤተሰብን የሁሉ ሀብት መገኛ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ዶ/ር የሺጥላ መንግስቱ «የማገባው ማንን ነው?» በማለት በፃፉልን ሰነድ ይህን የመሰሉ በርካታ መሰረታዊ ጭብጦችን አብራርቶልናል። ይልቅኑ በመነሻችን ላይ ያነሳነውን ቃል ኪዳን መግባት ለድህረ ጋብቻ አጠቃላይ አኗኗር ተፈላጊ መሆኑንም ፅፎልናል።

ብዙዎች ጋብቻቸውን ቃል ኪዳን በማይፈፅምባቸው ባህላዊና መንግስታዊ የጋብቻ መስመሮች ውስጥ በመገኘት ይፈራረማሉ ወይም ያለ ፊርማ አብረው ይኖራሉ በክርስቲያናዊ ማህበር ውስጥ ቃል ኪዳንና ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ቢከናወን ተመራጭ ነው፤ ይህም እንደ የሺጥላ አባባል የእግዚአብሔርን ባርኮት ለመቀበል፣ ተጋቢዎች ያለባቸውን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ለማስገንዘብ፣ አንዱ ለሌላው ያለበትን ግዴታ ለማስተዋል እንዲሁም የምዕመናንና የመሪዎች ፀሎት፣ ምክር እና እንክብካቤ ለማስገኘት ይረዳል።

ይህ ቃል ኪዳን ደግሞ መነሻውን ያደረገው በሁለቱ ተጋቢዎች አጠቃላይ ተፈጥሮ ውስጥ ልዑል የሆነው እግዚአብሔር ተጋቢዎቹን፡-

- ጉልበት፣ ውበት እና ራሳቸውን የመተካት ችሎታ በመስጠት በመፍጠሩ፣

- *ማፍቀር፣ መቀራረብና መሳሳብን የሚያስችል ስሜታዊ አቅምን በፍጥረታቸው ውስጥ በማድረጉ፣*
- *የሚያስቡ፣ የሚያመዛዝኑ፣ የሚወስኑ፣ የሚቀይሱና ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የመትጋት አቅም ያላቸው መሆኑ፣*
- *ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ በመገናኘት የፈጣሪን ሕብረትና ግንኙነት በዕለታዊ ኑሮአቸው ለመፈፀም በውስጣቸው አቅም በመኖሩ የገቡት ቃል ኪዳን ተፈፃሚ ለመሆን ጉልበት አለው(የማገባው ማንን ነው?ገፅ* 155)

ቃል ኪዳን እግዚአብሐርን ለማክበር ቅድሚያ የመስጠት መገለጫ ነው፤ ቤተሰብን እግዚአብሔር እስከ አቋቋመ ድረስ እሱው እስከ መራው ድረስ ተቋሙ ከእርሱነቱ የመነጨ ለሰዎች የተሰጠ ቸርነት መሆኑን ተጋቢዎቹ አሳወቁ ማለት ልዑሉን አከበሩ ማለት ነው።

ቃል ኪዳን የዛሬው ደስታና ፍንደቃ በቀጣይነት ላይኖር ቢችል እንኳ ኪዳኑ ጉልበትን በመፍጠር እግዚአብሔር ያጣመራቸውን ሊያኖራቸው እንደሚችል ማረጋገጫ ነው (ማቴ 19፡ 6) ይህ ደግሞ ሁል ጊዜም ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባውን ማወቃችንን ያበስራል፤ ቃል ኪዳንን መጠበቅ አስቸጋሪ ሊሆን የሚችለበት በርካታ ጊዜያት ይኖራሉ፤ እነዚህን ፈታኝ ጊዜዎች የመቋቋም አቅምን ይፈጥር ዘንድ ሁልጊዜ «ቃል ኪዳን የገባሁት ሌላውን እንደራሴ በመውደድ እንድዘልቅ ነው» ያስብላል።

በቃል ኪዳን ውስጥ ትዳሩ የማያቋርጥ ጥረት መጠየቁንም ያመላክታል። አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር የተጠጋጋ ግንኙነት በመፍጠር ሲኖር ግንኙነቱ እየሰፋ፣ ቤተሰቡ ሲደረጅ በዚያ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ክርስቲያናዊ እሴቶችን የሚለኩበት የመፈተኛ ስፍራ ይገኛል፤ ይህም ዕድገትን፣ መተሳሰብን እና ጥንካሬን ያመጣል።

ይህ ቃል ኪዳን ግን በቅድመ ጋብቻ የመነሻ ጊዜ ውስጥ አቆጥቁጠው ያሉ በጎ ምልክቶች ሆነው መገኘታቸውን ሁሌም ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ ይህም በአካል በማደግ የሰውነት ዕድገትንና ጥንካሬን ማሟላት፣ በአእምሮ በመብሰል ሐላፊነትን የመቀበል ብቃትንም መያዝ ነው ይህም፣ በማህበራዊ ጉዳይ ላይ በመደጋገፍ ከራሳቸው የወጣ የማይመስለው የራሳቸው ክፋይ መሆኑን መረዳት፣ በመንፈሳዊ ጥንካሬ የክርስቶስ ከመሆን ባሻገር ወደ ክርስቶስ ቁመት ለማደግ የሚጥርን የቃል ኪዳን ውጤታማ ኑሮን ያመጣል።(**የማገባው ማንን ነው?** ገፅ 92)



# «ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሀም ግባ. . . ስራህንም አድርግ. . .

*ራዕ 2፡5*

ወደ ኋላ ስለመመለስም ሆነ ወደ ፊት ስለመሄድ ለመነጋገር አቅም የሚገኘው የመነሻ ስፍራን ማወቅ ሲቻል ነው፤ ከዚህም የተነሳ የቅድመ እና የድህረ መገለጫ ኖረ።

- ❖ ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለን ዘመን ለማመልከት ቅድመ ክርስቶስ እንላለን፣
- ❖ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለን ዘመን ለማመልከት ድህረ ክርስቶስ እንላለን።

ለድህረም ሆነ ለቅድመ ክርስቶስ የመነሺያ ወይም የመቁጠሪያ መለኪያ ሆኑዋል። እሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ነው።

ዛሬ ላይ ቆመን፡- ስለ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ለመናገር እና ስለ «ደርግ» ዘመነ መንግስት መነጋገር ቢያስፈልግ አሁንም መነሻ ጊዜ ያስፈልጋል። ያም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት ያበቃበት መስከረም 2/1967 ን መለያ በማድረግ ቅድመ ደርግ የንጉሱ የአገዛዝ ዘመንን ለማመልከት፣ ድህረ ቀ.ኃ.ሥ የደርግ የ17 ዓመታት ታሪክን ለመግለፅ እና ከዚያ በኋላ ያለውን የወቅቱን መንግስት ለማብራራት የመነሻው መስመር ይሆናል።

***

መቼም ቢሆን የአንድን ግለሰብ የሕይወት ጉዞ ለመከፋፈል መነሻ ማድረግ የሚቻለው ልደቱን ነው። ከመወለዱ በፊት ያሉትን የዘጠኝ ወራት ወቅትን ቅድመ ልደት፣ ከተወለደ በኋላ ያሉትን ግዜያት የአራስነት ፡- የሕፃንነት ፡- የልጅነት ፡- የወጣትነት፡- የጎልማሳነት፡- የሽምግልና እያለ የድህረ ልደትን ምንነት መግለፅ ይቻላል።

በመሰረቱ የሰውን ቅድመ ልደትና የድህረ ልደቱን ሕልውና ከእግዚአብሔር እይታ አኳያ እንመዝን ካልን ደግሞ፡-

- ➢ እግዚአብሔር ከሰው ቅድመ እና ድህረ ልደት በፊት ስላሉት የየሰው ልጆች አካሄድ ቀድሞ በእርሱ የታወቀ እንደሆነና፤
- ➢ ልደትን ከሰው በመወለድ ላይ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም በመወለድ አብራርቶ ስለ ዳግም ልደት ይናገራል፣ ዳግም ልደት በራሱ መነሻ ሆኖ ቅድመ ዳግም ልደት እና ድህረ ዳግም ልደት በማለት የመለያ መስመር ሊሰመርለትም ይችላል።

አንባቢያን ሆይ በአንድ ወቅት በተከናወነ ከንውን አቅጣጫን የቀየራችሁበት ወይም ያሻሻላችሁበት የራሱ የሆነ የታሪክ መነሻ አላችሁ።

ዛሬ ላይ መጋቢ፣ ዲያቆን፣ አስተማሪ፣ ዘማሪ፣ አስተባባሪ፣ ወንጌላዊ፣ ሚሲዮናዊ የሚሉ ተለጣፊዎችን ማንም ሳይለጥፍ ቀድሞ የክርስቶስ የሆንበት ጊዜ ነበር፤ ያን ጊዜን አንዳንዶች ላያውቁት ይችላሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ በቅጡ ሊረዱት ይችላል፣ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን «ነፋስ ከየት መጥቶ ወደየት ሊሄድ (ሊነፍስ) እንደሚችል» እንደማናውቅ በመኖር ውስጥ ከየት እንደ ወገንን ራሳችንን አይተን አውቀናል፤ በዚህም ክርስቲያን ሆነን ተገኝተናል።

ይህን የሕይወት መነሻ፡- «ዳግም ልደት» ወይም«ዳግም መወለድ» በማለት የእግዚአብሔር ቃል ይገልፀዋል። ኒቆዲሞስ የራሱ የሕይወት ቅድመ እና ድህረ ነበሩት፡-እስከ ሽምግልና ዕድሜው ድረስ፤-

- ስለ ዓለም ያለው አመለካከት፣
- ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ግንዛቤ፣
- ስለ ማህበራዊ ኑሮ ያለው አቋም፣
- በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤው





- ግለሰባዊ እና ቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ የነበረውን ሐላፊነቱን ይወጣ የነበረው

ዓለሙ ሁሉ «እንደ ሰው» እንደሚኖረው አኗኗር ነበር፤ አንድ ቀን ግን ወደ የወቅቱ መምህር መጥቶ፡ - (ዮሐ 3፡2) «...ከእግዚአብሔር *ዘንድ የመጣህ መምህር እንደሆንህ እናውቃለን» አለው ኢየሱስ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣትህን ተረድቻለሁ ያለውን ሰው የጠየቀው«...እውነት እልሀለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፤ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው፤ ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁህ አትገረም፤ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከየት እንደመጣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው»* አለው። (ዮሐ 3፡5)

ኒቆዲሞስ በመኖር ውስጥ እያለ ዳግም ተወልዶ ራሱን በጊዜ ውስጥ አግኝቷል። እኛም እንደኒቆዲሞስ «የዳግም ልደት» ታሪክ በአንድ ወቅት የተከናወነልን ሰዎች ከሆንን፤- ይህ ዳግም መወለድ ለሁለት መሰረታዊ ጉዳይ የማንነት መለኪያ ሆኖ ያገለግላል።

**አንድ፡-** ዳግም መወለድን የኑሮ መነሻ በማድረግ ስለ ቅድመ ዳግም ልደት አኗኗራችን መናገር፤ መመስከር፣ ማመዛዘን ያስችለናል።

**ሁለት፡-** ዳግም መወለድ የሁሉ ነገር መነሻ በመሆን ስለ ድህረ ዳግም ልደት በቅጡ ለማየት ለመመዘን፣ ለመገንዘብ የሚያስችልን ኑሮን በማመልከት መነሻ ሊሆን ይችላል።

ይህም ሰው የስጋ ልደትን በመወለዱ ጊዜ በማግኘቱ ከዚያ በኋላ ያለውን አመታት አንድ፣ ሁለት፤ አስራ ሁለት፣ አርባ፣ ሀምሳ፤ ወዘተ አመቴ በማለት ከመወለዱ በፊት የነበሩትን የቅድመ ልደት ታሪክን ከግምት ሳያስገባ እንደሚናገር።

እኛም ዳግም ልደትን መነሻ በማድረግ ድህረ ዳግም ልደትን ማጤን የዛሬው የመናበቢያ ትምህርት ይሆናል።

ሳኦል የተባለው ጳውሎስ በቅድመ ዳግም ልደቱ፡-

- ➢ በትምህርቱ የተመሰገነ፣
- ➢ በማህበራዊ ሕይወቱ "እንከን የማይወጣለት፣"
- ➢ በፈሪሳዊነቱ ተደማጭ፣

- ➢ በዓለም አቀፍ ዕውቀቱ ከማንም የተሻለ ሰው ሆኖ ይኖር ነበር፤፤

እነዚህን ሁሉ ይዞ ትክክል ነኝ ብሎ በማመኑ ከእርሱ ግንዛቤ እና እምነት ወጡ ያላቸውን ሊያጠፋ ተነስቶ ነበር። ይህን ደግሞ ለማድረግ መነሳሳቱ እምነቱ፤ አደራው እና ሐላፊነቱ ስለነበረ ቀናኢነቱ ተገቢ ሊሆን ይችላል። በዳግም ልደቱ መነሻ ላይ ግን መሰረታዊ ለውጥ በሕይወቱ በመከሰቱ መለወጥ ያለበት እምነቱ ተለወጠ። መሻሻል ያለበት ተሻሻለ። መታረም ያለበት ታረመ። መተው ያለበት ተተወ።

ከዚህም የተነሳ የጳውሎስ መነሻ ግልፅ በሆኑ የተግባር መመሪያዎች ተመራ። በዚያው ጊዜ ነበር ጌታ ራሱ በሐዋ 9፡15 «ይህ ሰው በአሕዛብና በነገስታት ፊት እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ ዕቃዬ ነው» ብሎ ያወጀው። እሱንም በተመለከተ «...ወዲያውም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በምኩራቦች መስበክ ጀመረ...» ይለናል። (ቁጥር20) ከዚያም:-

ቁ 22 ሳውል ግን እየበረታ ሄደ በደማስቆ ለሚኖሩትም አይሁድ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማስረጃ እያቀረበ አፋቸውን ያስይዛቸው ነበር፣

ቁ 28 በኢየሩሳሌም በመዘዋወር በጌታ ስም በድፍረት ይናገር ነበር፣

ቁ 29 ከግሪክ አገር ከመጡት አይሁድ ጋር እየተነጋገረም ይከራከር ነበር ይላል።

***

የጳውሎስ ታሪክ ከድህረ ዳግም ልደቱ ስንነሳ የመነሻ ሩጫውን ከዚህ መስመር ላይ አድርጎ ጀመረ:- የጀመረበት መነሻ:- የአመለካከት ለውጥ፣

- የእምነት ለውጥ እና

- የአቋም ለውጥ ባስገኘ መነሻ ላይ ነበር።

አንባብያን ሆይ ልክ እንደ ሳኦል - ጳውሎስ የመነሻ ስፍራ የድህረ ዳግም ልደት ታሪክ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ራሱ እግዚአብሔር አከናውኖት ከሆነ፤ የዚያን መነሻ ምንነት ዕብ 12፡1 ን በመረዳት እንጀምር። «...በፊታችን ያለውን ሩጫ በፅናት እንሩጥ» ይላል። መቼም በየጊዜው ኢትዮጵያውያን ከዓለም ከተውጣጡ ሩዋጮች ጋር ይፋለማሉ፤ ሁሉም ሩዋጭ ከመሮጡ በፊት በመነሻው መስመር ላይ ይቆማል። ለመሮጥ መነሻ የሚሆነው ድምፅ (ተኩስ) እስኪሰማ ተጠባብቀው ሲተኮስ ሁሉም ይሮጣሉ ሮጠውም ሁሉም ያሸንፉ ነበር። ሁሉም ያሸነፉት:-





- ያቋረጠ ከመካከላቸው ባለመኖሩ፤

- ወደ ኋላ የተመለሰ ባለመኖሩ፤

- በፅናት ሩጫቸውን ስለቀጠሉ ሁሉም አሸናፊ ሆነዋል።

እርግጥ አሸናፊዎችን በቅደም ተከተል ለመለየት ተችሏል፤ እንኪያስ የመነሻ ታሪካቸው ዳግም መወለድ የሆነላቸውን ሁሉ የዕብራውያን ፀሐፊ እንዳለው በፊታቸውያለውን ሩጫ በፅናት ይሮጡ ዘንድ ይገባል። **መራር ቀልዶች** በሚለው የተስፋዬ ገብረአብ ስራ ውስጥ:- በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ድንገት ተከስቶ ስለነበረው ሩዋጭነት ያስነብባል።

*ሀይሌ ገብረስላሴ እና ቫለቃ ደራርቱ ቱሉ ዝናቸው በማሸነፋቸው ገኖ ስለወጣ በአዲስ አበባ፣ በየክፍለሀገር፣ በከተማው፣ በገጠሩ፣ በየተራራው ላይ ሩዋጮች በዝተው ታይተው ነበር።*

*ከነዚህ ውስጥ አንዳንድ ከተመኛ ሩዋጮች መሮጥ ጀምረው ሲደከማቸውና ሲታከታቸው ታክሲ ተሳፍረው መመለሳቸውን፣ ሌሎቹም ከልብ ድካም እና ከመሳሰሉ በሽታዎች ጋር ተያይዘው መግባታቸውን ያስታውሳል፤ ለአንዱ ሰው ግን እየሮጠ ሳለ የሆነ ሰው ብርቱካን ይሰጠዋል፤ ተቀብሎ ከመንገድ ዳር ካለው ዛፍ ስር ልጦ ከበላ በኋላ ተነስቶ መሮጡን ይቀጥላል፤ እየሮጠ ሆዱን ስለቆረጠው እናቶቹ እንዳስተማሩት በጣቱ መሬቱን እየነካ «ውጋቱን ላንተ ጤናውን ለኔ» በማለት ጎንበስ ቀና ሲል ሳየውቀው ዘግይቶ ኖሮ ስታዲየም ሲደርስ ለካስ ውድድሩ ተጠናቆ ስታዲየሙም ተዘግቷል።*

*ሩዋጩ ቁና ቁና እየተነፈሰ ዘበኛውን «የሉም እንዴ» ይላል ዘቡም*

*«የመቹህን ሁሉም መዳልያቸውን ወስደው ሄደዋል» ይለዋል።*

*«እንግዲያስ መጥቶ ነበር ብለህ ንገርልኝ» ብሎት ይመለሳል።*

እንደዚህ አይነት ሩዋጮች ፀንቶ በመኖር ምክር ውስጥ የሌሉ ናቸው ሳይጨርሱ የጨረሱ የመሰላቸው፣ ሳይሮጡ የሮጡ የመሰላቸው ናቸው።

ሐዋሪያው ጳውሎስ፡ - መነሻ መኖሩን፣ ከመነሻ ላይ ተነስቶ ፀንቶ መሮጥን፤ ሮጦም መጨረስ ተገቢ እና የግድ መሆኑን ያሳውቃል።

ከዚህም የተነሳ ጳውሎስ ራሱን በተመለከተ በ2ጢሞ 4፡7ላይ«...ሩጫውን ጨርሻለሁ...» አለ፤

ሩጫን መጨረስ:- የተሰጠ ሐላፊነትን ዳር ማድረስ ነው፤

- ውጣ ውረዶችን በሙሉ መወጣት ነው፣

- የቀረበውን ፈተና በአግባቡ ማለፍ ነው፣

- በሩጫው ላይ የገጠሙትን እንቅፋቶች ሁሉ መቋቋም ነው፤ሩጫ መነሻ ኖሮት እየሮጠ ያለ ሩዋጭ በሩጫው ውጤታማ የማያደርጉ ምክንያቶች (ችግሮች) ሊኖሩት ይችላሉ።

**አንደኛው:-** *ፀንተው እንዳይሮጡ በልብ የሚጉላላን ሌላ ሀሳብን መሸከም ነው፤* በአንድ ወቅት አንድ ሯጭ «የፍችና የንብረት ክፍፍል ጥያቄን ባለቤቴ ባነሳችብኝ ቀን ሮጥኩኝ በዚያን ቀን ህሊናዬ በሀሳብ ተወጥሮ ተጨንቄ ስለነበር በሩጫው ላይ ውጤታማ አልሆንኩም» አለ የስፖርት ልብሱ የላባ ያህል ቢቀልም የውስጡ ከከበደ ማሸነፍ ሕልም ነው።

**ሁለተኛው:-** *ራስን በአግባቡ ከመነሻው ጋር አለመቃኘት ነው፤ ሩጫውን ለመጨረስ ሊከፈል የተገባውን ዋጋ ሁሉ ቀድሞ አለማጤን ችግርን ያመጣል፤ በሀገራችን በጎ በመሰለ ዓላማ* ውስጥ ተገኝተው ግን ተበላሽተው የቀሩ ታሪኮች አሉ።

የኦሮማይ ፀሐፊ በዓሉ ግርማ በሀገሪቱ የተካሄዱትን ዘመቻዎች በገፀባህሪው ያናግራል *«...ነጋ ጠባ ዘመቻ፣ እድገት በኅብረት ብሎ ዘመቻ፣ ለጦርነት ዘመቻ፣ የኢኮኖሚ ግንባታ ዘመቻ፣ ማይምነትን ለማጥፋት ዘመቻ፣ በድንቁርና ላይ ዘመቻ፣ አረንጓዴው ዘመቻ፣ አሁን ደግሞ የኤርትራን ችግር ለመፍታት ዘመቻ፣ የዘመቻ ባህል ፈጥረናል ያለ ዘመቻ ኖረን የምንሞትበት ቀን መቼ ይመጣ ይሆን?»* (ገፅ 9) ማለቱ" ያስነብበናል፤ ይህ ንባብ በሁሉም ሩጫ ውስጥ ስኬት አለመኖሩን በመናገር ከመነሻው ከዓላማው ጋር አለመጣጣምን ያስተዋውቃል።

***

*ታህሳስ 1/1953 ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ተነሱ ሲነሱ ባለስልጣናቱን ከየአሉበት ለቅመው በአንድ ክፍል ከአጎሩ በኋላ የአዘጋጁትን ቃል አልጋ ወራሽ ተገድደው በሬድዮ እንዲናገሩ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሰማ ማድረግ ነበር፤*

*ይህን ከመፈፀማቸው በፊት ግን የክብር ዘብ መኮንኖችን በአንድ አዳራሽ ሰብስበው «ልዑል አልጋ ወራሽና ሚኒስትሮቹ ጃንሆይን ከድተው ነገ አልጋ ወራሹን ሊያነግሱ ነው፤ የጦር ሰራዊቱም የጃንሆይን መንግስት ከድቶ ከአልጋ ወራሹና ከሚኒስትሮቹ ጋር ተባብሮአል ስለዚህ እኛ ለጃንሆይ መንግስት መሞት አለብን» በማለት የተዛባ ዲስኩር ባቀረቡ ከአምስት ቀናት በኋላ ታህሳስ 6 ላይ መግለጫ አወጡ።*





*1. «ከተራ ወታደር ጀምሮ እስከ ሻለቃ ማዕረግ ድረስ የደሞዝ ጭማሬ መደረጉን*

*2. የከተማው ነዋሪ ሕዝብ አቅሙ የሚፈቅድለትን ቤት ሰርቶ እንዲኖር የሚል መግለጫ አስነገሩ። (አፄ ኃይለስላሴ ዘሪሁን ከበደ ገፅ720-751)*

እነዚህን በመሰሉና በሌሎች ሁለገብ ግንዛቤን በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ግን ቀድመው ስላልሰሩ እንደ ጀመሩት አቋረጡት።

***

በ1983 ኢ.ም. የሆነውም ተመሳሳይ ነው። ጀኔራሎቹ ፕሬዝዳንቱን ሕዝቡም ሰራዊቱም ጠልቷቸዋል፤ በሚል አቋም ሀገር ለመጎብኘት እንደወጡ በመከላከያ ሚኒስቴር ተሰባሰቡ። የተሰባሰቡት ወደ ማጠቃለያው ሳይደርሱ ሳያጠናቅቁ የአስመራው ጦር በጀኔራል ደምሴ ቡልቶ አማካኝነት መግለጫ አወጣ።

የአዲስ አበባዎቹ ገና ከመነሻው ጀኔራል አበራ አበበ እንቅስቃሴውን ለማየት የመጡትን ጀኔራል ኃይለ ጊዮርጊስን ገደሉ።

ጀኔራሎቹ ይህን ሁሉ ሲፈፅሙ የራዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ለመቆጣጠርና ከህዝብ ጋር ለመገናኘት አልሞከሩም፤ ከዚህም የተነሳ መነሻው ዳር ሳይደርስ ቀረ፤ የልብ አንድነት፣ የአላማ ፅናት ሳይኖርና ዙሪያ ገቡን ሳይረዱ የተነሱበት ሩጫ በአጭር ቀረ።

**ሦስተኛው:-**ሩዋጭ ሌላውን ባለማስሮጥ የሚገታበት ጥፋት ነው፤ ይህ ሆን ተብሎ ወይም በሌላ ተያያዥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ሁሉም መነሻውን አውቆ በፅናት እየሮጠ:- ሌላው ቀዳሚ ሩዋጭ ድንገት ከቆሞ ከኋላው በሙሉ አቅሙ የሚሮጠው ተላትሞ እንዲሰናከል ቢሆን ወይም ከፊት ከፊት የሚሮጠውን ከኋላው ያለው «አንተ የውሻ ልጅ» እያለ ቢጎነትለው፤ የተጣበበ በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ሲያገኘውም የእግሩን ኮቴ ቢመታው ወይም ልብሱን ቢጎትት ይህ ገጠመኝ ሩዋጩን ያዋዥቃል።

በእግር ኳስ ሜዳው ባንድ ወቅት «ዚነድን ዚዳ» ይኸው ተፈፅሞበት ስለነበር የደረት ቴስታ ለነገረኛው ሰጥቶ ገለበጠው፤ በመሰረቱ መገልበጡ አልጠቀመውም በቀይ ካርድ ከትግል ሜዳው አስቀረው። እንግዲህ ተወዳዳሪን ሁሉ ሰላማዊ ራዕይ አለው ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም።

**አራተኛው:-** በራሱ ሩጫውን ለመጨረስ:- ተግዳሮቶች አሉ፤ በዚህ ውስጥ ግን መጨረስ

መለኪያ መሆኑን አለማወቅ ሌላው ፈተና ነው።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን መነሻውን በውል አውቆ መሮጥ ከጀመረ 39ኛው አመት ላይ ተገኝቶ ከ 68-69 ዓ.ም ላይ በፃፈው ያረጋገጠልን እሱ፡-

- በሩጫው ላይ ለአንድ አፍታ አልቆመም፣
- ሩዋጮችን አላስቆመም ወይም ከኋላ አልጎተተም፣
- እየሮጠ ወደ ግቡ ለመድረስ አልተዘናጋም፣
- የሚሮጥበትንም ምክንያት በውል ሳያውቀ አልሮጠም፡
- ሩጫውን ያለ እንቅፋት አልዘለቀም፣
- በሩጫው ፀንቶ የሚከፈለው ዋጋ ሞትም ቢሆን ለመሞት ራሱን

አዘጋጅቷል።

***

በሩጫ ውድድርም ሆነ በእግር ኳስ ግጥሚያ ላይ ሰዎች ተሸናፊ መሆናቸው እርግጥ ሲሆን፡- ብዙዎች ግን ፈጥነው አሰልጣኙ ላይ፣ አሰልጣኙ ተጫዋቾች ላይ፣ ተጫዋቹ ፌዴሬሽን ላይ ፌዴሬሽን መንግስት ላይ፣ መንግስትም በወቅቱ በዓለም ላይ ከደረሰው «የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር» አገጣጥመው «እሮይ» ብለው ውለው ያድራሉ።

በሩጫ ፀንቶ ለማሸነፍም ሆነ ተጋጥሞ በድል ለመወጣት እያንዳንዱ ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤን መያዝ እንዳለበት ማመን የመፍትሄ ሁሉ ቁልፍ ነው።

አንድ ፀሐፊ «ዘመንን» እንደ አህያ ጀርባ ወይም እንደ ተንቀሳቃሽ ሲኒማ ማንፀባረቂያ ሸራ ነው በማለት መስሎታል፡-

በአህያ ጀርባ ላይ ኩበትም ሆነ ወርቅ የምንጭንበት እኛ ነን፤ በፊልም የማሳያ ሸራ ላይ ስድ ፊልም የምናሳይበት፣ ሀገር ገንቢ ስራም እምናቀርብበት እኛው ነን።

«...ዘመን አህያ ነው፤ የተጫነውን ሁሉ ተሸክሞ ወደፊት ያዘግማል ለነገ ማፈሪያም ሆነ መኩሪያ የሚሆን ተግባር የምናከናውነው እኛ ነን፤» ይላል እንኪያስ እያንዳንዱ በግሉ ተጠያቂ ነው።





ጳውሎስ በሐዋ 20፡31 «ሦስት አመት ሙሉ ሌሊትና ቀን ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ እያንዳንዳችሁን እንደመከርኳችሁ አስታውሱ» ይላል።

ከዚህም የተነሳ 2ጢሞ 4፡1-8 በሩጫ ላይ ላሉት ፀንተው እንዲጨርሱ አቅም የሚሰጡ መፍትሄዎችን አሳወቀ፤-

1. *በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው ክርስቶስ ኢየሱስ ፊት መገለጡንና መንግስቱን በማሰብ ይህን አደራ እልሀለሁ፤*
2. *ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግስትና በማስተማር አቅና፣ ገስፅ፣ አበረታታም፤*
3. *ብዙዎች እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ፤*
4. *አንተ ግን በሁኔታዎች ሁሉ የረጋህ ሁን፣ መከራን ታገስ፣ የወንጌል ሰባኪን ተግባር አከናውን፣ አገልግሎትህን ፈፅም፤*
5. *እኔ እንደ መጠጥ ቁርባን መስዋዕት ለመፍሰስ ተቃርቤያለሁ ተለይቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል፤*
6. *መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ ሃይማኖትንም (እምነቴንም) ጠብቄያለሁ፤*
7. *ወደፊት የፅድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ፃድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው።*

***

እያንዳንዳችን እየሮጥን ባለንበት መሮጥ ከጀመርን በኋላ የትጋ ወድቀን የትጋ ቀስ ብለን ከተሰጠን አቅም በታች እየሮጥን ይሆን?

በሩጫው ላይ ከወዴት እንደወደቅህ/ሽ አስብ/ቢ ንስሀም ግባ/ቢ የቀደመውንም ስራህ አድርግ/ጊ።